# በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ

# የ 2014 በጀት ዓመት የህዝብ ንቅናቄ መፍጠሪያ ዕቅድ

መስከረም 2014

ትምህርት ቢሮ

ባህርዳር፣

**ማውጫ**


| ተ.ቁ | ርእስ | ገጽ |
|---|---|---|
| | መግቢያ | |
| 1 | የእቅዱ መነሻ ሁኔታዎች ...................................................................... | |
| | 1.1. የትምህርት ስልጠና ረቂቅ ፖሊሲ እና ስትራቴጂዎች እንደመነሻ፤.................. | |

| ተ.ቁ | ርእስ | ገጽ |
|---|---|---|
| | 1.2. የ 2013 ዓ.ም የዕቅድ አፈፃፀምን እንደመነሻ፣ ......................................... | |
| | 1.3. በትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ የሕዝብ አስተያየቶች እንደመነሻ፣ ............ | |
| | 1.4. በክልልና በፌደራል ደረጃ የተዘጋጀው የአስር ዓመት ዕቅድ እንደመነሻ፤ ........... | |
| | 1.5. የድህረ 2015 ዘላቂ የልማት ግቦች እንደ መነሻ፤ ..................................... | |
| 2 | የ 2013 ዓ.ም. እቅድ አፈፃፀም ግምገማ ...................................................... | |
| | 2.1. የዝግጅት ምእራፍ አፈፃፀም ............................................................ | |
| | 2.1.1. የዕቅድ ዝግጅት ................................................................. | |
| | 2.1.2. ፈፃሚዎችን ማዘጋጀት ........................................................ | |
| | 2.1.3. የትምህርት ግብአት ማሟላት ................................................ | |
| | 2.1.4. አሠራርና አደረጃጀት ማጠናከር ............................................. | |
| | 2.2. የተግባር ምእራፍ አፈፃፀም .............................................................. | |
| | 2.2.1. በመልካም እሴቶች የታነፁ፣ በሁለንተናዊ ስብዕናቸው ብቁ የሆኑ ዜጎችን ማፍራት ............. ................................................................... | |
| | 2.2.2. የገበያ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ጥራት ያለው ትምህርት መስጠት ..... | |
| | 2.2.3. የትምህርት ስርዓቱን በዲጂታል ቴክኖሎጂ መደገፍ ........................ | |
| | 2.2.4. አካታች የሆነ ትምህርት ተሣትፎና ውስጣዊ ብቃት ....................... | |
| | 2.2.5. ከሥራ ጋር የተሣሠረ የጎልማሶች እና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ..... | |
| | 2.2.6. ያልተማከለ የትምህርት ስርዓት .............................................. | |
| | 2.2.7. የትምህርት ጥራት የማረጋገጥ ስርዓት ...................................... | |
| | 2.3. የማጠቃለያ ምዕራፍ አፈፃፀም .......................................................... | |
| | 2.4. ማጠቃለያ ..................................................................... | |
| | 2.5. ለቀጣይ ዕቅዳችን መነሻ የሚሆኑ ስኬታማ አፈፃፀሞችና ወሣኝ ጉዳዮች ............ | |
| | 2.5.1. ስኬታማ አፈፃፀሞች ......................................................... | |
| | 2.5.1.1. የትምህርት ተሣትፎና ተደራሽነት ................................ | |
| | 2.5.1.2. የትምህርት ውስጣዊ ብቃትና ጥራት ማረጋገጥ ተግባራት .... | |
| | 2.5.1.3. ሠላማዊ የመማር ማስተማር ተግባራት .......................... | |
| | 2.5.2. ዋና ዋና ፈተናዎች ........................................................... | |
| | 2.5.2.1. ፍትሃዊ የትምህርት ተደራሽነትና ተሣትፎ ...................... | |
| | 2.5.2.2. የትምህርት ውስጣዊ ብቃትና ጥራት .............................. | |
| | 2.5.3. ለቀጣይ እቅዳችን መነሻ የሚሆኑ መነሻ ጉዳዮች ......................... | |
| | 2.5.3.1. የትምህርት ጥራትና ተገቢነት ማረጋገጥ፣ ......................... | |
| | 2.5.3.2. የትምህርትን ተሳትፎና ተደራሽነት ማስፋት፣ .................... | |
| | 2.5.3.3. መልካም አስተዳደርና ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሁኔታ በትምህርት ተቋማት ማረጋገጥ፣ ........................................... | |
| | 2.5.3.4. የትምህርት ግብአቶችን በስታንደርዱ መሠረት ማሟላት፣ .... | |
| 3 | የእቅዱ ዓላማ፣ ግቦችና ዒላማዎች .......................................................... | |
| | 3.1. ዓላማ ........................................................................... | |
| | 3.2. ግቦች ........................................................................... | |
| | 3.2.1. በትምህርት ዘርፍ በየደረጃው የላቀ የመፈፀም አቅም ያለው የትምህርት አመራር፣ ፈጻሚና ባለድርሻ አካላት መፍጠር። .................................. | |
| | 3.2.2. በክልላችን የሚሠጠውን የአጠቃላይ ትምህርት ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ፣ ................................................................ | |
| | 3.2.3. የትምህርት ተደራሽነትና ፍትሃዊነትን ማረጋገጥ፣ ....................... | |
| | 3.2.4. የትምህርት ቤቶችን መሰረተ ልማትና ግብዓት ችግሮችን በመፍታት ቢያንስ 75% የሚሆኑትን ትምህርት ቤቶች የተቀመጠውን ትምህርት ቤቶች ደረጃ ስታንዳርድ እንዲያሟሉ ማድረግ። ..................................... | |
| | 3.2.5. በትምህርት መዋቅሩ መልካም አስተዳደርን በማስፈን ልማታዊ አስተሣሠብን ማስረጽ፣ ሰላማዊ የመማር ሁኔታን ማረጋገጥ፣ .................. | |
| 4 | ዓላማና ግቦች ለማሣካት የሚከናወኑ ቁልፍና አበይት ተግባራት ........................ | |

| ተ.ቁ | ርእስ | ገጽ |
|---|---|---|
| | 4.1. የዝግጅት ምእራፍ ተግባራት አፈፃፀም ................................................... | |
| | 4.1.1. የ 2013 ዕቅድ አፈፃፀምን በየደረጃው በመገምገም ለ 2014 ዓ.ም ዕቅድ በትምህርትነት የሚወሰዱ ጉዳዩችን መለየትና ጥቅም ላይ ማዋል ................ | |
| | 4.1.2. ጥራት ያለው የተሟላ ዕቅድ ማዘጋጀት ...................................... | |
| | 4.1.3. ፈፃሚና ባለድርሻ አካላትን የማዘጋጀት ሥራ በብቃት መፈፀም ........... | |
| | 4.1.4. አደረጃጀትን መፍጠርና ማጠናከር ............................................ | |
| | 4.1.5. የአሠራር ግልጽነት መፍጠር ................................................. | |
| | 4.1.6. ግብአትን በወቅቱ ማቅረብ .................................................... | |
| | 4.1.7. በ 2014 ዓ.ም. ት/ቤት መግባት ያለባቸው ተማዎች በሙሉ ምዝገባ ማጠናቀቅና ወደ ት/ቤት ገብተው የዘመኑን ትምህርት እንዲጀምሩ ማድረግ ..... | |
| | 4.1.8. የዘመኑን ትምህርት ሁሉን ባድርሻ አካላት ባሣተፈ መልኩ በህዝብ ንቅናቄ መጀመር ........................................................................... | |
| | 4.2. የተግባር ምእራፍ ተግባራት አፈፃፀም .................................................. | |
| | 4.2.1. ጠንካራና የማያቋርጥ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ሠራዊቱ የዓመቱን ዕቅድ የሚፈጽምበትን ንቅናቄ መፍጠርና ወደ ተግባር ማስገባት .................. | |
| | 4.2.2. የንቅናቄውን ቀጣይነት ለማጋገጥ የሚያስችሉ የህዝብ ግንኙነት ሥራዎችን በውጤታማነት መፈፀም ................................................. | |
| | 4.2.3.በተግባር ሂደት የሚከሰቱ የኪራይ ሰብሣቢነት ተግባርና ዝንባሌዎችን በመለየት፣ በማጋለጥና በመታገል ልማታዊ ዲሞክራሲየዊ አስተሣሣብ ማስፈን | |
| | 4.2.4. በየደረጃው የሚሰጠውን የአጠቃላይ ትምህርት ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ ................................................................................ | |
| | 4.2.5. የትምህርት ተደራሽነትን፣ ተሣትፎንና ፍትሐዊነትን ማረጋገጥ ......... | |
| | 4.2.6. የትምህርት ፋሲሊቲዎችን /መሠረተ ልማትና ግብአት/ማሟላት ........ | |
| | 4.2.7. በየደረጃው ባለ የትምህርት መዋቅር መልካም አስተዳደርን በማስፈን ልማታዊ አስተሣሠብን ማስረጽ ...................................................... | |
| | 4.3. የማጠቃለያ ምዕራፍ ተግባራት አፈፃፀም .............................................. | |
| | 4.3.1. የዘመኑን እቅድ አፈጻጸም ተቋማዊ በሆነ መንገድ መገምገምና ለአደረጃጀቶችና ፈጻሚዎች ግምገማውን መነሻ ያደረገ ደረጃ መስጠት፣ .......... | |
| | 4.3.2. የዘመኑን የተግባር አፈጻጸም በህዝባዊ ኮንፈረንስና ጉባኤ ማጠቃለል፤ | |
| | 4.3.3. በዘመኑ የታዩ ምርጥ አፈጻጸሞችን መቀመርና ለ 2015 ዕቅድ ዝግጅት ማድረግ፣ | |
| | 4.3.4. የተማሪዎች ውጤት በማጠናከርና በመተንተን ለቀጣይ ለ 2015 ዕቅድ ዝግጁ ማድረግ፣ | |
| 5 | የክትትልና ድጋፍ ስርዓት .................................................................... | |
| 6 | የአፈፃፀም አቅጣጫዎችና ስልቶች ............................................................ | |
| 7 | ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና መፍትሄዎች ................................................ | |


## መግቢያ

አገራችን በልማት ወደፊት እንድትራመድና እንድትበለጽግ ለማድረግ ወሣኙ በትምህርት አማካይነት የታነፀ ሁለንተናዊ ስብእና የተሟላ፣ አምራች፣ ተመራማሪ፣ ንቁና ታታሪ ዜጋ ማፍራት መሆኑ የታመነ ነው፡፡ የትምህርት ዘርፍ የመማር ማስተማር ሥራ ብቃትና ጥራት ባለው ሁኔታ እየተካሄደ አገር አቀፍ የትምህርት ዓላማ ግቡን እንዲመታ ለማድረግ ግንባር ቀደም ሃላፊነትና ሚና የተጣለበት መስሪያ ቤት ነው፡፡

ከዚህ አኳያም በ 2013 በጀት ዓመት ጥራት ያለው ትምህርት ፍትሃዊነቱን በጠበቀ መልኩ ለማስፋፋት ባለድርሻ አካላትን ያሣተፈ ዕቅድ በማዘጋጀት ለተግባራዊነታቸው መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል፡፡ በተለይም በትምህርት ዘመኑ መጀመሪያ በየደረጃው ወደ ትምህርት ቤት መምጣት የሚገባቸውን ህጻናት በእቅድ ተመስርቶና ባለድርሻ አካላትን አሳትፎ ወደ ትምህርት ቤት ለማምጣት ከፍተኛ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡

ከዚያም በመቀጠል የተማሪዎችን የመማር ውጤትና ስነ ምግባር የሚያሻሽሉ በርካታ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን በዚህም አንፀባራቂ ድሎች ተመዝግበዋል። የተማሪዎች ውጤት ትንተና የሚያመለክተው የተማሪዎች አማካይ ውህድ ካለፉት ዓመታት ጋር ሲነፃፀር በሁሉም የትምህርት አይነቶች ከፍተኛ መሻሻሎች የታዩበት ነው። ይህም ሆኖ በአንዳንድ አካባቢዎች በነበረው አለመረጋጋት የተነሣ ውጤቱ በሁሉም አካባቢዎች በተመሣሣይ መልኩ የተፈፀመ አልነበረም።

በ 2013 በጀት ዓመቱ በተለያዩ ጊዜያት ዕቅድ አፈፃፀም ላይ ተመስርቶ በተካሄዱት ግምገማዎች በክልሉ የትምህርት እቅድ አፈጻጸም ያለበት ደረጃና በስርዓቱ ውስጥ ያሉ መሰረታዊ ችግሮችና አነዚህን ችግሮች ለመፍታትም በ 2014 ዓ.ም ርብርብ የሚደረግባቸው ወሳኝ ጉዳዮች ተለይተው ወጥተዋል። በዚህ መሰረት በ 2014 የትምህርት ዘመን የርብርብ ማዕከል የሚሆኑ አራት ወሳኝ ጉዳዮች ተቀምጧል። እነርሱም የትምህርት ጥራትንና ተገቢነትን ማረጋገጥ፣ የትምህርት ተሣትፎና ተደራሽነት ማስፋት፣ መልካም አስተዳደርንና ሠላማዊ መማር ማስተማርን ማስፈን፣ የትምህርት ግብአቶችን በስታንዳርዱ መሠረት ማሟላት ሲሆኑ እነዚህን ወሳኝ ጉዳዮች ለመፈጸምም በበጀት ኣመቱ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል። በመጨረሻም በ 2014 ንቅናቄውን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ይቻል ዘንድ የንቅናቄ ዕቅዱ እንደሚከተለው ቀርቧል።

# 1. የዕቅዱ መነሻ ሁኔታዎች፣

የትምህርት ዘርፍ ዕቅድ ይዘትና ዋና ዋና ግቦች በአግባቡ ለመወሰን በርካታ ጉዳዮችን ከግምት ማስገባት አስፈላጊ በመሆኑ የ 2014 በጀት ዓመት የዕቅድ ዝግጅት መነሻዎች በተሟላ መንገድ ተተንትነው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## 1.1. የትምህርት ስልጠና ረቂቅ ፖሊሲ እና ስትራቴጂዎች እንደመነሻ፤

የትምህርት ስልጠና ፖሊሲና ስትራቴጂ ረጅም ዘመናትን ተሻጋሪ ባህሪ ያላቸው ሲሆኑ ተግባራዊ በማድረግ ሂደትም የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ እና ስትራቴጂዎች ተቀርጸው የትምህርት ተደራሽነት፣ ፍትሐዊነት እንዲሁም ጥራትና አግባብነት ለማረጋገጥ ሰፊ እንቅስቃሴ ተደርጓል። በዚህ እቅድ ዝግጅትም የፖሊሲውንና ስትራቴጂውን መሠረታዊ አቅጣጫዎችን፣ተግባራዊ በማድረግ የሚኖረውን ለውጥ ለዕቅድ ዝግጅቱ መነሻ በማድረግ ታሣቢ ተደርጓል። ስለሆነም ረቂቅ ፖሊሲውንና ስትራተጂውን ለዕቅድ ዝግጅቱ መነሻ አድርጎ መውሰድ በአንድ በኩል በፖሊሲው አማካይነት የመጣውን ለውጥ በአግባቡ ለመመዘንም ሆነ ከዚሁ ጋር አያይዞ ፖሊሲውና ስትራቴጂውን በጥልቀት በመገንዘብ ክፍተቱ በቀጣይ ተሻሽሎ በሚወጣው የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ በማረም ዕቅዱን ለመፈፀም የሚያግዝ ይሆናል።

## 1.2. የ 2013 ዓ.ም የዕቅድ አፈፃፀምን እንደመነሻ፣

የ 2013 ዓ.ም ዕቅድ ሲዘጋጅ መሠረታዊ መነሻዎች ተቀምጠው የነበሩ ግቦችና ግቦቹን ለማሳካት በተደረገው ርብርብ የተገኙ ውጤቶች፣ እቅዱን በመተግበር ሂደት የነበሩ ጥንካሬዎችና ድክመቶች በተለይም ለቀጣዩ ዘመን ዕቅድ ዝግጅት ካላቸው ፋይዳ አንፃር ታይቶ በዝርዝር መገምገምና ውጤቱን ለቀጣይ ዓመት ዕቅድ ዝግጅት በመነሻነት መጠቀም የግድ ይላል።

ስለሆነም የ 2013 ዓ.ም ዕቅድ አፈፃፀም አጠቃላይ ግምገማ በማካሄድ በግምገማው ላይየታዩ የአፈፃፀም ስኬቶች፣ መልካም ተሞክሮዎችና ተግዳሮቶች ከሀገራዊ ራእይ ጋር በማስተሣሰር ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር መግባባት መፍጠር ለመጪው ዓመት መሪ ዕቅድ ዝግጅትም ወሣኝ መነሻ ተደርጎ ተወስዷል።

## 1.3. በትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ የሕዝብ አስተያየቶች እንደመነሻ፣

የህብረተሰቡን አዳዲስ የሕዝብ ፍላጐቶችና አዳዲስ ጥያቄዎችን ለመመለስና ሕዝብን በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ ለማድረግ የፌዴራልና የክልል ደረጃ በትምህርት ስልጠና ፍኖተ- ካርታ የተነሱ ጉዳዮች በመነሻነት መውሰድ አስፈላጊ ነው። በዚህ ረገድ በትምህርት ዘርፍ በአመቱ ውስጥ የህዝቡን ተሳትፎ ባረጋገጠ መንገድ በዕቅድ ሊመለሱ የሚገቡ የልማትና መልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን ከወዲሁ መለየት እና በዕቅድ መመለስ እንዲቻል ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶታል።

## 1.4. በክልልና በፌደራል ደረጃ የተዘጋጀው የአስር ዓመት ዕቅድ እንደመነሻ፤

በአገር ደረጃ የተቀመጠውን የአጭርና የረጅም ጊዜ ራዕዩን ለማሳካት ከፌደራል እስከ ክልል ባሉ የሴክተር አደረጃጀቶች የተናበበ የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ ማዘጋጀት ተገቢ በመሆኑ ከ 2013 ዓ.ም እስከ 2022 ዓ.ም የሚተገበር የረጅም ጊዜ እቅድ ተዘጋጅቷል። ስለዚህም በአመታዊ እቅድ ዝግጅት ወቅት የሴክተሩን እና ክልላዊ የዘርፉን አገራዊ ዕቅድ ከክልል ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር በመቃኘት የመነሻ ዕቅድ

ማድረግ ይገባል። በዚህ ደረጃ ያልተናበበ ዕቅድ ማዘጋጀት በረጅም ጊዜ እንዲሳኩ የተቀመጡ ክልላዊና አገራዊ አጀንዳዎችን ማሳካት ስለማይቻል በዝግጅቱ ሂደት ይህንን ሁኔታ ከግምት ውስጥ እንዲገቡ ተደርገዋል።

## 1.5. የድህረ 2015 ዘላቂ የልማት ግቦች እንደ መነሻ፤

የአስር አመት እቅድ እና የ 2013 በጀት ዓመት ዕቅድ ሲዘጋጅ የዘላቂ የልማት ግቦችን በተለይም ከትምህርት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ግብ አራት (Provide equitable and inclusive quality education and life-long learning opportunities for all) እና ግብ አምስት (Attain gender equality, empower women and girls everywhere) ማሳካት እንደ አንድ መነሻ ተወስዶ ለተፈጻሚነቱ ሰፊ ስራ ሲሰራ ቆይቷል። በዚህም አበረታች ውጤት የተመዘገበ ሲሆን ቀሪዎቹን ለማሳካት ጥረት እየተደረገ ይገኛል ። ከላይ የተጠቀሱ ዘላቂ የልማት ግቦችን ከሀገራችን ፖሊሲ፤ ስትራቴጂና የልማት ቅደም ተከተል ጋር በተጣጣመ መንገድ እንዲሆኑና ሀገራችንም ኃላፊነቷን እንድትወጣ በሚደረግ ጥረት የክልል ድርሻን ከወዲሁ መውሰድ ስለሚገባ በ 2013 ዓ.ም መሪ ዕቅድ ዝግጅት ሂደት ከግምት እንዲገቡ ተደርገዋል።

# 2. የ 2013 ዓ.ም እቅድ አፈፃፀም ግምገማ፣

## 2.1. የዝግጅት ምዕራፍ አፈፃፀም፣

### 2.1.1. የዕቅድ ዝግጅት

የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ ዝግጅት ክልላዊና አገር አቀፍ መነሻዎችን መሠረት በማድረግ ተዘጋጅቷል። በመቀጠልም የ 2013 በጀት ዓመት የትምህርት ዘርፍ መሪ ዕቅድና የዚህ ማስፈፀሚያ ዕቅዶች ከትምህርት ቢሮ እስከ ት/ቤቶች ድረስ ተዘጋጅተዋል። መሪ ዕቅዱን መነሻ በማድረግም የክረምት ስራዎች፣የመልካም አስተዳደር እቅድ እራሱን ችሎ እንዲታቀድ ተደርጓል። በዘመኑ በክልላችን የሚገኙ ሁሉም ዞኖችና ወረዳዎች መሪ ዕቅድ ከማዘጋጀታቸው በተጨማሪ አብዛዎቹ ት/ቤቶች (95.01% የመጀመሪያና 90.73% ሁለተኛ ደረጃ) የት/ቤት መሻሻል ዕቅድ አዘጋጅተዋል። መምህራንና ተማሪዎች በግል፣ በቡድንና በትምህርት ቤት ደረጃ የውጤት ማሻሻል ግብ አስቀምጠው ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተሸጋግረዋል። ከጥራት አኳያም የት/ቤቶችን የግብዓት ችግር የለየና እነዚህ ክፍተቶችን የህዝብ አቅምን በመጠቀም ማሟላት የሚችሉበትን ስልት የጠቀመ፤ ግቦች፣ ተግባራት፣ ውጤቶች እና የአፈጻጸም አቅጣጫዎችን መሰረት አድርጎ ለማዘጋጀት ጥረት በመደረጉ ካለፉት ዓመታት ጋር ሲነፃፀር በጥራትም ሆነ በይዘት መሻሻል የታየበት ነው። በመሆኑም በየደረጃው የሚገኙ

አመራሮችና ፈጻሚዎች የትምህርት ሴክተሩን እቅድ በዝግጅት፣ በትግበራ እና በማጠቃለያ ምእራፍ በመከፋፈል የማቀድ ክህሎት እየተሻሻለ መምጣቱንም ለማየት ተችሏል።

ከእቅድ ዝግጅት አንፃር ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻልና ለውጦች የታዩ ቢሆንም አሁንም ያልተሻገርናቸው ጉደለቶች ታይተዋል። አልፎ አልፎ በትምህርት ቤት ደረጃ የተዘጋጀው እቅዱ በበቂ የሁኔታ ትንተና ላይ ያልተመሰረተ፣ በትምህርት ቤቶች ግለግምገማ እና የኢንስፔክሽን የግብዓት ትንተና ላይ ተመስርቶ የትምህርት ቤቶችን የግብዓት ችግር በክረምት በህዝብ ንቅናቄ ሰርቶ ደረጃቸውን በማሻሻል የተቋማት የገጽታ ግንባታ አሁን ካለበት ችግር እንዲወጣ የሚያደርግ አይደለም። አዳዲስ ትምህርት ቤቶች የ 3 ዓመት ስትራቴጅክ እቅድ በማቀድ ረገድ ሰፊ የእውቀት ችግር ያለባቸው መሆኑ በእቅድ ዝግጅት ወቅት የታዩ ችግሮች ነበሩ።

ስለሆነም በ 2014 በጀት ዓመት የዕቅድ ዝግጅትን አስመልክቶ አዲስ ለሚከፈቱ ት/ቤት አመራሮችን ተገቢው ኦሬንቴሽን መስጠት፣ የከፍተኛው የትምህርት አመራር ለዝቅተኛው አካላት የተዘጋጀውን የ 2014 በጀት ዓመት ዕቅድን በዝርዝር በማየት ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን ድጋፍ የማድረግ ተግባራት ከወዲሁ ትኩረት ተሰጥቷቸው መከናወን ይኖርባቸዋል።

### 2.1.2. ፈፃሚዎችን ማዘጋጀት፣

ፈፃሚን በማዘጋጀት ረገድም በ 2013 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ ከክልል እስከ ት/ቤት ድረስ የወረደ የእቅድ ትውውቅ መካሄዱ፣ በመስከረም ወር 2013 ዓ.ም በተካሄደው የትምህርት ሳምንት ወቅት ከመምህራን፣ ከወላጆችና ከተማሪዎች ጋር በአደጋ ጊዜ ትምህርትን መምራት በተለይም ኮረናን በመከላከል ትምህርትን ማስቀጠል አስመልክቶ የተካሄደው ውይይት ነው።

#### 2.1.2.1. የእቅድ ኦሬንቴሽን መድረክ አፈፃፀም

በየደረጃው በተዘጋጀው ዕቅድ ላይ የጋራ መግባባት በመፍጠር የአመራሩንና የፈጻሚ አካላትን የማስፈጸም ብቃት የማሳደግና በእቅድ አፈጻጸሙ ላይ እምነትና ቁርጠኝነት ከመገንባት አኳያም በክልል ደረጃ የአስር ዓመትና የ 2013 ዓ/ም እቅዶች ላይ ለ 863 (ወንድ 566 ሴት 297) የዞንና የወረዳ አመራሮች እና የቢሮ ሰራተኞች እንዲሁም የህዝብ ክንፍ ተወካዮች የተሳተፉበት እቅድ ኦሪንቴሽን በመስጠት የጋራ መግባባት ላይ መድረስ ተችሏል። በዞን ደረጃም የወረዳ አመራሮችን፣ የዞን አጠቃላይ አመራሮች፣ የህዝብ ክንፍ አመራሮች በተገኙበት ከ 2-3 ቀን ቆይታ ያለው በዕቅድ ላይ ውይይት ተደርጓል። የውይይት ዋና ትኩረትም በ 2012 ዓ/ም ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት በማስፋፋት ረገድ የተገኙ ውጤቶች፣ ያልተፈቱ ተግዳሮቶች እንዲሁም የ 2013 ዓ/ም እቅድ ግቦችና የአፈጻጸም አቅጣጫዎች ላይ ኦሪንቴሽን የተሰጠ ሲሆን በኦሪንቴሽኑም በየደረጃው የሚገኙ አመራሮችና ፈጻሚዎች የበጀት ዓመቱን እቅድ በተሻለ ሁኔታ ለመፈፀም መነሣሣት የፈጠረ መሆኑ በወቅቱ ተገምግሟል።

ከዞን መድረክ በኋላም በወረዳ ደረጃ የተሣታፊዎች ብዛትና ተዋጽኦ ቢለያይም በአብዛኛው ወረዳዎች የቀበሌ፣ የማህበራትና የት/ቤት አመራሮች፣ እንዲሁም ሌሎች ተጽእኖ ፈጣሪ የህብረተሰብ ክፍሎችን ያካተተ መድረክ በመፍጠር የ 2012 ዓ/ም ዕቅድ አፈፃፀምን በዝርዝር በመገምገም በ 2013 ዓ/ም የትምህርት ዘመን ግቦች፣የአፈጻጸም አቅጣጫዎች፣ግነቶዎች እና መፍትሄዎች ላይ ውይይት አድርገዋል። በመድረኮቹ የተሻለ ቁጭትና መነሣሣትን መፍጠርም ተችሏል። ከወረዳ መድረክ በኋላም በቀበሌና በመንደር ደረጃ መድረኮች የተፈጠሩ ሲሆኑ በእነዚህ መድረኮችም ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዩች የት/ቤቶችን ግብአትና መሠረተ ልማት ማሟላት፣እድሚያቸው

ለትምህርት የደረሱ ሁሉንም ህፃናት በአጭር ጊዜ በህዝብ ንቅናቄ ወደ ትምህርት ቤት እንዲገቡ ማድረግ እና የ 2013 ዓ/ም ዋና ዋና ግቦችን ለማሳካት የወላጆች ድርሻ በተመለከተ የሚሉት ናቸው።

### 2.1.2.2. የትምህርት ቫምንት ስልጠና መድረክ አፈፃፀም

በትምህርት ቫምንት ልዩ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ የኮረና ቫይረስን በመከላከል ትምህርት ቤቶች የሚከፈቱበት መመሪያ፣ ፕሮቶኮሎች፣ መግባቢያ ሰነዶች እና ማስፈጸሚያ ስልቶች በማዘጋጀትና ወደ ተግባር መግባት ነበር። በዚህም ላይ በቅድሚያ በክልል ደረጃ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ተሳታፊ የሆኑበት መድረክ ሲሆን በዚህም ት/ቤቶች በሁለት ምዕራፍ የሚከፈትበትን የጊዜ ሰሌዳ እና የመክፈቻ መስፈርቶችን በሚመለከት የጋራ መግባባት ላይ መድረስ ተችሏል። ከዚህ በመቀጠልም በክልሉ በትምህርት ስራው በአጋርነት ከሚንቀሳቀሱ 115 (ወንድ 96 ሴት 19) ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ተወካዩች በተገኙበት በመመሪያው ላይ ውይይት ተደርጓል። በመድረኩም ላይ የኮረና ቫይረስ ስርጭት ወቅት ተማሪዎችን እና ማህበረሰቡን ከበሽታው በመከላከል ትምህርት ለማስቀጠል እንዲቻል መመሪያው ላይ የተመላከቱ ወሳኝ የግብአት፣ የአቅም ግንባታ እና የመሰረተ ልማት ስራዎች ላይ እንዲሳተፉ ጥሪ የተላለፈበት እና የጋራ ስምምነት ላይ የተደረሰበት ነበር።

ሌላው ትኩረት ተሰጥቶት የተከናወነው ተግባር ደግሞ የቀውስ ወቅት አመራርን አስመልክቶ ለ 877 (ወንድ 864 ሴት 13) የዞን፣ የወረዳ፣ የ 2 ኛ ደረጃ ት/ቤት ር/መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ስልጠና መስጠቱ ነው። በዚህ ረገድም በትምህርት ስራው ውስጥ በተከታታይ የገጠሙንን የጎርፍ፣ የአንበጣ መንጋ፣ የኮረና ቫይረስ ወረርሽኝ እና በህወሃት ጥቃት ምክንያት ክልሉ ገጥሞት የነበረውን ፈተና በመቋቋም ትምህርት ስራው እንዴት ይመራል በሚለው ላይ ሰፊ ምክክር ተደርጓል።

በክልል ደረጃ ከተካሄዱ መድረኮች በኋላ እና ጎን ለጎን የቀውስ ወቅት የትምህርት አመራር እና የኮረና ቫይረስን በመከላከል የመማር ማስተማሩን ሥራ ማስጀመር አስመልክቶ በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ ውይይቶች ተካሂደዋል። በመድረኮች ላይም መምህራን፣ ርዕሳነመምህራን፣ ሱፐርቫይዘሮች፣ ተማሪዎች እና የተማሪ ወላጆች ተሳታፊ ሆነዋል። በኮንፈረንሱ የትምህርት በተነሱ ርዕሰ ጉዳዩች ዙሪያ አሁን የተመዘገቡ ውጤቶች፣ የነበሩበት ተግዳሮቶች፣አሁንም ያሉበት ፈተናዎች እና ለቀጣይ ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዮች አስመልክቶ በአብዛኛው መድረኮች ላይ ከሞላ ጎደል የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል።

ምንም እንኳ በዞንና በወረዳ ደረጃ የተፈጠሩ መድረኮች በተነፃፃሪነት ከሞላ ጎደል ውጤታማ ነበሩ ብሎ ማጠቃለል ቢቻልም በት/ቤት ደረጃ የተከናወኑት የወላጆችና የተማሪዎች ኮንፈረንስ ግን አልፎ አልፎ እጥረቶች ተስተውለዋል። እነዚህም በውይይት መድረኮቹ ተሳታፊዎች ተሟልተው ያለመገኘትና የመንጠባጠብ ችግር፣ በተወሰኑ አካባቢዎች ውይይቱን ለመፈጸም የሚያስችሉ ብቁ ዝግጅት ባለመደረጉ ውይይቶችን በአነስተኛ የሰው ሀይል የመፈጸምና ውይይቱም ብስለት የለሌው መሆኑን፣ ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት የአመለካከት ትግል እንዲካሄድበት ያለማድረግ፣ በት/ቤቶች ገጽታ ግንባታ መንግስት ብቻ እንዲፈጽም የመፈለግና የህዝቡን አቅም አሳንሶ የመመልከት ዝንባሌዎች ታይቷል።

### 2.1.3. የትምህርት ግብአት መሟላት፣

የሰው ኃይሉን ከማሟላት አንፃር ትኩረት ተሰጥቶት የተከናወኑት የመምህራንና የት/ቤት አመራሮችን ማሟላት ሲሆኑ በትምህርት ዘመኑ መጀመሪያ ላይ አመራር ለሌላቸው 196 ት/ቤቶችን (የ 142 የመጀመሪያ ደረጃ፣ 54 የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት) ር/መምህራን እና

ለ 49 የጉድኝት ማዕከላት (42 የመጀመሪያ ደረጃና 7 የሁለተኛ ደረጃ) ሱፐርቫይዘሮች ምደባ በማድረግ አመራሮች እንዲሟሉ ተደርጓል፡፡ የመምህራን እጥረት በመፍታት ረገድም በ 2013 ዓ/ም የ 3,224 የመጀመሪያ ደረጃ እና የ 911 የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ቅጥርና ስምሪት ተከናውኗል፡፡ በተጨማሪም 2,937 በጎ ፈቃደኛ የዩኒቨርቲና የኮሌጅ ተማሪዎች በክረምት ወቅት ለ 4,418 የመጀመሪያና 2 ኛ ደረጃ ተማሪዎች የማጠናከሪያ ትምህርት ሰጥተዋል፡፡

ከመሠረተ ልማት አኳያም 59 አዲስ የመጀመሪያ ደረጃ እና 23 አጠቃላይ 2 ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተከፍተዋል፡፡ 782 ነባር የመጀመሪያ ደረጃ እና 141 ሁለተኛ ደረጃ አሣድገዋል፡፡ 2,551 የመጀመሪያ ደረጃና 716 ሁለተኛ ደረጃ መጨናነቅ ባለባቸው አካባቢዎች ተጨማሪ ክፍሎች ተገንብተዋል፡፡ 1,327 የመጀመሪያ ደረጃ እና 39 የ 2 ኛ ደረጃ ት/ቤቶች መማሪያ ክፍሎችን መልሶ መተካት ስራ ተከናውነዋል፡፡ በመሆኑም በ 2012 ዓ/ም አገልግሎት በመስጠት ላይ ከነበሩት የመማሪያ ክፍሎች በተጨማሪ 7,614 (6,164 በመጀመሪያ ደረጃ እና 1,450 በሁለተኛ ደረጃ ) በተጨማሪነት ተከፍተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህ ረገድ በአልማ አስተባባሪነት የተከናወነው ተግባር የበለጠ ማጠናከር ይገባል፡፡

የተማሪዎች መጽሃፍ በበቂ ሁኔታ ለማቅረብ ሰፊ ርብርብ የተደረገ ሲሆን በዘመኑ 1,975,940 (1,137,732 የመጀመሪያ ደረጃ፣ 758,538 2 ኛ ደረጃ፣ 27,295 አዊኚ፣ አርጎብኛ 2,575 እና ህምጣና 49,800) ታትሞ ተሠራጭቷል፡፡ ለዚህም ብር 96,352,688.26 (ለአንደኛ ደረጃ 56,474,472.10 እና ለሁለተኛ ደረጃ 39,878,216.16) ወጭ ሆኖ በስራ ላይ ውሏል፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ስነውበት ከ 1 ኛ-4 ኛ ክፍል፣ ሙዚቃና ስነጥበብ ከ 5 ኛ-6 ኛ ክፍል፣ ሰውነት ማጎልመሻ ከ 5 ኛ-8 ኛ ክፍል የመማሪያና ማስተማሪያ መፃህፍት እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ደግሞ ሰውነት ማጎልመሻ ከ 9 ኛ-12 ኛ ክፍል እና ታሪክ ከ 9 ኛ-12 ኛ ክፍል ውጭ በሌሎች የክፍል ደረጃዎች የተማሪዎች መማሪያ መፃህፍትን በነፍስ ወከፍ ለተማሪዎች እንዲዳረስ የሚያስችል የህትመት ሥራ ተሰርቷል፡፡

የልዩ ልዩ ፈርኒቸር ከማሟላት አንፃርም በዘመኑ በወረዳና በት/ቤት ደረጃ በተመደበ በጀት 4,958 (4037 ለመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች እና 921 ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች) ጥቁር ሠሌዳ እንዲሁም 44620 (27,704 ለመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች እና 16,916 ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች) ኮምባይንዱ ዴስክ አዲስ ተዘጋጅተው ቀርበዋል፡፡ ከዚህ ባሻገር በትምህርት ቢሮው በተመደበ በጀት 5,836 ኮምባይድ ዴስክ ተገዝቶ ተሠራጭቷል፡፡

የፕላዝማ ተከላና ጥገና በተመለከተም በዘመኑ በዞንና በወረዳ ባሉ የ ICT ባለሙያዎች የ 18 ፕላዝማ ተከላ ስራ እና የ 144 ፕላዝማዎች ጥገና ስራ ተከናውኗል፡፡

ለት/ቤቶች የትምህርት ፋይናንስ በማሟላት ረገድም በ 2013 በጀት ዓመት ከፌዴራል ትምህርት ሚኒስቴር ለሁሉም የመንግስት ት/ቤቶች (8,881 የመጀመሪያ እና በ 570 ሁለተኛ ደረጃ) ለሚገኙ ተማሪዎች እና የልዩ ፍላጎት ድጋፍ መስጫ ማዕከላት በድምሩ ብር 292,009,350.00 ተመድቦ ለት/ቤቶች እንዲርሣቸው ተደርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለ 888 ት/ቤቶች የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች 26,640,000 ብር የላቀ አፈፃፀም ላስመዘገቡ ት/ቤቶች እንዲደርሣቸው በማድረግ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ከዚህ ባሻገር በዘመኑ ለ 4,398,021 በመንግሥት ት/ቤቶች ለሚማሩ ተማሪዎች ብር 62,458,278.00 ከወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች ተመድቧል፡፡ ትምህርት ቤቶች የውስጥ ገቢያቸውን በማመንጨት እንዲጠቀሙበት በማድረግ ረገድም በዘመኑ ብር 235,817,138 (61.30%) ሰብስበው ተጠቅመዋል፡፡ በተጨማሪም ከህብረተሰብ ተሣትፎ አንፃርም በ 2013 ዓ/ም ብር 974,650,945

(በጥሬ ገንዘብ ብር 340,411,725፣ በቁሣቁስ ብር 236,349,248 እና በጉልበት ብር 397,889,971) ወይም 62.42% በመሰብሰብ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

ከላይ የተጠቀሱት ሥራዎች እንደተጠበቁ ሆነው በግብአት አቅርቦቱ በኩል የነበሩ ችግሮች በርካታ ናቸው። አብዛኛው ትምህርት ቤቶች የፈራረሱና በርካታ መሠረት ልማት የሌላቸው በመሆናቸው ምክንያት አሁንም ምቹ የመማር ማስተማር ሁኔታ ያልፈጠሩ ትምህርት ቤቶች ቁጥር ብዙ ነው። በየት/ቤቱ ያሉ ኰምፒውተሮች ቁጥር ከተማሪዎች ቁጥር ጋር የማይጣጣም በመሆኑ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ትምህርት አሠጣጡ ላይ ከፍተኛ ጫና ፈጥሯል። የመፅሐፍት አቅርቦት ችግሩ የተፈታ ቢሆንም ስርጭት ላይ ያለው ችግር ሙሉ በሙሉ አልተቀረፈም። ለቤተሙከራ አገልግሎት የሚውሉ የኬሚካል አቅርቦቱ ችግርም አልተፈታም። የትምህርት ፋይናንስ ከማሟላት አንፃር በየዓመቱ ተደማሪ እድገት ቢኖረውም የት/ቤቶች የደረጃ ምደባን በሚፈለገው መልኩ መሻሻል አልቻለም። ከተለያዩ ምንጮች የሚገኙ ሀብቶችን በቁጠባና አዋጭ በሆነ መልኩ አለመጠቀም በተለይ የመማሪያና ማስተማሪያ መጽሀፍት፣ ኬምካሎች፣ ፕላዝማ፣ ኮምፒዩር፣ ወዘተ በቀጣይ ልዩ ትኩረት ማድረግ ይገባል። ስለሆነም ለትምህርት ጥራት መረጋገጥ አንዱ የሆነው የግብአት አቅርቦታችን በበርካታ ችግሮች የተተበተበ በመሆኑ በቀጣዮ ዓመት በአቅርቦቱም ሆነ በአጠቃቀሙ ዙሪያ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መረባረብ ይጠይቀናል።

#### 2.1.4. አሠራርና ደረጃጀቶችን ማጠናከር፣

በበጀት ዓመቱ ከክልል እስከ ት/ቤት ድረስ ባሉት ደረጃዎች አዲስ መደራጀት በሚያስፈልገበት ቦታ በአዲስ የማደራጀት እንዲሁም ቀደም ብሎ በተመሠረተበት ነባሩን የማጠናከርና የአሠራር መሻሻሎች ተፈጥረው ወደ ሥራ ለመግባት የሚያስችል የዝግጅት ሥራዎች በስፋት ተከናውኗል። ከዚህ አንፃር በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ የበላይ አመራር እና የማኔጅመንት ኮሚቴ በአግባቡ ተደራጅተው ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል። ከዚህ ባሻገር የተማሪ ወላጅ ህብረት በክልልና በዞን ደረጃ የማጠናከር ሥራዎች ተከናውነዋል። በተመሣሣይ መልኩም የመምህራን ማህበር ጋር ተቀራርቦ የመሥራት ሁኔታ እንዲጠናከር ተደርጓል።

በበጀት ዓመቱ በመምህራን ጉባኤ አደረጃጀቶችን በአዲስ መልክ የማቋቋምና ነባሩን የማጠናከር ስራ ተሠርቷል። በተጨማሪም ለልዩ ልዩ አደረጃጀት በሁሉም ት/ቤቶች መምህራንና ሠራተኞች ተግባርና ሃላፊነታቸውን እንደ ግል ሆነ ቡድን በግልጽ እንዲረዱ ተደርጓል።

### 2.2. የተግባር ምእራፍ አፈፃፀም፣

በተግባር ምዕራፍ ዋነኛው የርብርብ ማዕከል የትምህርት የልማት ወሣኝ ሥራዎችን በብቃትና በውጤታማነት መፈፀም ሲሆን አፈፃፀማችን እንደሚከተለው ቀርቧል።

#### 2.2.1. በመልካም እሴቶች የታነጹ፤ በሁለንተናዊ ስብዕናቸው ብቁ የሆኑ ዜጎችን ማፍራት፣

በትምህርት ስርዓቱ የሚያልፉ ሁሉም ዜጎች እኩል እድል ማግኘት እንዳለባቸው ከልባቸው የሚያምኑ፣መልካም እሴቶችን፣መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶችንና ህግን የሚከብሩ፣ዴሞክራሲያዊ እሴቶችንና መርሆዎችን የሚገነዘቡ፣ከራሳቸው ይልቅ ለማህበረሰቡ ጥቅም ቅድሚያ የሚሰጡ፣ሃላፊነትን የሚቀበሉና ግዴታቸውን በአግባቡ የሚወጡ፣ በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ዙሪያ ሃላፊነት የሚሰማቸው፣ ለሌሎች ባህሎችና የአኗኗር ዘይቤዎች እውቅናና ክብር የሚሰጡ፣ ለሰላም ቅድሚያ የሚሰጡ ፣ሃገራቸውንና ህዝቡን ከወራሪ ለመጠበቅ ሁልጊዜም ዝግጁ የሆኑ፣ ግብር መክፈል እንደ ውዴታ ግዴታ የሚቀበሉና በአግባቡ በታማኝነት የሚከፍሉ፣ ለቤተሰብ ለጎረቤቶችና ለሚኖሩበት ማህበረሰብ ሃላፊነት የሚሰማቸው ለጓደኞቻቸው እና ታላላቆቻቸው ክብር የሚሰጡ፣ ሃዘኔታና የመርዳት ፍላጎት ያላቸው፣ የሌሎችን

ሃይማኖት የሚያከብሩ፣ በፍትህ የሚያምኑ፣ ታማኝ፣ ሌላውን መጉዳት የማይፈልጉ፣ ሌብነትን የሚጠየፉ፣ የትምህርት ጥቅም የተረዱና ፍቅሩ ያደረባቸው መልካም ዜጎች እንዲሆኑ ይጠበቃል።

በዚህ መሠረት የትምህርት ቤት ህገ-ደንብ የሚተገብሩ ተማሪዎችን ቁጥር በመጨመር በስነምግባራቸው አርአያ የሆኑ ተማሪዎችን ድርሻ ለማሳደግ በታቀደው መሠረት በዘመኑ የ 2 ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የስነምግባር ደንብ በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅቷል። ይህንን ደንብ መሠረት በማድረግ በ 2014 የትምህርት ዘመን በሁሉም ት/ቤቶች ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል።

በበርካታ ት/ቤቶች የስነ ዜጋና ስነ ምግባር ክበቡ የተቋቋመ ሲሆን ሰላማዊ የመማር ማስተማሩን ሂደት በመደገፍ በኩል ጥሩ አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ ነው። በዚህ መሠረት የስነ ዜጋና ስነ ምግባር ክበብ በየ 15 ቀኑ እየተገናኙ የሥነ ዜጋና ሥነ ምግባር ቀን ብሎ በመሰየም በህገመንግስቱ እና በእሴቶች ዙሪያ የጥያቄና መልስ ውድድር በማድርግ ግንዛቤአቸውን እያሻሻሉ ናቸው። ክበቡ የሰላም እሴቶችን ለተማሪዎች በተለያዩ ጊዜያት በማስተማር በኩል እየሰራ ሲሆን በዚህም የተነሣ ተማሪዎች መብታቸውን ለማስከበር እንዲጠይቁ፣ ራሳቸውን ባግባቡ እንዲገልጹ እንዲሁም በቂ የህገመንግስት ዕውቀት እንዲኖራቸው በማድረግ በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል። ከዚህ በተጨማሪ የስነ ምግባር ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች መከታተልና መምከር ተችሏል።

ተማሪዎች በትምህርት ቤትና ከትምህርት ቤት ውጪ በማህበረሰብ አገልግሎት የሚሳተፉበትን ሥርዓት በመዘርጋትና በማጠናከር ረገድም በዘመኑ በስነ ዜጋና ስነ ምግባር ክበብ አማካይነት 3,098 (2,902 የመጀመሪያ ደረጃና 196 2ኛ ደረጃ ) ት/ቤቶች በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች ለህብረተሰቡ የሥነዜጋ እና ሥነ ምግባር ትምህርት መስጠት ችለዋል።

ልዩ ልዩ የተማሪዎችን አደረጃጀቶች በማጠናከር በኩልም የተማሪዎች ፓርላማና የተማሪዎች መማክርት በተቻለ መጠን የሴቶችን ምጥጥን ባረጋገጠ መልኩ በመደራጀት ተጨባጭ ሥራዎች አከናውነዋል። በዘመኑ 2,069 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ዲሞክራሲያዊ የምርጫ ስርዓትን በተከተለ መልኩ የተማሪዎች ፓርላማ ያደራጁና ያቋቋሙ ሲሆን 177 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች መማክርት አደራጅተዋል። ከዚህ ባሻገር ተማሪዎች በየክፍላቸው የወደፊት ራእያቸውን በፍላጎታቸው መሠረት የማውጣትና ለተግባራዊነቱም መረባረብ፣ በየክፍላቸው የሚተዳደሩበትን ደንብ ማዘጋጀትና ተገዥ መሆን ሥራዎች በተሟላ መልኩ ተከናውነዋል። በአጠቃላይ የተማሪዎች ፓርላማ እንዲቋቋም መደረጉ ተማሪዎች ሀላፊነትን እንዲለማመዱና ሰላማዊ የመማር ማስተማሩ ሂደት እንዲጠናከር የማድረግ ስራ በመስራት ረገድ የጎላ አስተዋጽኦ አበርክቷል።

በአጠቃላይ በዘመኑ በተማሪዎችና በመምህራን ዘንድ ከታዩት ለውጦች መካከል ጥቂቶቹ ተማሪዎች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብታቸውን ለማወቅና ለማስከበር መቻላቸው፣ ተማሪዎች የመጠየቅ፣ ችግሮችን በውይይት የመፍታት፣ ለት/ቤታቸው ንብረት የመቆርቆር ስሜት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱ፣ በልዩ ልዩ አካባቢያዊ የልማት ሥራዎች በራስ ተነሳሽነት የመሳተፍ፣ በመምህራንና በተማሪዎች መካከል ያለው ግንኙነት በአውንታዊ መልኩ እየተሻሻለ መምጣቱ፣ በልዩ ልዩ የክበባት እንቅስቃሴ በንቃት የመሳተፍ ባህል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየዳበረ መምጣቱ፣ በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚታዩ ችግሮችን በመፍታት በኩል ለት/ቤቱ አመራር ትልቅ እገዛ በማድረግ፣ በተማሪዎች መካከል የመረዳዳት ባህል እያደገ መምጣቱ፣ ተማሪዎች ላይ ይደርስ የነበረው ጉንተላ ከበፊቱ አንጻር ሲታይ እየቀነሰ መምጣቱ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው።

ይሁን እንጅ እነዚህ ለውጦች ቢታዩም አሁንም የመርሀ ግብሩን ዓላማ ሙሉ ለሙሉ እውን ከማድረግ አንጻር የሚከተሉት ችግሮች አጋጥመዋል። ትምህርቱን ከት/ቤት ግቢ ውጭ በማውጣት እሴቶቹን ወደ ህብረተሰቡ እንዲዘልቁ ማድረግ ላይ ውሱንነት መኖሩ፣ ትምህርቱ

መጭው ትውልድ እውቀትና ክህሎት እንዲሁም ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብና መልካም ስነ ምግባር ያለው እንዲሆን ለማድረግ ያለውን አስተዋጽኦ በውል ተገንዝቦ አለመተግበር፣ ከተግባራዊ እውነታዎች ጋር አስተሳስሮ ትምህርት የመስጠት ብቃት ማነስ፣ መምህራንም ትምህርቱን የእውቀት ብቻ ሳይሆን የአመለካከትና የባህሪ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችላቸውን ሥነ ዘዴ በበቂ ሁኔታ አለመተግበር፣ ተማሪዎች መብታቸውን እንዲከበሩላቸው ከመጠየቅ ባለፈ ግዴታቸውን መወጣት አለመቻል፣ በየደረጃው የሚገኘው አመራርና ባለሙያ ለመርሃ ግብሩ የተሰጠው ትኩረት በየጊዜው እየቀዘቀዘ መመጣቱ ወዘተ ሲሆኑ እነዚህን ችግሮች ፈትቶ ብቁ ዜጋ የማፍራት ተልዕኮን ለማሳካት እንዲቻል በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። ስለሆነም በት/ቤት ክበባት፣ በተማሪዎች አደረጃጀቶች የበለጠ የተጠናከሩ ሥራዎችን ማከናወን ይጠበቃል።

### 2.2.2. የገበያን ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ጥራት ያለው ትምህርት መስጠት፣

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ የተካተቱት (ሀ) ከስርዓተ-ትምህርት ዝግጅት፣ ትግበራና ግምገማ ስራዎች፣ (ለ) ከመምህራን እና ትምህርት አመራር ልማት ስራዎች፣ (ሐ) ከሒሳብና ሳይንስ ትምህርትን ጥራት ማሻሻል እና (መ) የትምህርት ቤት መሻሻል ጋር የተያያዙ ተግባራት ናቸው። ዝርዝር አፈፃፀማቸው እንደሚከተለው ቀርቧል።

#### 2.2.2.1. ስርዓተ ትምህርቱን ከፍላጎት ጋር በማጣጣም መቅረፅና የሥርዓተ ትምህርቱን ተገቢነት መጠበቅ

ለአንድ ሀገር እድገትና ልማት ወሳኙ ትምህርትና ስልጠና ሲሆን ለትምህርትና ስልጠና የታለመለትን ግብ መምታት ዋነኛው መሳሪያ ስርዓተ ትምህርት ነው። በተገቢው መንገድ የታቀደ፣ የተተገበረ፣ የተገመገመና በየወቅቱም እየተፈተሸ የሚስተካከል ስርዓተ ትምህርት ለትምህርት ስርዓተ ውጤታማነት ዋነኛ መሳሪያ ነው። በቀጣይ 10 ዓመት ኢትዮጵያ ልትደርስበት ያሰበችውን የብልጽግና ራዕይ ለማሳካት ስርአተ ትምህርቱ በትምህርቱ ስርዓት አማካኝነት ብቁና በቂ የሰው ሀይል ከማፍራት ረገድ ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ስርዓተ ትምህርቱ የሚጠበቅበትን ቁልፍ ሚና እንዲጫወት ግብረ ገብነትን፣ ሀገር በቀል እውቀቶችን፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂን፣ የ 21 ኛው ክፍለ ዘመን ክህሎቶችን እንደዚሁም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናን ማካተት ይጠበቅበታል። እነዚህንም በማካተት በሀገር ደረጃ የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት የሚደረገውን ጥረት በከፍተኛ ደረጃ ያግዛል። ከስርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ትግበራ አኳያ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

በ 2013 የትምህርት ዘመን መጀመሪያ ላይ በኮቪድ-19 ምክንያት ሳይጠናቀቅ የተቋረጠውን የ 2012 ዓ.ም ትምህርት ለማካካስ የሚያስችል መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ ከማድረግ አኳያም በ 33 (15 የመጀመሪያ ደረጃና 18 ሁለተኛ ደረጃ) የትምህርት አይነቶች ላይ መሠረታዊ ይዘቶች ተመርኩዞ የተጨመቀ መነሻ መለማመጃ ጥያቄዎች/ወርክ ሽቶች ተዘጋጅተው ጥቅም ላይ ውለዋል። በመቀጠልም የ 2013 የትምህርት ዘመኑን ይዘት በየክፍል ደረጃው ለመሸፈን እንዲቻል በፌደራል ደረጃ የተሰራውን የይዘት ማጣጣም ስራ በማከናወን በት/ቤቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ ተደርጓል።

በኮቪድ-19 ምክንያት ሳይጠናቀቅ የተቋረጠውን የ 2012 ዓ.ም ትምህርት በ 2013 ዓ.ም የትምህርት ዘመን መጀመሪያ ላይ ለማካካስ የሚያስችል እንቅስቃሴ ከማድረግ አኳያም በ 33 (15 የመጀመሪያ ደረጃና 18 ሁለተኛ ደረጃ) የትምህርት አይነቶች ላይ መሠረታዊ ይዘቶች ተመርኩዞ የተጨመቀ መነሻ መለማመጃ ጥያቄዎች/ወርክ ሽቶች ተዘጋጅተው ጥቅም ላይ ውለዋል። በመቀጠልም የ 2013 የትምህርት ዘመኑን ይዘት በየክፍል ደረጃው ለመሸፈን እንዲቻል በፌደራል ደረጃ የተሰራውን የይዘት ማጣጣም ስራ በማከናወን በት/ቤቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪ በቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም በተመለከተ በኮቪድ 19 ምክንያት

ህጻናት ወደ ት/ቤት ሣይመጡ በቤት ውስጥ በአሳዳጊዎች ወይም አመቻቾች ወይም ወላጆች ድጋፍ ህጻናት ሊማሩበት የሚችሉት ሞጁል ተዘጋጅቶ በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

ሌላው ስርዓተ ትምህርቱን ከማበልፀግ ጋር ተያይዞ የተከናወነው ተግባር ልዩ ልዩ አዳዲስ የመማሪያ፣ ማስተማሪያና ማጣቀሻ መጽሀፍትን ማዘጋጀት ነበር። በዚህ መሠረት በመደበኛው መርሃ ግብር ከ 1 ኛ- 3 ኛ ክፍል የሚሰጡትን አማርኛ፣ እንግሊዝኛ፣ ሂሳብና አካባቢ ሳይንስ አይነቶች ከ 9 ኝ ዓመት በላይ ለሆናቸው ሕጻናት በ 10 ወር በማስተማር ወደ 4 ኛ ክፍል እንዲዛወሩ የሚያስችል  የተፋጠነ የትምህርት ፕሮግራም መርሃ ትምህርት፣ ጠመማሪያና ጠማስተማሪያ መጽሀፍ ተዘጋጅቶ በተወሰኑ አካባቢዎች በሥራ ላይ ውሏል። ከዚህ በተጨማሪ የኦ ክፍል ተማሪዎች ከልጅነታቸው ጀምሮ እጃቸውንና ፊታቸውን በሳሙናና ውሃ በመታጠብ ትራኮማን መከላከል እንዲችሉ የሚያግዝ አጋዥ ጽሁፍ ተዘጋጅቷል። ቀደም ባሉት ዓመታት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እየተደረገ  ያለው የቅድመ መደበኛ ደረጃ 1-3 ድረስ ያለው ማስተማሪያ መጽሀፍት በአውደ ጥናት ግምገማ በማድረግ እንዲሻሻል ተደርጓል።

ሌላው ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት የተከናወነው ተግባር በአዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፍኖተ ካርታ ጥናት ምክረ ሃሣብ መሠረት በማድረግ አዲስ የመማሪያና ማስተማሪያ መጽሀፍት ማዘጋጀት ነበር።  ከዚህ አኳያም በ 2013 ዓ/ም በክልል ደረጃ ከቅድመ አንደኛ ደረጃ ጀምሮ እስከ 8 ኛ ክፍል የስርዓተ-ትምህርት ዝግጅቱን ለመጀመር ተዘጋጅቶ የሚላከውን የይዘት ፍሰት (Content Flow Chart)፣ ዝቅተኛ የብቃት መለኪያ እና መርሀ ስርዓተ-ትምህርት (Syllabus) ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የማስማማት ስራ ተከናውናል። በመቀጠልም የስርዓት ትምህርት ዝግጅት ጽ/ቤት በማደራጀትና ጽ/ቤቱም ከትምህርት ቢሮውና ከአማራ ምሁራን መማክርት አስተባባሪነት ነባር የመጽሀፍት አዘጋጂዎችን በመጠቀም ከ 1 ኛ-6 ኛ ክፍል በስምንት የትምህርት አይነቶች እና ከ 7 ኛ-8 ኛ ክፍል በአስራ አንድ የትምህርት አይነቶች የመማሪያና ማስተማያ መጽሀፍት እንዲዘጋጁ ተደርገዋል። በሚቀጥለው 2014 የትምህርት ዘመን በሁሉም የክፍል ደረጃዎች በየወረዳው በተመረጡ ናሙና ት/ቤቶች የሙከራ ስራ የሚካሄድ ይሆናል።

ስለሆነም በየደረጃው የሚገኙ አካላት ለሙከራ ትግበራ ስራው በቂ ዝግጅት እና ልዩ ትኩረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። አዲሱ ስርዓተ ትምህርት የሙከራ ትግበራ የሚደረግባቸውን አንድ ት/ቤት በየወረዳው መምረጥ፣ ፕሮራሙን በአግባቡ መስጠት የሚችሉ መምህራንን መልምሎ መመደብ፣ ለመምህራን በቂ የማስተዋወቂያ ስልጠናዎች መስጠት፣ የመማሪያና ማስተማሪያ መጽሀፍት በክልል ትምህርት ቢሮው በሚላኩበት ጊዜ ት/ቤቶች እንዲደርሱ ማድረግ፣ የመማር ማስተማር ተግባሩን በየጊዜው ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ መልስ አዘጋጅቶ ለበላይ አካል ማሣወቅ ይገባል። ከዚህ ጎን ለጎንም በ 1 ኛና 12 ኛ ክፍል የሚሰጡ የትምህርት አይነቶች ሁሉም ተማሪዎች በጋራ የሚወስዷቸው እና ልዩ ኮርሶች በማባል የሚከፈሉ መሆኑን ከወዲሁ ግንዛቤ በመያዝ በምን መልኩ እንደሚፈፀሙ በየደረጃው ከወዲሁ በቂ ዝግጅት ማድረግ ይገባል።

ሌላው ከመማሪያና ማስተማሪያ መጽሀፍት ጋር ተያይዞ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባው ቁልፍ ጉዳይ የሙከራ ትግበራ ከሚካሄድባቸው ት/ቤት ውጭ ባሉ ት/ቤቶች በነባሩ ስርዓተ ትምህርት መጽሀፍት የሚማሩ በመሆናቸው በ 2014 በጀት ዓመት የነባር መጽሀፍት ዳግም ህትመት አይኖርም። በመሆኑም በክዘና ማዕከላት እና በወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች ተከዝነው የሚገኙ መጽሀፍት ካሉ ፍተሻ በማድረግ በአስቸኳይ ወደ ት/ቤት እንዲሠራጩ ከማድረግ ጎን ለጎን ነባሩን መጽሀፍት ከዞን ዞን፣ ከወረዳ ወረዳ፣ በወረዳው ውስጥ በሚገኙ ት/ቤቶች ሽግሽን በማድረግ የመጽሀፍ እጥረትን ለመቅረፍ ከወዲሁ በቂ ጥናትና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ይጠበቃል።  ከዚሁ ጋር አያይዞ መጽሀፍት ተማሪዎች ተማሪዎች እጅ ከደረሱም በኋላ ቢሆን ተማሪዎች በየቀኑ መጽሀፍቱን ት/ቤት ይዘው በመምጣት የማይጠቀሙበት ሁኔታ መኖሩን በተለያዩ ጊዚያት በተደረገ የመስክ ምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል። ስለዚህ በቀጣይ የመማሪያና ማስተማሪያ መጽሀፍት አጠቃቀምን ለማሻሻል

በተለይ ተማሪዎች ተየቀኑ የሚጠቀሙባቸውፀ ማለትም የሣይንስና ሂሣብ እንዲሁም የቋንቋ መጽሀፍትን ክፍል ይዘው በመምጣት መጠቀም እንዲችሉ የት/ቤት አመራሮችና መምህራን ለተማሪዎችና ለወላጆች ግንዛቤ የማስጨበጥ በመስራት አጠቃቀሙን ማሻሻል ይጠበቃል፡፡

## 2.2.2.2. የመምህራን እና ትምህርት አመራር ልማት ስራዎች

የመምህራንና ትምህርት አመራር ልማት ዋና ትኩረት የሚፈለገውን አካዳሚያዊ እውቀት፣ በቂና ተገቢ ሙያዊ ሥነ ምግባርና ክህሎት እንዲሁም የመልካም ዜጋ አመለካከትን ያዳበሩ መምህራንንና የትምህርት ባለሙያዎችን ማፍራት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ በአመራር ልማትና በመምህራን ልማት ያለው አፈፃፀም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሀ) የት/ቤት አመራር ልማት ሥራዎች አፈፃፀም

ከት/ቤት አመራር ልማት አኳያ ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዩች ሁሉም ት/ቤቶች አመራር እንዲኖራቸው ማድረግ፣ በየደረጃው ያሉ ት/ቤቶች ለደረጃው ብቁ የሆኑ የት/ቤት አመራር እንዲኖራቸው ማድረግ፣ የሴት አመራሮችን ድርሻ ማሣደግ፣ የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎችን በመስጠት የአመራሮችን የመፈፀም አቅም ማሣደግ የሚሉት ሲሆኑ ዝርዝር አፈፃፀማቸው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የት/ቤት አመራሮች በተለይም ር/መምህራንና የጉድኝት ሱፐርቫይዘሮች በሀገራችን የተጀመረውን ለውጥ በማስቀጠል፣ የአካባቢያቸውን ብሎም የሀገሪቱን ሰላም በማረጋገጥ እና የትምህርት ጥራትን በማስጠበቅ ረገድ የላቀ ሚና እንዳላቸው ይታመናል፡፡ ከዚህ አኳያም ሁሉም ት/ቤቶች ቋሚ አመራር እንዲኖራቸው ለማድረግ ታቅዶ በ 2013 የትምህርት ዘመን በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተቋማት መካከል ቋሚ ር/መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ያላቸው እንደቅደምተከተላቸው 9,036 (99.48%) እና 2,234 (98.15%) ናቸው፡፡ እንዲሁም ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች አኳያም 582 (98.76%) ት/ቤቶችና 200 (94.79%) ጉድኝት ማዕከላት ቋሚ አመራር አላቸው፡፡

ለትምህርት ጥራት መሻሻል ቁልፍ ከሆኑት ጉዳዮች አንዱ እና ዋናው ትምህርት ቤቶች ለደረጃው በሰለጠኑ የትምህርት ቤት አመራሮች እንዲመሩ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አኳያም የት/ቤቶች አመራሮችን በክረምት ተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም አማካይነት የትምህርት ደረጃቸውን የማሣደግ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ዝግጅት ያላቸው ር/መምህራን ----(63.30%) እና የጉድኝት ሱፐርቫይዘሮች ------------(94.50%) ማድረስ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ለደረጃው የሚፈለገውን የትምህርት ዝግጅት ያላቸው ር/መምህራን -- (5310%) እና የሱፐርቫይዘሮች ----- (86.70%) ለማድረስ ተችሏል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ከጠቅላላ ር/መምህራን መካከል የሴት ድርሻ በ 2012 ዓ.ም 6.52% የነበረ ሲሆን ይህም በዘመኑ 6.48% ደርሷል፡፡ እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ 2012 ዓ.ም ከነበረበት 1.38% ብዙም መሻሻል ሣያሣይ በዘመኑ 1.39% ሆኗል፡፡

የት/ቤት አመራሮችን አቅም አጫጭር ስልጠና በመስጠት የመፈፀም አቅማቸውን ለማጎልበት በታቀደው መሠረት በዘመኑ ለ 166 (110 ር/መምህራንና 56 ሱፐርቫይዘሮች የኦ ክፍል ኮቺንግ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ከዚህ ባሻገር ለት/ቤት አመራሮች የሚሰጠው አጫጭር የሙያ ማጎልበቻ ስልጠና እንደተጠበቀ ሆኖ በሁሉም ት/ቤቶች የሚገኙት አብዛኛዎቹ ር/መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የራሳቸውን የተሙማ ፍላጐት በመለዬት የት/ቤት የተሙማ እቅድ፣ የግለሰብ የተሙማ እቅድ እና ሞጁል በማዘጋጀት ተሣታፊ ሆነዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩት አፈፃፀሞች ቢኖሩም ጥቂት ት/ቤቶችና የጉድኝት ማዕከላት አመራር የላቸውም፡፡ የሴት የት/ቤት አመራሮችን ድርሻ ከማሣደግ አኳያም በ 2013 ዓ/ም የተመዘገበው አፈፃፀም ብዙም ለውጥ የሌለውና በሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ አይደለም፡፡ የት/ቤት አመራሮች የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብርን ለመተግበር ያላቸው ተነሣሽነት ነው፡፡ ስለሆነም እነዚህን ችግሮች በቀጣይ ዓመት ልዩ ትኩረት በመስጠት መፍታት ይገባል፡፡

### ለ) የመምህራን ልማት ሥራዎች አፈፃፀም

የመምህራን ልማት መርሀ ግብር የሚፈለገውን አካዳሚያዊ እውቀት፣ በቂና ተገቢ ሙያዊ ሥነ ምግባርና ክህሎት እንዲሁም የመልካም ዜጋ አመለካከትን ያዳበሩ መምህራንንና የትምህርት ባለሙያዎችን የማፍራት ተልዕኮ ያለው ነው፡፡ ከዚህ በመነሣት በዘመኑ የመምህራን ሙያ በብቃትና በፍላጎት የሚገባበት ሙያ ማድረግ፣ ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ዝግጅት ያላቸው መምህራን ድርሻ ማሣደግ፣ የመምህራን አካዳሚያዊ እውቀትና የሙያ ክህሎት ማሣደግ የሚሉት ታቅደው የተከናወኑ ሲሆኑ ዝርዝር አፈፃፀማቸው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የመምህርነት ሙያ ተመራጭ የሙያ መስክ ከማድረግ አኳያም መምህራን በስራቸው/ በሙያቸው ያላቸው እርካታ ማሣደግ፣ ወላጆች በመምህርነት ሙያ ላይ ያላቸው አወንታዊ ግንዛቤ ማሣደግ እና የመምህራን ስራ መልቀቅ ምጣኔ ከ 4.5% እንዳይበልጥ ማድረግ የሚሉ ታቅደው ልዩ ልዩ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በዚህ መሠረት በቴሌቪዥንና በሬዲዮ የመምህርነት ሙያን ምንነት አስመልክቶ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ተከናውኗል፡፡ በእውቀታቸውና በትምህርት ደረጃቸው የተሻሉ ዕጩ መምህራን ወደ መምህርነት ሙያ በማስገባት በኩልም 12 ኛ ክፍልን ያጠናቀቁ ብቻ ለዲፕሎማ መምህርነት እንዲመለመሉ ተደርጓል፡፡ የመምህራን ምስጋና እና እውቅና አሰጣጥ ዙሪያ በተመለከተ በወረዳ እና ት/ቤት ደረጃ በየዓመቱ ሰኔ 22 ቀን በየደረጃው በሚገኙ የትምህርት ተቋማት የመምህራንን ቀን የሚከበር ሲሆን በዚህም ላይ አንጋፋ መምህራን እና ውጤታማና ታታሪ ሽልማት ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከዚህ ባሻገር መምህራንም ሆነ የትምህርት ቤት አመራሮች የሚያነሷቸው የጥቅማጥቅም ጥያቄዎች ለመፍታት ከቢሮውና ከመምህራን ማህበር የተወጣጣ ግብረ ኃይል በማቋቋም በአሠራር ክፍተት የሚታዩ የተዥጎረጎሩ አሠራሮችን ሙሉ በሙሉ እንዲፈቱ ጥረት ተደርገዋል፡፡ እንዲሁም የመምህራን ዝውውር አሣታፊነት ባለው አኳኋን ከመፈፀም በተጨማሪ የደረጃ እድገት ጥያቄዎችን እንዲፈቱ የማድረግ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ በመሆኑም የመምህራን የስራ መልቀቅ ምጣኔ ሲታይ በዘመኑ በማስተማር ላይ ካሉት መምህራን መካከል ስራቸውን በተለያዩ ምክንያቶች የለቀቁት በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት 1,836 (ወንድ 1,152፣ ሴት 684) ወይም 1.3% ( ወንድ 1.5%፣ ሴት 1.0%) መምህራን እና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 654 (ወንድ 484፣ ሴት 170) ወይም 1.6% (ወንድ 1.6%፣ ሴት 1.6%) መምህራን ናቸው፡፡ በዘመኑ የታየው የመምህራን መልቀቅ ምጣኔ በዓመቱ ከታቀደው አኳያም ሆነ በ 2012 የትምህርት ዘመን በተመሣሣይ ወቅት ከነበረው ጋር ሲነፃፀር በእጅጉ መሻሻል የታየበት ነው፡፡

ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ዝግጅት ያላቸውን መምህራን በማሟላት በኩልም በቅድመ ስራ እና ስራ ላይ ስልጠና አማካይነት መምህራን በስፋት እንዲሰለጥኑ በመደረጉ የተነሣ በዘመኑ ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ዝግጅት ያላቸው መምህራን በቅድመ መደበኛ ተቋማት 3,913 (35.30%)፣ በልዩ ፍላጎት 173 (9.90%)፣ በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት 10,345 (7.10%)፣ በ 2 ኛ ደረጃ ት/ቤት 4,137 (11.20%) ደርሷል፡፡

የመምህርነት ሙያ ሁሌም ማንበብንና መማርን የሚጠይቅ ሙያ በመሆኑ በቅድመ ስራ ስልጠና በተገኘ እውቀትና ክህሎት ማስተማር እንደማይቻል ግልጽ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር መምህራን በስራ ላይ እያሉ እውቀታቸውንና የሙያ ክህሎታቸውን የሚያዳብሩበት ስልጠዎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ አጫጭር የሙያ ማጎልበቻ ስልጠና ከመስጠት አኳያም ለ 551 የአ ክፍል መምህራን የማስተማር ስነ ዘዴ ስልጠና፣ ለ--- መምህራን በተከታታይ የክፍል ውስጥ ምዘና የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ በሣይንስ ቤተ ሙከራ አጠቃቀም ዙሪያ በተግባር

የተደገፈ ስልጠናና የልምድ ልውውጥ ተደርጓል፡፡ ት/ቤት ተኮር የሆኑ የአቅም ማጎልበቻ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ በማድረግ ረገድም በክልላችን በሚገኙ ት/ቤቶች ከሞላ ጎደል ሁሉም መምህራን የተከታታይ ሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብር ተከታትለዋል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት መልካም አፈፃፀሞች እንደተጠበቁ ሆነው ለሀገር እድገት ወሳኝ የሆነውን የተማረ የሰው ሀይል የሚፈጥርና የተከበረ ሙያ የተሰጠው ክብርና ቦታ እየቀነሰ ከመምጣቱም በላይ ወደ ሙያው የሚገቡትም ሙያው የሚጠይቀውን ችሎታ፣ ብቃትና ተነሳሽነት እየቀነሰ ሊመጣ ችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ህብረተሰቡ ለሙያው ያለው አመለካከትና የሚሰጠው ክብርም እንደዚሁም ለመምህራን የተዘረጉ የማትግያ ስርአቶች በአግባቡ ባለመተግበራቸውና በቂ ባለመሆናቸው የተነሳ ሙያው ተመራጭ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ የሆነው ሆኖ ይህንን ሁኔታ በመቀየር መምህርነት የሚመረጥና ፈልገው የሚገቡበት እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ሌላው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ በመምህራን ዘንድ የማስተማር ክህሎት ክፍተቶች በስፋት ያሉ በመሆኑ በቀጣይ የተጠናከረ የአቅም ማጎልበቻ ስልጠና መስጠት ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ በየደረጃው የሚሰጠው አጫጭር የሙያ ማጎልበቻ ስልጠና እንደተጠበቀ ሆኖ የመምህራን ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና መርሃ ግብር ከውሸት ሪፖርት በማለቀቅ መሠረታዊ ለውጥ በሚያመጣ መልኩ መቃኘትና ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡

## 2.2.2.3. የሒሳብና ሳይንስ ትምህርትን ጥራት ማሻሻል

በዚህ ረገድ የሂሳብና ሳይንስ ትምህርቶችን የመማር ማስተማር ሂደት በቴክኖሎጂ በማስደገፍ የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል በየደረጃው የቴክኖሎጂ፣ ምህድስና፣ የስነጥበብና ሂሳብ ትምህርት (STEAM) ፕሮግራም ላብራቶሪ የተሟላላቸው የትምህርት ተቋማት ድርሻን ከፍ ማድረግ እና በክልል ደረጃ በፈጠራ ስራ እውቅና የተሰጣቸው መምህራንና ተማሪዎች ማሳደግ ስራዎችን በሚመለከት ትኩረት ተደርጎ በርካታ ተግባራት ተፈጽመዋል፡፡

በክልላችን ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትቤቶች መካከል 310 (50.6%) ሶስት ቤተ ሙከራ ክፍል ፣ 197 (32%) ሁለት ቤተሙከራ ክፍል ፣ 75 (12.2%) አንድ ቤተሙከራ ክፍል ሲኖራቸዉ 31 (5.1%) ት/ቤቶች ምንም ቤተሙከራ ክፍል የላቸዉም፡፡ በእነዚህ ፋሲሊቲዎች ከ 613 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በተግባር የተደገፈ ትምህርት እየሰጡ ያሉት 308 (50.2%) ሲሆኑ ሌሎች ትምህርት ቤቶች በኮቪድ-19 ምክንያት በተግባር የተደገፈ ትምህርት የማይሰጡ ናቸው፡፡ በዘመኑ 79 የባዮሎጅ እና 129 የኬሚስትሪ አይነት ኬሚካሎችን ርክክብና ስርጭት ተፈጽሟል፡፡

በዘመኑ በክልላችን ካሉት 6349 የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች ውስጥ 4058 (63.9%) ሁለገብ የቤተ ሙከራ ክፍል አላቸው፡፡ በተግባር የተደገፈ ትምህርት እየሰጡ ያሉት 2348 (37%) ሲሆኑ ሌሎች ትምህርት ቤቶች በኮቪድ-19 ምክንያት በተግባር የተደገፈ ትምህርት የማይሰጡ ናቸው፡፡ በክልላችን በዘመኑ ካሉት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል 4452 (48.9%) የሳይንስ ኪት አላቸው፡፡ በመሆኑም የኬምካልና በ 2 ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ኬሚካል፣ አፓራተስና ኢኩፐመንት እንዲሟሉ በመደረጉ መምህራንና ተማሪዎች በቤተሙከራዎች የመሳተፍ እንቅስቃሴያቸው እና የፈጠራ ሥራዎችን እንዲሰሩና ሥራዎቻቸውን በኢግዚቢሽን ለት/ቤቱ ማህበረሰብና ለአካባቢው ህብረተሰቡ እንዲያቀርቡ አስችሏል፡፡

የተማሪዎች የፈጠራ ስራን ለማበረታታት የሚያስችል የአሰራር ስርአት ለመፍጠርና ተግባራዊ ለማድረግ የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ፣ የምህንድስና፣ የስነጥበብ እና የሂሳብ አወደርዕይ (የፈጠራ ስራዎች) ማወዳደሪያ ረቂቅ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡ የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ክበብን በማደራጀት የተማሪዎችን የምርምርና ፈጠራ ስራን ለማበረታታት ከ 363 የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መካከል 153 (42.1%) ት/ቤቶች ክበቡን ያደራጁ ሲሆን በዚህም የተማሪ አባላት ብዛት ወንድ 2836 (54.2%) ፣ሴት 2338 (44.6%) ድምር 5234 ሲሆኑ ከ 5341

የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች መካከል 1327 (24.8%) ት/ቤቶች ክበቡን ያደራጁ ሲሆን በዚህም የተማሪ አባላት ብዛት ወንድ 14598 (55.8%) ፣ ሴት 11556 (44.2%) ድምር 26159 ተማሪዎች ተመዝግበው ተግባራዊ እንቅስቃሴ እያደረጉ ይገኛሉ።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት አፈፃፀሞች እንደተጠበቁ ሆነው የሳይንስና የቴክኖሎጂ ትምህርቶችን ለማጠናከር አዲስ የተዘጋጀውን ስርዓተ ትምህርት በመመርኮዝ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ምህንድስና ትምህርት በይዘትም ሆነ በክፍል ውስጥ አተገባበር ተገቢውን ትኩረት በመስጠት የተማሪዎችን ፍላጎት የማነሣሣት ሥራዎችን ማከናወን፣ እንዲሁም የመምህራንም አሰለጣጠን ቢሆን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን ይጠበቃል። ከዚህ በተጨማሪም ኬሚካል፣ አፓራተስና ኢኩፕመንት የሌላቸውን ት/ቤቶች ዝርዝር ጥናት በማድረግ የማሟላት ሥራዎችን ማከናወን እንደተጠበቀ ሆኖ መወገድ የሚባቸው ኬሚካሎች የሚወገዱበትንና ቤተ ሙከራዎች በተሟላ ሁኔታ ተገቢ አገልግሎት የሚሰጡበትን ስልት ነድፎ በትኩረት መሥራት ይጠይቃል።

## 2.2.2.4. የትምህርት ቤት መሻሻል

የትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ ግብር የትምህርት ግብአቶችንና የመማር ማስተማር ሂደቱን ቀጣይነት ባለው ሂደት በማሻሻል የሁሉንም ተማሪዎች ውጤትና ስነምግባር ማሻሻል ላይ ያተኮረ ነው። ከዚህ አኳያ በዘመኑ የሚጠበቁ ውጤቶች በትምህርት ቤት መሻሻል የግለ ግምገማ የደረጃ ምደባ መስፈርት መሰረት የት/ቤቶችን ደረጃ ሽግግር ማሣደግ፣ የወላጅ ት/ቤት ግንኙትን ማጠናከር፣ ት/ቤቶችን ለመማር ማስተማር ምቹ ማድረግ የሚሉት ነበሩ።

በትምህርት ቤት መሻሻል የግለ ግምገማ የደረጃ ምደባ መስፈርት መሰረት የት/ቤቶችን ደረጃ ከማሣደግ አኳያም ታቅደው የተከናወኑ ተግባራት መካከል ዋቂቶቹ በመጀመሪያ ዙር የኢንስፔክሽን ውጤት በደረጃ አንድ ላይ የሚገኙ ት/ቤቶች በየስታንዳርዱ ውጤታቸውን በመተንተንና ለትምህርት ቤት መሻሻል ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ ስታንዳርዶችን በመለየት “ልዩ ስትራቴጂ” ሰነድ ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ፣ እጅግ የከፋ ችግር ያለባቸውን እና አፋጣኝ ምላሽ የሚሹትን ት/ቤቶች በመለየት በአልማ አስተባባሪነት ህብረተሰቡን በማነቃነቅ መፍታት፣ ት/ቤት ተኮር ተግባራትን መፈፀም የሚሉት ይገኙበታል። ከሁሉም በላይ ደግሞ በአማራ አቀፍ ልማት ማህበር አማካይነት ደረጃቸውን ያሟሉ ት//ቤቶች ድርሻ ከ 16 በመቶ ወደ 50 በመቶ በሦስት ዓመት (2012- 2014) ውስጥ ለማሳደግ ስትራቴጂያዊ የለውጥ ዕቅድ ተዘጋጅቶና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ልዩ ልዩ ባለድርሻ አካላት ኦረንቴሽን በመስጠት ወደ ትግበራ የተገባ ሲሆን ይህንንም የማጠናከር ስራ በቀጣይ ጊዚያት ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል።

የወላጅ ት/ቤት ግንኙነት ከማጠናከር አኳያም 15 አባላት ያሉት ክልላዊ የተማሪ ወላጅ ማህበር ምክር ቤትና ሁሉም ዞኖች የተወከሉበት የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንዲዋቀር የተደረገ ሲሆን በተመሳሳይ ሁሉም ዞኖች፣ ወረዳዎችና ት/ቤቶች አደረጃጀቱን እንዲዘረጉ የአሰራር ስርዓት ተፈጥሮ ወደ ስራ ተገብቷል። በክልላችን በአማካይ በ 45.34% የመጀመሪያና 33.39% ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ወላጆች በየወሩ በወተመህ አማካኝነት በክፍል ደረጃ ውይይት ተደርጓል። እንዲሁም በአማካይ 45.45% የመጀመሪያ ደረጃ እና 43.84% የ 2 ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በየሁለት ወሩ በት/ቤት ደረጃ በተማሪዎች ውጤትና ስነ ምግባር መሻሻል ላይ እንዲመክሩ ተደርጓል።

በአጠቃላይ ጠንካራ የወላጅ ት/ቤት ግንኙነት ባለባቸው አካባቢዎች የተማሪዎች የማርፈድና ማሳለስ መጠን መቀነሱ፣ የህብረተሰብ ተሳትፎ መጨመሩ፣የተማሪዎች ስነ ምግባር መሻሻሉ፣ የወላጅ ት/ቤት መደጋገፍ ተነሳሽነት መጨመሩ፣ የህብረተሰብ ተሳትፎ ግብዓትን የማሟላት

ሂደት መጨመሩ፤ የተማሪዎች ስነምግባር መሻሻል አሳይቷል፣ በቤተመጻሐፍት የማንበብ ባህል ጎልብቷል፣ የተማሪዎች አለባበስ ተስተካክሏል። በመምህራንና በተማሪዎች መካከል ያለዉ ተግባቦት መሻሻል እያሳየ መጥቷል።

ሌላው ከት/ቤት ህብረተሰብ ግንኙት አኳያ የተከናወነው ተግባር ህብረተሰቡ ለት/ቤቶች የሚያደርገው ድጋፍ ሲሆን በ2013 ዓ/ም በህብረተሰብ ተሣትፎ አማካይነት ብር 1,561,404,122 ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 974,650,945 (በጥሬ ገንዘብ ብር 340,411,725፣ በቁሣቁስ ብር 236,349,248 እና በጉልበት ብር 397,889,971) አስተዋጽኦ አበርክቷል። ስለሆነም የህብረተሰብ ተሣትፎ ዕቅድ አፈፃፀም 62.42% ይሆናል። የአካባቢው ህብረተሰብና ወላጆች የትምህርት ሴክተሩን በስፋት የደገፉ ሲሆን ዋና ዋና የተሣትፎ መስኮችም በገንዘብ መዋጮ በማሰባሰብ የታቀዱ ስራዎችን በክትትል ማሰራት፣ የአካባቢ ጥሬ ዕቃዎችን ማቅረብ፣ የግንባታ ቁሣቁሶችን ማጓጓዝ፣ አጥር በማጠር፣ የትምህርት ቤት አስተዳደርን በማገዝ ወዘተ ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪም የተማሪዎችን የመማር ፍላጎትና ውጤታማነት ለማሳደግ ታዋቂ ግለሰቦች እና የመንግስት ከፍተኛ አመራሮች በተማሩባቸው ትምህርት ቤቶች በመገኘት የህይወት ክህሎታቸውንና የሀገር ሰላም ግንባታ ላይ የተመሰረተ ቀስቃሽ፣ አበረታችና አነቃቂ ንግግሮችን በማድረግ የአለም ታላቁ የትምህርት ቀንን እንዲያከብሩ ተደርጓል።

ትምህርት ቤቶች ምቹ የመማሪያ ማስተማሪያ አካባቢዎች እንዲኖራቸው ከማድረግ አንፃር በ2013 የትምህርት ዘመን ለመማር ማስተማሩ ወሳኝ የሆኑ የቤተ ሙከራ፣ የቤተ መጽሀፍት፣ መፀዳጃ ቤት፣ ንፁህ የመጠጥ ውሃ፣ የተማሪዎችን መቀመጫ ወንበር ግብዓቶችን በማሟላት የት/ቤቶችን ገፅታ መቀየርና ተማሪዎች ተረጋግተው ት/ቤት ላይ እንዲቆዩ በማድረግ በኩል የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል።

የትምህርት ቤቶችን የውሃ አቅርቦት ለማሻሻል በተሰራው ስራ 4,168 (45.7%) አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ንጹህ የመጠጥ ውሃ ያላቸው ሲሆን ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ 477 (77.6%) ያህሉ ንጹህ የመጠጥ ውሃ አላቸው። በተመሳሳይ መጸዳጃ ቤት ያላቸውን ትምህርት ቤቶች መረጃ ስንመለከት በአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ 7,931 (86.9%) እና በሁለተኛ ደረጃ 599 (97.4%) ያህሉ ናቸው።

የቤተመፃህፍት እና ንባብ ኮርነርን ማሟላትን በሚመለከት ደግሞ የንባብ ኮርነር ያላቸው የመጀመሪያው ሳይክል የአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 1,778 (69.4%) ሲሆኑ ቤተመፃህፍት ያላቸው ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤቶች 4,633 (52.7%) ናቸው። 590 (95.9%) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቤተመፃህፍት አላቸው።

የስርዓተትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል ያላቸው ትምህርት ቤቶች አፈጻጸም ሲታይ 5,792 (63.5%) አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና 411 (66.8%) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያሟሉ ናቸው።

የስፖርት ሜዳን በሚመለከት በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ 4,237 (46.4%) ትምህርት ቤቶች በስታንዳርዱ መሰረት የተሟላ ሜዳ አላቸው፣ 2,752 (30.2%) ያልተሟላ ሜዳ ሲኖራቸው 1,955 (21.4%) ደግሞ ምንም አይነት ሜዳ የላቸውም። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ 393 (63.9%) ትምህርት ቤቶች በስታንዳርዱ መሰረት የተሟላ ሜዳ አላቸው፣ 139 (22.6%) ያልተሟላ ሜዳ ሲኖራቸው 99 (14.6%) ደግሞ ምንም አይነት ሜዳ የላቸውም።

ሌላው ግብአትን በማሟላት የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሻሻል እና ጥራት ያለው ትምህርት ለማድረስ የተማሪ መቀመጫ እና ኮምባይንድ ዴስክ እንዲሟላ ሰፋፊ ስራ የተሰራ ቢሆንም አሁንም የሚቀሩ ተግባራት እንዳሉ መረጃዎች ያመለክታሉ።

የመማር ማስተማር ሂደቱን ውጤታማ ለማድረግ ትኩረት የተደረገው የመምህራን የማስተማር ክህሎት ማጎልበት ነው። ከዚህ አኳያም በት/ቤትና ጉድኝት ደረጃ በተለያዩ ርዕሶች ላይ (በቤተ ሙከራ አሰራር፣አሳታፊ የማስተማር ስነ ዘዴ፣ ተከታታይ ምዘና፣ ዕለታዊና ዓመታዊ የትምህርት ዕቅድ ዝግጅትና ትግበራ፣ ከአካባቢ በሚገኙ ቁሣቁሶችን በመጠቀም ሚዲያ ዝግጅትና አጠቃቀም፣ ተማሪ ተኮር የትምህርት አቀራረብ፣ የእርስ በርስ ሱፐርቪዥን ዙሪያ... ወዘተ) ያተኮሩ በርካታ አጫጭር ስልጠናዎች በማዘጋጀት እንዲሰጡ ተደርገዋል። ከዚህ ሌላ መምህራን በሌሰን ጥናት መርሃ ግብር አማካኝነት በትምህርት ክፍላቸው የትምህርት ዕቅድና የክፍል ጊዜ ጥናት (Lesson plan and Lesson study) ስታንዳርድ ተከትለው ሌሰን ፕላን በማዘጋጀትና በክፍል ተጠሪ መምህራን እንዲረጋገጥ በማድረግ የክፍል ውስጥ መማር ማስተማር ስራውን ከማከናወን ጎን ለጎን በየጊዜው እየተገናኘ በሚያስተምሩት የትምህርት አይነት ይዘትና የማስተማር ስነ ዘዴ ላይ የሚያደርጉት የልምድ ልውውጥ አበረታች ሆኖ ተገምግሟል።

በአጠቃላይ በተሰጡት ሥልጠናዎች መምህራን ሥልጠናዎችን እንደግብዓት በመጠቀም የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል እየተጉ መሆናቸው፣ የፋብሪካ ውጤቶችን በአካባቢ ከሚገኙ ቁሳቁሶች በመተካት የመጠቀም ልምድ መዳበሩ፣ ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ የማዘጋጀትና መጠቀም ባህል መጨመሩ፣ ተከታታይ ምዘና በተገቢ ሁኔታ መጠቀም፣ ተማሪ ተኮር የትምህርት አቀራረብን ተግባራዊ ለማድረግ ጅምር እንቅስቃሴ መኖሩ፣ ተመሳሳይ የትምህርት ዓይነት የሚያስተምሩ መምህራን እርስ በርስ መደገገፍ መጀመራቸው የሚሉ ለውጦች ታይተዋል።

ሌላው ከመማር ማስተማር አኳያ የተከናወነው ተግባር የባከነ ክፍል ጊዜ በትምህርት ቤቶች እንዳይከሰት/ሲከሰትም ለማካካስ የሚያስችሉ አካባቢያዊ ስልቶች እንዲቀየሱ በማድረግ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ያለ መምህር/ያለ ትምህርት እንዳይቀመጡ ተደርጓል።

የተማሪዎች ውጤት በማሻሻል በኩልም በ 2012 የ 8 ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ከወሰዱ 382,991 (ወንድ 185,632 ሴት 197359) ተማሪዎች መካከል 50% እና በላይ ያስመዘገቡት 275,434 (ወንድ 136,225፣ ሴት 139,209) ወይም 71.92% (ወንድ 73.38%፣ ሴት 70.54%) ናቸው። በሌላ በኩል የ 12 ኛ ክፍል ሀገራዊ ፈተና ከተፈተኑት ተማሪዎች መካከል 350 በላይ ያስመዘገቡ ተማሪዎች ምጣኔ 66.1% ሆኖአል። ይህም ከአገርአቀፉ አማካይ 55.9% ጋር ሲነፃፀር ብልጫ ያለው ውጤት መሆኑን መረዳት ያስችላል። በተመሳሳይ ከ 400 በላይ ያስመዘገቡ 38.0% (አገርአቀፍ 28.8%)፣ ከ 500 በላይ 5.0% (አገር አቀፍ 3.8%) እንዲሁም ከስድስት መቶ በላይ 156 ተማሪዎች (በአገርአቀፍ 704 ተማሪዎች) በመሆኑ ክልላዊ ውጤቱ በንጽጽር የተሻለ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

በአጠቃላይ ሲታይ የተማሪዎችን ውጤት በሚፈለገው ደረጃ ከማሻሻል አንፃር የተወሰኑ ለውጦች እንዳሉ ሆኖ የችግሩ አሣሣቢነት እንደቀጠለ ነው። የተማሪዎች የመማር ብቃት ምዘና ውጤቶች አስመልክቶ ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻሎች ቢኖሩም ከተቀመጠው ስታንዳርድ አኳያ ሲታይ በቀጣይ የትምህርት ዘመን የበለጠ ርብርብ ማድረግ ያለብን መሆኑን ያመለክታል። የመጀመሪያው ችግር የት/ቤት መሻሻል መርሃ ግብርን በሚገባ በመረዳት በግለ ግምገማ በተለዩ የትኩረት ጉዳዮች ላይ የማቀድ ክህሎት ማነስና ዕቅዱን በቁርጠኝነት የመፈፀም ችግር ነው። ሁለተኛው የሚስተዋለው ችግር ደግሞ ለተማሪዎች ትምህርት መከታተልና ውጤት መሻሻል ቁልፍ ሚና ያለውን ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር አቀራረብና የተከታታይ ምዘና ስርዓት በአግባቡ አለመተግበር ነው። ሦስተኛው ችግር ደግሞ ከመንግሥት ግ/ቤት ከሚመደብ

በጀት ጎን ለጎን ሌሎች ባለድርሻ አካላትን በማሣተፍ ሁሉንም ት/ቤቶች ምቹና ጤናማ የትምህርት አካባቢ ለማድረግ ጥረት በመደረጉ በየዓመቱ ተደማሪ ለውጦች ቢኖሩም ከችግሩ ስፋትና ግዝፈት አንፃር በአጭር ጊዜ ውስጥ ሁሉንም ት/ቤቶች ምቹና ተደራሽ ማድረግ አልተቻለም። ከሁሉም በላይ ት/ቤቶች ለሴቶችና ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ሆነው አይስተዋሉም። አራተኛው ችግር ወላጆች በልጆቻቸው ትምህርት የመከታተልና የትምህርት ውጤት ላይ በባለቤትነት የሚሣተፉበት ደረጃ በየጊዜው መሻሻሎች ያሉበት ቢሆንም አሁንም የሚጠበቀውን ያህል አላደገም። አምስተኛው ችግር የተማሪዎችን የመማር ውጤትና ስነ ምግባር በማሻሻል ረገድ ወላጆች፣ መምህራንና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የራስን ድርሻ ከመውሰድ ይልቅ ችግሩን ውጫዊ በማድረግ ችግሩን ለመፍታት የሚያደርጉት ርብርብ በቂ አይደለም። ስድስተኛው ችግር ውስን የሆነውን የትምህርት ሐብት በመጠቀም ረገድም ያለው አፈፃፀም ከብክነት የፀዳ ባለመሆኑ በቀጣይ ልዩ ትኩረት መስጠት ይገባል።

### 2.2.3. የትምህርት ሥርዓቱን በዲጂታል ቴክኖሎጂ መደገፍ

የትምህርት ስርዓቱ በዲጂታል ቴክኖሎጂ መደገፍ የተለያዩ የትምህርት ይዘቶችን ለተማሪዎች ግልፅ እና በቀላሉ ሊገባ በሚችል መልኩ ለማቅረብ፣ የተማሪዎችን የምዘና ስርዓት ለማሻሻል እና የመረጃ ልውውጡን ለማቀላጠፍ እንዲሁም በት/ቤቶች የመረጃ አያያዝን ለማሻሻል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል። ከዚህም በተጨማሪ ስርአተ ትምህርቱ፣ የመማር ማስተማሪያ ማቴሪያሎች፣ የማስተማር ስልቶችና የምዘና ስርአቶችን በማዘመንና በማሳደግ ተማሪዎችን በቂ የሆነ እውቀት፣ ክህሎትና ችሎታ እንዲኖራቸው በማድረግ ማህበረሰቡ ውስጥ ሁለንተናዊ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያስችላል። ከዚህ በመነሣት በ 2013 ዓ/ም የተከናወኑ ተግባራት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

የዲጂታል ቴክኖለጂን በመጠቀም የትምህርት ስርዓቱን ለማሻሻል ምዘናን በማዘመን ረገድ የ 2012 የዩኒቨርስቲ መግቢያ የ 12 ኛ ክፍል ተፈታኞችን በቴክኖሎጂ ለመፈተን የሚያስችል የአቅም ግንባታ ስራዎች ተሰርተዋል፣ ብሮድባንድ ኔትዎርክ መሰረተ ልማት ተሳስረው የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የሆኑ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ኮሌጆች ድርሻ ለማሳደግ እና ከ 2014 ዓ.ም ጀምሮ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የትምህርት ታብሌት ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ።

በክልሉ ከሚገኙት 568 የመንግስት 2 ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 285 ትምህርት ቤቶች የኢንተርኔት መሰረተልማት የገባላቸው ሲሆን፤ ከነዚህም ውስጥ 183 ትምህርት ቤቶች ብሮድባንድ ተጠቃሚ ናቸው። 102 ት/ቤቶች ደግሞ የቪሳት ኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ናቸው። ነገር ግን የተማሪ መማሪያ ክፍሎችን በኔትወርክ በማስተሳሰር ኢንተርኔትን ለተማሪዎች ተደራሽ ማድረግ የቻሉት 65 ትምምህርት ቤቶች ብቻ ናቸው። በክልላችን ከሚገኙ 615 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የኮምፒተር ትምህርት በመስጠት ላይ የሚገኙት 398 (64.7%) ብቻ ናቸው። መረጃው በተሰበሰበባቸው ዞኖች የተጠቃሚ ተማሪዎችን ቁጥር በመውሰድ በተሰራው ስሌት መሰረት የኮምፒተር ተማሪ ጥምርታ 0.07 መሆኑን ያሳያል።

በተመሳሰይ በክልሉ ከሚገኙ 10 የመንግስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች 10 ሩም የብሮድባንድ ኢንተርኔት ተጠቃሚ ናቸው። ነገር ግን የተማሪዎችን ቁጥር ታሳቢ ያደረገ በኔትወርክ የተያያዘ እና ለተማሪወች ኢንተርኔትን ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል የኮምፒዩተር ክፍል አደረጃጀት ላይ በኮሌጆች መካከል ሰፊ ልዩነት አለ።

በሚቀጥለው አመት ከፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር ጋር የሚሰሩ ትምህርትን በዲጂታል ቴክኖሎጂ የመደገፍ ስራዎች (የታብሌት አቅርቦት፣ ዲጂታል ፈተና፣ ዲጂታል ምዘና፣ ዲጂታል የትምህርት ቤት መረጃ ማሰባሰብ ወዘተ) እንደሚሳኩ የሚጠበቅ ይሆናል።

### 2.2.4. አካታች የሆነ ትምህርት ተሳትፎና ውስጣዊ ብቃት

ትምህርት አገራችን ላቀደችው የመካከለኛ ገቢ ኢኮኖሚ ራዕይ መሣካት በዋነኛነት ጉልህ ድርሻ ያለውና በመካከለኛና በከፍተኛ ደረጃ የሚፈለግ የሰለጠነ የሰው ሃይል ልማት መሠረት በመሆኑ በክልላችን መንግሥት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት በመከናወን ላይ የሚገኝ ሲሆን በዘመኑ ያለው አፈፃፀም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

#### 2.2.4.1. የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም፣

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ህፃናት ለተስተካከለ የአካልና የአእምሮ፣ የስሜትና የማህበራዊ ግንኙነት እድገት በማዳበር ለመደበኛው ትምህርት እንዲዘጋጁ የሚያመቻች እንዲሁም በየደረጃው አካባቢያቸውን እንዲገነዘቡና እንዲያውቁ የሚያደርግ ነው፡፡ በፕሮግራሙ 830,190 (ወንድ 422,466፣ ሴት 407,724) ህጻናትን በመመዝገብ ጥቅል የትምህርት ተሳትፎውን 43.49% (ወንድ 43.44%፣ ሴት 43.53%) ለማድረስ ታቅዶ በትምህርት ዘመኑ መጀመሪያ ላይ 672,853 (ወንድ 344,969፣ ሴት 327,884) ህፃናት በትምህርት ገበታ ላይ የነበሩ ሲሆን በዚህም የ 2013 በጀት ዓመት ጥቅል የትምህርት ተሣትፎ 35.24% (ወንድ 35.47%፣ ሴት 35.01%) ማድረስ ተችሎ ነበር፡፡ በተነፃፀሪነት ሲታይ የተሻለ አፈፃፀም ያላቸው ዞኖች ሰሜን ሸዋ (97.26%)፣ ዋግኅምራ (95.42%)፣ እና ኦሮሞ ብሄረሰብ (94.62%) ሲሆኑ አነስተኛ አፈጻጸም ያላቸው ደግሞ ጎንደር ከተማ (66.51%)፣ ደቡብ ጎንደር (69.08%) እና ሰሜን ጎንደር (70.99%) ናቸው፡፡

ከፆታ ፍትሃዊነት አንፃርም የ 2013 የትምህርት ዘመን የቅድመ መደበኛ ትምህርት ጥቅል ተሣትፎ ፆታዊ ክፍተት 0.99 ሲሆን ይህም በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል ከሞላ ጎደል ልዩነት የሌለ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

በክልላችን በዓመቱ መጨረሻ ላይ 674,449 (346,840 ወንድ፣ 327,609 ሴት) ህፃናት ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ሲሆኑ በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ተመዝግበው ትምህርት ከጀመሩት መካከልም ያቋረጡ ተማሪዎችም 85,592 (45,541 ወንድ፣ 40,051 ሴት) ወይም 11.26% (11.61% ወንድ፣ 10.89% ሴት) ናቸው፡፡

የቅድመ መደበኛ ትምህርት በሁሉም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጋር አብረው በተከፈቱ የመማሪያ ክፍሎች እየተሰጠ ሲሆን በአንዳንድ አካባቢዎች ሣተላይት ጣቢያዎችን በመክፈት የተቋማቱን ተደራሽነት እንዲሰፋ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የመማር ማስተማሩ ያለበትን ሁኔታ ስናይ የመማሪያ ክፍሎችን በማዘጋጀት ፤መምህራንን ቀጥሮ ፕሮግራሙ ባለቤት እንዲኖረው በማድረግ ፤የውስጥና የውጭ መጫዎቻዎችን በማዘጋጀት ፤ውስን ቢሆኑም የራሳቸው ክልልና መጸዳጃ ቤት እንዲኖራቸው በመደረጉ ወደፊት ጥራት ያለው ቅድመ መደበኛ ትምህርት ለመስጠት ጥሩ ልምዶች ተገኝተዋል፡፡

በሌላ በኩል በአንድ ክፍል ከስታንዳርዱ በላይ የሆኑ ህጻናት መኖር፣ ያለመማሪያ ክፍል በሜዳና በዛፍ ጥላ ስር ማስተማር፣ ባልሰለጠኑ አመቻች መጠቀም፤ ከስታንዳርዱ በላይ በአንድ ክፍል ውስጥ ተጨናንቀው ምቹ ባልሆነ ሁኔታ እንዲማሩ መደረጉ፣ የሰለጠኑትን አመቻች አለመቅጠር እና የማስተማሪያ መጽሀፍት አለመኖር ወዘተ ችግሮች ይታያሉ፡፡ስለሆነም የፕሮግራሙ የችግር መጠንና የችግሮችን ምንጭ እንዲሁም ፍላጎትና አቅርቦት መካከል የሚታየው ከፍተኛ ልዩነት በየደረጃው ባለው አመራሩ የትኩረት መጠን ልዩነቶች የተነሳ በመሆኑ ችግሮቹን ለመቅረፍ ተገቢ እቅድ ተዘጋጅቶ መስራትን ይጠይቀናል፡፡

#### 2.2.4.2. የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም አፈፃፀም፣

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በስምንት ዓመት የሚጠናቀቅ ሆኖ፣ በመሠረታዊና አጠቃላይ ትምህርት ለሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ የሚያዘጋጅና በሂደት የሚዳብር መሠረታዊ ችሎታ ያላቸውን ዜጎች የሚያፈራ ነው። በዘመኑ በክልላችን 4,299,594 (ወንድ 2,215,813፣ ሴት 2,083,781) ነባርና አዲስ ገቢ ተማሪዎችን በመመዝገብ ጥቅል የትምህርት ተሳትፎውን 84.71% (86.08% ወንድ፣ 83.30% ሴት) ለማድረስ ታቅዶ በትምህርት ዘመኑ መጀመሪያ ላይ ለመማር የተመዘገቡት 3,825,090 (ወንድ 1,939,624፣ ሴት 1,885,466) ሲሆኑ ጥቅል ተሳትፎው 75.36% (75.35% ወንድ፣ 75.37% ሴት) ሆኗል። የየዞኖች አፈፃፀም ሲታይ የተሻለ አፈፃፀም ያስመዘገቡትን ስንመለከት ኦሮሞ ብሄረሰብ (96.78%)፣ ደሴ ከተማ (96.55%) እና ምዕራብ ጎንደር (96.30%) ሲሆኑ ዝቅተኛ አፈፃፀም ያላቸው ደግሞ ሰሜን ወሎ (85.89%)፣ምስራቅ ጎጃም(86.22%) እናሰሜን ሸዋ (86.48%)ናቸው።

ከፆታ ፍትሃዊነት አንፃርም የ 2013 የትምህርት ዘመን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሣትፎ ፆታዊ ክፍተት 1.00 ሲሆን ይህም በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል ልዩነት የሌለ መሆኑን ያስገነዝባል።

በተግባር ምእራፍ ወቅት ልዩ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ አዘዉትሮ ትምህርት ቤት አለመገኘትንና ትምህርት ማቋረጥን መከላከል ሲሆን ይህንንም በውጤታማነት ለመፈፀም ከአካባቢዉ አስተዳደርና ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች፣ የሴቶች የልማት ቡድን፣ የእናቶች አደረጃጀት፣ በትኩረት እየተሰራ ይገኛል። ይህ ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ በአንዳንድ ት/ቤቶች እስከ 10% ተማሪዎች እያሣለሱ ት/ቤት የሚመጡ መሆናቸውን ከስም መጠሪያ ደብተር ማረጋጥ ተችሏል። የተማሪዎችን ማቋረጥ በተመለከተ በዓመቱ መጀመሪያ ላይ በትምህርት ገበታ ላይ ከተገኙት ተማሪዎች ውስጥ 154,888 (ወንድ 95,736፣ ሴት 59,152) ቀሩ ሲሆን ይህም ከተመዘገቡት 4.05% (ወንድ 4.94%፣ ሴት 3.14%) አቋርጠዋል። በከፋ ሁኔታ ተማሪ የቀረባቸው ዋግ ህምራ (12.6%)፣ ምዕራብ ጎንደር (9.1%)፣ ሰሜን ጎንደር (7.9%) እና ደቡብ ጎንደር (8.3%)

## 2.2.4.3. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም አፈፃፀም፣

በዘመኑ በክልላችን 989,152 (ወንድ 487,147፣ ሴት 502,005) የሚሆኑ ነባርና አዲስ ገቢ ተማሪዎችን በመመዝገብ ጥቅል ተሳትፎውን 40.08% (38.74% ወንድ፣ 41.48% ሴት) ለማድረስ ታቅዶ 947,578 (ወንድ 446,024፣ ሴት 501,554) በመመዝገብ አፈፃፀሙ 95.80% (91.56% ወንድ፣ 99.91% ሴት) ሲሆን ጥቅል ተሳትፎው 38.40% (35.47% ወንድ፣ 41.44% ሴት) ደርሷል። የተሻለ አፈፃፀም ያላቸው ዞኖች ደሴ ከተማ (111.27%)፣ ጎንደር ከተማ (103.87%) እና ባህር ዳር ከተማ (101.97%) ሲሆን ዝቅ ያለ አፈፃፀም ያላቸው ኦሮሞ ብሄረሰብ (67.57%)፣ ሰሜን ሸዋ (87.69%) እና ደቡብ ወሎ (87.91%) ናቸው።

ከፆታ ፍትሃዊነት አንፃርም የ 2013 የትምህርት ዘመን የሁለተኛ ደረጃ በጥቅል የትምህርት ተሣትፎ ፆታዊ ክፍተት 1.17 ሲሆን ይህም የሴቶች ተሣትፎ ከወንዶች የበለጠ መሆኑን ያስገነዝባል። በ 2013 የትምህርት ዘመን የተመዘገበው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሣትፎ በ 2012 የትምህርት ዘመን ከነበረው 40.40% (ወንድ 36.93%፣ ሴት 44.13%) ጋር ሲነፃፀር በ 2.36% (2.19% ወንድ፣ 2.54% ሴት) ጨምሯል።

የተማሪዎችን ማቋረጥ በተመለከተ በዓመቱ መጀመሪያ ላይ በትምህርት ገበታ ላይ ከተገኙት ተማሪዎች ውስጥ 30,244 (ወንድ 13,784፣ ሴት 12,817) ወይም 3.19% (ወንድ 3.09%፣ ሴት 2.56%) ተማሪዎች አቋርጠዋል። በከፋ ሁኔታ ተማሪ የቀረባቸው ደቡብ ጎንደር (8.1%)፣ ሰሜን ጎንደር (7.2%)እና ዋግ ህምራ (5.2%) ናቸው።

## 2.2.4.4. የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፕሮግራም አፈፃፀም

በዘመኑ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም 23,023 (ወንድ 12,261፣ ሴት 10,762) የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን በማስተማር ጥቅል ተሳትፎውን 2.58% (2.71% ወንድ፣ 2.44% ሴት) ለማድረስ ታቅዶ 17,026 (ወንድ 9,423፣ ሴት 7,603) ተማሪዎችን በመመዝገብ የምዝገባ እቅድ አፈፃፀሙ ከታቀደው 73.95% (ወንድ 76.85%፣ ሴት 70.65%) ሲሆን ጥቅል ተሳትፎውን 1.91% (2.08% ወንድ፣ 1.73% ሴት) ሆኗል። በትምህርት ዘመኑ መጨረሻ ላይ በመማር ላይ ያሉት 14,515 (ወንድ 8,140፣ ሴት 6,375) ሲሆኑ የማቋረጥ ምጣኔውም 9.13% (ወንድ 9.67%፣ ሴት 8.44%) ሆኗል።

በዘመኑ 2283 (ወንድ 1,411፣ ሴት 872) የልዩ ፍላጎት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎችን በማስተማር ጥቅል ተሳትፎውን 0.53% (0.64% ወንድ፣ 0.41% ሴት) ለማድረስ ታቅዶ የተመዘገቡት 1,448 (ወንድ 856፣ ሴት 592) ተማሪዎችን ሲሆኑ በዚህ መሠረት የምዝገባ እቅድ አፈፃፀሙ 61.96% (ወንድ 59.65%፣ ሴት 65.63%) እና ጥቅል ተሳትፎ ምጣኔው 0.33% (0.39% ወንድ፣ 0.28% ሴት) ሆኗል። በ 2013 የትምህርት ዘመን መጨረሻ ላይ ደግሞ 846 (ወንድ 535፣ ሴት 311) ተማሪዎች በመማር ላይ ያሉ ሲሆን በዚህም መሠረት የማቋረጥ መጠን 3.97% (ወንድ 2.55%፣ ሴት 6.33%) ነው።

## 2.2.4.5. ማጠቃለያ

በ 2013 ዓ/ም ለማሣካት ካስቀመጥነው ግብ አንፃር ሲታይ የዘመኑ የቅድመ መደበኛና የመጀመሪያ ደረጃ የተማሪዎች ምዝገባና ተሣትፎ ግቡን አልመታም። እንዲሁም በ 2012 በጀት ከተመዘገበው ጋር ሲነፃፀር አፈፃፀሙ ዝቅተኛ ነው። በ 2012 ዓ/ም በመማር ላይ የነበሩ ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ ወደ ት/ቤት አለመምጣትና አዲስ ገቢ ተማሪዎችን መመዝገብ አለመቻል ለዕቅዱ አለመሣካት በምክንያትነትም ይጠቀሣሉ።

ተማሪዎች ወደ ት/ቤት ያልመጡበት ቁልፉ ችግር በኮረና ቫይረስ በሽታ ምክንያት ት/ቤቶች ተዘግተው ለረጅም ጊዜ በመቆየታቸው የተነሣ በርካታ ተማሪዎች ወደ ሌላ አካባቢ ለቀው መሄድና ያሉትም ቢሆን ወላጅ ለመላክ ፈቃደኛ አለመሆን፣ በ 2013 ዓ/ም የተማሪዎች እቅድ ላይ በቂ መተማመን አለመፈጠሩ፣ የአጎራባች ዞን፣ ወረዳና ቀበሌ፣ ት/ቤት ተማሪዎችን አሟጥጦ አለመመዝገብ፣ የቦታ አቀማመጡ ለህፃናት አመቺ አለመሆኑ፣ በየደረጃው ያለው መዋቅር ለምዝገባ ስራው ትኩረት አለመስጠት፣ በክልል ደረጃ መግባባት ከተደረሰበት አቅጣጫ ውጭ መፈፀም እና ከተመዘገቡት መካከል ሁሉም በትምህርት ቤት መጥተው መማር አለመቻላቸው ናቸው።

የመጀመሪያው ችግር የኮቪድ-19 ያስከተለው አሉታዊ ተጽእኖ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተውን የኮቪድ ስርጭት ተከትሎ በሀገራችን የኮቪድ-19 ስርጭትን ለመከላከል ከ 2012 ዓ.ም መጋቢት ወር ጀምሮ ለ 9 ወራት የመማር ማስተማር ሂደት በመቋረጡ የተነሣ በርካታ ተማሪዎች ከቤታቸው ውለዋል። በመቀጠልም ት/ቤቶች ዳግም እንዲከፈቱ ለማድረግ ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ የመፍጠር እና የንቅናቄ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች መካከል በት/ቤት የኮቪድ-19 ፕሮቶኮሎች አተገባበር፣ በኮቪድ-19 ምክንያት ከትምህርት የቀሩ ተማሪዎች ወደ ት/ቤት እንዲመጡ ማድረግና የት/ቤቶች ዝግጁነትና መደበኛ የመማር ማስተማር ሂደትን ማስቀጠል ይገኙበታል። በዚህም በበጀት አመቱ ከቅድመ መደበኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ድረስ ከ 5.6 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት መመለስ ተችሏል። ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ከመጡ በኋላም በትምህርት ቤት ውስጥ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ የግንዛቤ የመፍጠር ስራዎችን

በማከናወን በትምህርት ቤቶች የኮቪድ ስርጭት እንዳይኖር በማድረግ የመማር ማስተማር ሂደቱ ያለመቋረጥ እንዲቀጥል ማድረግ ተችሏል። ከላይ የተዘረዘሩት አበረታች አፈፃፀሞች ቢኖሩም በ 2012 በመማር ላይ የነበሩ ሁሉም ነባር ተማሪዎች ወደ ት/ቤት አልተመለሱም።

ሁለተኛው ችግር በዘመኑ ዕቅድ ላይ በወረዳና በት/ቤት መካከል በቂ መተማመን አለመድረስ ነው። በዘመኑ እንደ ቀደሙት ዓመታት ሁሉ ከክልል እስከ ት/ቤት ድረስ የታቀደው የተማሪዎችን ብዛት ወጥ የሆነና ተመጋጋቢ መሆን ይገባዋል። ነገር ግን በወረዳና በት/ቤት ደረጃ የታቀደው እቅድ የማይናበብና ልዩነት ያለው ነው። ለልዩነት መከሰት ዋናው ችግር አመራሩ በየት/ቤቶች ለታቀደው እቅድ ተገቢውን ግንዛቤ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት መፍጠር አለመቻሉ ነው። በዚህም የተነሣ በወረዳና በት/ቤት ደረጃ እቅዱ የተጋነነ ወይም በጣም የተለጠጠ በመሆኑ ማሣካት አይቻልም የሚል ጫፍ የወጣ አስተሣሰብ በመያዙ ነው። በተለይም በት/ቤት ደረጃ ያለው አመራርና መምህራን የትምህርት ቤት ወላጅ ግንኙነት በጣም ዝቅተኛ በሆነበት የታቀደውን እቅደ ለማሳከት አይቻልም የሚል አመለካከት መያዙና ይህንንም ለማስተካከል የተከናወኑ ተግባራት ውስኑንነት ያለባቸው በመሆኑ ተግባሩ እንዳይሣካ መሠናክል ሆነዋል።

ሦስተኛው ችግር የአጎራባች ዞን፣ ወረዳና ቀበሌ፣ ት/ቤት ተማሪዎችን አሟጥጦ አለመመዝገብ ነው። በአንዳንድ አካባቢዎች በቀበሌው ያለው ት/ቤት ለሌላ ቀበሌ ቅርብ የሚሆንበት አጋጣሚዎች አሉ። ይህ ክስተት ሲፈጠር በቀበሌው ያለው የመንግሥት አደረጃጀት ተማሪዎችን ቀስቅሶ በአጎራባች ቀበሌው ለሚገኘው ት/ቤት መላክና መመዝገባቸውን ማረጋገጥ ሲገባ በቸልታ የማለፍ ሁኔታ ታይቷል። ተመሣሣይ ሁኔታም በአጎራባች ወረዳዎችና ዞኖች ተከስቷል። ይህንን ፈጥኖ እንዲስተካከል ጥረቶች ቢደረጉም በአንዳንድ አካባቢዎች በተሟላ ሁኔታ ባለመፈፀም የተማሪዎች ምዝገባ እንዳይሣካ መሠናክል ሆኗል።

አራተኛው ችግር የቦታ አቀማመጡ ለህፃናት አመቺ አለመሆኑ ነው። በምሥራቅ አማራ በሚገኙ ዞኖች የመሬቱ አቀማመጥ ተራራማና ወጣ ገብ የበዛበት በመሆኑ ተማሪዎች በቀላሉ ወደ ት/ቤት መምጣት አልቻሉም። ይህንን ችግር ለመፍታት በአብዛኛው አካባቢዎች ሣተላይት የመማሪያ ክፍሎች የተከፈቱ ቢሆንም ችግሩ ሙሉ በሙሉ መቅረፍ ባለመቻሉ የተማሪዎችን ምዝገባ ውጤታማ እንዳይሆን አድርጎታል።

አምስተኛው ችግር በየደረጃው ያለው መዋቅር ለምዝገባ ስራው ትኩረት አለመስጠት ነው። በዘመኑ የተማሪዎችን ምዝገባ በህዝብ ንቅናቄ አግባብ ለመፈፀም በቅድሚያ የተማሪ ልየታ ስራውን በአደረጃጀት ማከናወን፣ በመቀጠልም የፓይለት ምዝገባ ማካሄድና አፈፃፀሙን መገምገም በመጨረሻም አደረጃጀትን ተጠቅሞ በአንድ ቀን ውስጥ የተማሪዎችን ምዝገባ ማጠናቀቅ በሚሉት የአሠራር ስርዓት ላይ ስምምነት ተደርሶ ነበር። ይሁን እንጂ በተግባራዊ ሂደት በሁሉም አካባቢዎች በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት አልተፈፀመም። በበርካታ ት/ቤቶች በ 2012 በበጋው ወቅት የተለየውን የአዲስና የነባር ተማሪዎችን መረጃ በስም፣ በቀበሌ እና በጎጥ ለይቶ ለቀበሌ አደረጃጀት መሪዎች በመስጠት የምዝገባ ስራው እንዲከናወን ተደርጓል። በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ት/ቤቶች ለአደረጃጀቶች ምንም አይነት መረጃ ያልሰጡ ሲሆን ይህም ችግሩ በወቅቱ ለማረም ጥረቶች ተደርገዋል። ከተማሪ ልየታ በመቀጠልም የተማሪዎች ምዝገባ በተቻለ መጠን በአንድ ቀን ውስጥ ማጠናቀቅ ካልሆነ በሦስት ቀን ውስጥ ሙሉ በሙሉ ለማጠናቀቅ በቅድሚያ በሁሉም ት/ቤት ከመጀመሩ በፊት የምዝገባ የሙከራ ስራ (pilot) በመጠቀም የሙከራ ስራው በጥንካሬ እና በድክመት ተገምግሞ ለሁሉም ቀበሌዎችና ት/ቤቶች በማድረስ በንቅናቄ ማስመዝገብ የሚል አቅጣጫ የተቀመጠ ቢሆንም አፈፃፀሙ የተዥጎረጎረና በሁሉም አካባቢ በተመሣሣይ ሁኔታ አልተፈፀመም። ከዚህ በተጨማሪ ተሞክሮዎቹን ቀምሮ በማስፋት ረገድም የተሄደበት ርቀት ውስንነት ያለበት ነው። በአጠቃላይ በየደረጃው ያለው አመራር የተማሪዎችን ምዝገባ በክልል ከተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት በጥብቅ ዲስፒሊን መፈፀም ባለመቻሉ ግቡን ማሣካት አልተቻለም።

በአደረጃጀት የተመዘገቡት ሁሉም ተማሪዎች ወደ ት/ቤት መጥተው ትምህርት መጀመር አለመቻላቸው ሌላው ስድስተኛው ችግር ነው። በአደረጃጀት የተለዩ ተማሪዎች በስም ዝርዝር ከተለዩ በኋላ ወደ ት/ቤት መጥተው ትምህርት አልጀመሩም።

ሰባተኛው ችግር የውሸት መረጃ በተለይ በቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ማስተላለፍ ነው። ቀደም ባሉት ዓመት በአቻ ለአቻ ትምህርት ስልት ይማራሉ ተብለው ይተላለፍ የነበረው መረጃ በተጨባጭ መሬት ላይ የሌለ በመሆኑና ይህ መርሃ ግብር ተገምግሞ እንዲቋረጥ ሲደረግ የተማሪዎች ቁጥር በእጅጉ እንዲቀንስ አድርጎታል።

በሁሉም ደረጃዎች የተማሪዎች ተሣትፎ ግቡን አለመምታት ደግሞ ሀገራችን በ 2017 ዓ.ም የመጀመሪያ ደረጃ መካከለኛ ገቢ ኢኮኖሚ ራዕይ ለማሣካትና ከዚህ ግብ እውን መሆን ጋር ለሚከሰተው ሁለንተናዊ የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሽግግር ውጤታማነት ከፍተኛ ድርሻ ያለውን ሰብአዊ በማፍራት ረገድ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል። እንዲሁም አገራችን የፈረመቻቸውን ዓለም አቀፍ እና አህጉር አቀፍ ስምምነቶች የዘላቂ ልማት ግብ፣ ትምህርት ለሁሉም ግብ ማሣካት አይቻልም። በመሆኑም የጉዳዩን አሣሣቢነት ግምት ውስጥ በማስገባት በ 2014 የትምህርት ዘመን ባለፈው ዓመት ያቋረጡትን ተማሪዎች፣ በ 2013 በትምህርት ገበታ ላይ የነበሩትን እና አዲስ ገቢ ተማሪዎች አማጥጦ ወደ ት/ቤት ለማምጣት ከምንጊዜውም በላይ የሞት ሽረት ትግል ማድረግ ይጠይቃል።

### 2.2.5. ከሥራ ጋር የተሳሰረ የጎልማሶች እና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት

ጐልማሶች በፍላጐታቸውና ችግራቸው ላይ የተመሰረተ፣ የዕለት ተግባራቸው ጋር የተገናዘበ፣ ወዲያውኑ ሊተገብሩት የሚችሉ፣ ለህይወታቸው ቅርብ የሆነ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማታቸውን የሚያሻሽሉበት የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጐልማሶች ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህንን ማድረግ ሲቻል ደግሞ ምርታማነቱ ያደገ፣ ጤንነቱ የተጠበቀ፣ ገቢው የተሻሻለ፣ በምክክር ዘይቤው የተለወጠ ህብረተሰብ መፍጠርና መካከለኛ ገቢ ያላቸውም ሆነ ከዚያ በላይ ሀብት መገንባት ይቻላል።

የፌደራል ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በ 2009 ዓ.ም በወጣው ሪፖርት መሰረት በክልላችን ዕድሜያቸው ከ 15-60 የሆኑ ጎልማሶች 10,958,954 (ወንድ 4,243,984፣ ሴት 5,714,970) ሲሆኑ ከእነዚህ መካከልም ማንበብና መፃፍ የሚችሉት 5,186,484 (ወንድ 3,085,472፣ ሴት 2,102,012) ናቸው። በመሆኑም ማንበብና መፃፍ የማይችሉት 5,772,470 (ወንድ 2,158,512፣ ሴት 3,613,958) ናቸው። በመሆኑም በክልሉ ከሚኖረው ጎልማሣ መካከልው ማንበብና መፃፍ የማይችሉት 52.67% (ወንድ 41.16%፣ ሴት 63.24%) ይሆናሉ። ከዚህ መካከል አብዛኛው በገጠር አካባቢ የሚኖረው ህዝብ ነው።

ከዚህ አጠቃላይ ሁኔታ በመነሣት በዘመኑ 242,260 (ወንድ 141,648፣ ሴት 100,612) ጎልማሶችን የህይወት ክህሎት ትምህርትን ለመስጠት ታቅዶ የተከናወነው 6,042 (ወንድ 3,435፣ ሴት 2,607) ወይም ከእቅዱ 2.5% (ወንድ 2.4% ሴት 2.6%) ብቻ ነው።

የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ተሣትፎን ከማሣደግ አንፃር በዘመኑ 5923 (14.9%) መማሪያ ጣቢያዎችን ተደራተዋል። እንዲሁም 4,604 (ወንድ 2,272 ሴት 2,332) (11.6%) አመቻቾች ወደ ስራ ገብተዋል። በተጨማሪም 40,897,464 ብር (ለአመቻች ቅጥር 40,610,692 ብር እና ለስልጠናና ስራ ማስኬጃ 286,772 ብር) ተመድቦ በስራ ላይ ውሏል። በመሆኑም በዘመኑ በአንደኛ እና ሁለተኛ አመት 1,190,815 (ወንድ 53,4018 ሴት 656,797) ጎልማሶችን ለማሳተፍ ታቅዶ የተመዘገቡ 420,424 (ወንድ 251,975 ሴት 170,653) ወይም 35.31% (ወንድ 47.18% ሴት 25.98%) ሲሆኑ ከተመዘገቡት መካከል በመሳተፍ ላይ የሚገኙት 85,573 (ወንድ 51,124 ሴት 32,963) ወይም 7.19% (ወንድ 9.57% ሴት 5.02%) መሆኑ የምንገኝበትን ዝቅተኛ አፈጻጸም የሚያሳይ ነው።

የትምህርት ብርሃን ምዘና ትልቅ ትርጉም የአለው የጎልማሶችን እና ታዳጊዎችን የእውቀትና ክህሎት ደረጃ መለኪያ መሳሪያ ሆኖ በዘመኑ በክልላችን ተጀምሯል። የትምህርት ምዘና ስረ በአገርአቀፍ በይፋ እንደተጀመረ መመሪያና ድርጊት መርሃግብር ክልላዊ ይዘት የተከለሰ ሲሆን በክልል ትምህርት አመራር እንዲሁም በዞን እና ወረዳ ባለሙያዎች ትውውቅ ተደርጓል። በመቀጠልም በሁሉም የዞን እና ወረዳ የትምህርት አመራሮች በተገኙበት መድረክ በይፋ መርሃግብሩ ተጀምሯል።

በመሆኑም በትምህርት ብርሃን በክልላችን በ 2,006 ቀበሌዎች በ 4,712 የምዘና ጣቢያዎች ተዘጋጅተው 234,610 (ወንድ 147,265፣ ሴት 60,345) ተመዛኞች ምዝገባ ተካሂዷል። ከምዝገባ በኋላ አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ ለ 142,786 (ወንድ 113,313፣ ሴት 29,473) ምዘና ተካሂዷል። በዚህም በምዘናው ስታንዳርዱን ያሟሉ 119,732 (ወንድ 96,485፣ ሴት 23,247) ወይም 83.85% ሆኗል።

የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት በማከናወን ረገድ ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች የሚሰጠው ሥልጠና ከጐልማሳው ሕይወት ማለትም ግብርና፣ ጤና፣ የሕይወት ክህሎት፣ ወዘተ. ጋር የተቆራኘ አለመሆን፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሴክተር መ/ቤቶች መካከል ያለው ቅንጅታዊ አሠራር ጠንካራ አለመሆን፣ ተአማኒና ወቅታዊ መረጃ አለመኖር፣ የግብአቶች አለመሟላት፣ ፕሮግራሙን ለመምራት በየደረጃው የተቋቋሙት የቦርድና የቴክኒክ ኮሚቴዎች ተግባራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ አለመግባት፤ መርሀግብሩን ለትምህርት ሴክተር ብቻ መተው … ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው።

የተቀናጀ  ተግባር ተኮር የጐልማሶች ትምህርት የሰው ሀብት ልማትን ለማሳደግ አንዱ አካልና የማያቋርጥ ከመሠረታዊ የማንበብና መጻፍ ክህሎት እስከ የሕይወት ክህሎት፣ የገቢ ማስገኛ እንዲሁም አጫጭር የሙያ ክህሎት ትምህርትና ስልጠና  የሚሰጥና ኢኮኖሚውን በከፍተኛ ደረጃ ሊደግፍ የሚችል ፕሮግራም ቢሆንም የተሰጠው ትኩረት በጣም አናሣ ከመሆኑም ባሻገር መካከለኛ ኢኮኖሚ ደረጃ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመግባት  ወሳኝ መሆኑን በየደረጃው ያለው አመራር ሊገነዘቡ ይገባል። እንዲሁም ከፌዴራል እስከ ጣቢያ ድረስ ባለቤት ሆኖ በሃላፊነት የሚሰራውን አደረጃጀት ማቋቋም እና ማጠናከር ያስፈልጋል። ከዚህ አንፃር የአገራችንን 53.68% (66.35% ወንድ፣ 42.10% ሴት) እና የክልላችን 47.28% (58.74% ወንድ፣ 36.75% ሴት) አፈጻጸም ስናየው መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች (76.4%) ተርታ ለመሰለፍ በሚቀጥሉት ጊዜያት በጣም በርካታ ስራ መፈፀም ይጠብቀናል።

ከዚህ መሠረታዊ ሃሣብ በመነሣት በ 2013 ዓ/ም የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት መርሀግብሮችን ተደራሽነት ማሳደግ፣ የጎልማሶች የህይወት ክህሎት ትምህርትን በታቀደው ልክ እንዲያጠናቅቁ ማድረግ፣ የተቋቋሙ መማሪያ ጣቢያዎችን ከፍ ማድረግ፣ በመደበኛው የትምህርት ፕሮግራም የመማር እድል ያላገኙ ዜጎችን በተከታታይ (የማታና የርቀት) ትምህርት ተደራሽነትን በማሻሻል እንዲቻል በየደረጃው ስራዎችን መስራት ይገባል። በተጨማሪም የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት መርሀግብሮችን ፍትሀዊነትን ለማሳደግ የፆታ ምጥጥንን በታቀደው መሰረት ከፍ ለማድረግ የተቀመጡ አቅጣጫዎችን መከተል አስፈላጊ ነው።

### 2.2.6. ያልተማከለ የትምህርት ሥርዓት

ያልተማከለ የትምህርት ስርዓትን ከማጎልበት አኳያ ትኩረት የተደረገው ያልተማከለ የትምህርት አስተዳደርን የበለጠ ማከናከርና ውጤታማ የሐብት አጠቃቀም ስርዓት መፍጠር ሲሆኑ በእያንዳንዱ ያለው ዝርዝር አፈፃፀሙ እንደሚከተለው ቀርቧል።

#### 2.2.6.1. ያልተማከለ የትምህርት አስተዳደር

አቅምን ያጎለበተና ተጠያቂነት የሰፈነበት ያልተማከለ የትምህርት አስተዳደርን ለማጠናከር የማስፈጸሚያ ማንዋል ዝግጅትን በተመለከተ በመምህራን እና ትምህርት አመራር ልማት ዳይሬክቶሬት በኩል የተጀመሩ ስራዎች በመጠናቀቅ ላይ ናቸው።

የትምህርት ቤት አመራሮችን ደረጃ ማሻሻልን በሚመለከት በቢሮው የመምህራን እና ትምህርት አመራር ዳይሬክቶሬት በኩል በተደራጀው መረጃ በዘመኑ ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚመጥን የትምህርት ዝግጅት ያላቸው ር/መምህራን ብዛት 72.8% ለማድረስ ታቅዶ መረጃው የሁሉንም ዞኖች ባያካትትም አፈጻጸሙ 63.3 (ሴት 66.2 ወንድ 63.1) ሆኗል። አፈጻጸሙ ዝቅተኛ የሆነበት አንዱ ምክንያት የሆነው በ 2012 ክረምት ትምህርታቸውን ማጠናቀቅ የነበረባቸው አመራሮች በኮቪድ ምክንያት ትምህርት አለማጠናቀቃቸው ነው። በተመሳሳይ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚመጥን የትምህርት ዝግጅት ያላቸው ር/መምህራን ብዛት 62.8% ለማድረስ ታቅዶ መረጃው በተሰባሰበባቸው ዞኖች አፈጻጸሙ 53.1 (ሴት 100 ወንድ 53.4) ሆኗል። በተመሳሳይ የአለፈው ክረምት ትምህርት አለመሰጠቱ እንደችግር የሚወሰድ ነው።

በ 2013 ዓ.ም ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚመጥን የትምህርት ዝግጅት ያላቸው ሱፐርቫይዘሮችን ብዛት 94.2% ለማድረስ ታቅዶ መረጃው ከተሰበሰበባቸው ዞኖች አፈጻጸሙ 94.5 (ሴት 97.4 ወንድ 94.5) ሆኗል። በተመሳሳይ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚመጥን የትምህርት ዝግጅት ያላቸው ሱፐርቫይዘሮችን ብዛት 86.91% ለማድረስ ታቅዶ መረጃው ከተሰበሰበባቸው ዞኖች አፈጻጸሙ 86.70 (ሴት 100 ወንድ 86.53) ሆኗል። በዚህም የአለፈው ክረምት ትምህርት መቋረጥ አሉታዊ ተፅእኖ ያሳደረ ነው።

በወረዳ ደረጃ የተደራጁና ውጤታማ የሆኑ የተማሪ ወላጆች ማህበር ማቋቋም እንዲቻል ወደ ታችኛው አካል እቅድ ወርዶ በመሰራት ላይ ይገኛል። የትምህርት መረጃ አስተዳደርና አጠቃቀም ስርዓትን ለማዘመን መለያ ኮድ ያላገኙ ተቋማትን በመለየት የማስተካከል ስራ ተሰርቷል።

አመታዊ የትምህርት ቤቶች መረጃ ማሰባሰቢያ መጠይቅን የማዘጋጀት፣ ማሳተም፣ ማሰልጠን እና ማሰራጨት ስራ ከተሰራ በኋላ በሁሉም የክልሉ ቅድመአንደኛ፣ አንደኛና መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና በጎልማሶች ማሰልጠኛ ማዕከላት ተሞልቶ ወደ ክልል ቢሮ ደርሷል። በዳታቤዝ የማስገባትና ለአስፈላጊ የእቅድ፣ ግምገማና ፖሊሲ ስራዎች አገልግሎት የመጠቀም ስራ ይሰራል።

መረጃን ከአሁኑ አሰራር በተሻለ ለማዘመን ከትምህርት ሚኒስቴር ጀምሮ ስራዎች የተጀመሩ ሲሆን በአዲስ መልክ ታብሌት በመጠቀም መረጃ ለማሰባሰብ የሚያስችል የመጠይቅ ዝግጅት ሲደረግ የቢሮው ባለሙያ ተሳትፎ አድርጓል፤ በቀጣይ ግብአት ሲሟላ ስልጠና ተሰጥቶ ወደ ስራ የሚገባ ይሆናል።

## 2.2.6.2. ውጤታማ የሀብት አጠቃቀም ሥርዓት

ውጤታማ የሀብት አጠቃቀም ስርዓትን ማጎልበት እንዲቻል በትምህርትና ስልጠና ዘርፉ ከክልል እስከ ትምህርት ቤት ድረስ የመንግስት የበጀት ድርሻን ከፍ ማድረግ አንድ ተግባር ነው። መንግስት ከአለው ውስን ሀብት ለመምህራንና ሰራተኞች ደመወዝና ስራ ማስኬጃ፣ በትምህርት ቤቶች የነፍስወከፍ ድጎማ እንዲመደብ በማድረግ እና ጥራት ያለው ትምህርት አቅርቦት እንዲሻሻል በአግባቡ የተደራጁ ትምህርት ቤቶች ግንባታዎችን ማስፈጸሚያ በጀት መመደብ የሚጠበቅበት ሲሆን ሰፋፊ ስራዎች በመሰራት ላይ ናቸው።

ከዚህ ሌላ በዘርፉ የሚታየውን የሀብት ጉድለት ለመሙላት የአጋር ድርጅቶች ድርሻን ከፍ እንዲል ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ በዘመኑ የተለያዩ ድርጅቶች እንዲሳተፉ ተደርጓል። የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻል ለፍትሀዊነት (GEQIP-E)፣ የተባበሩት መንግስታት የሕፃናት መርጃ ድርጅት (UNICEF) እና ሌሎችም አካላት በዘርፉ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ በዚህ ሪፖርት የፕሮጀክቶች አፈጻጸም በሚዳስሰብት ክፍል በዝርዝር ቀርቧል። ይህን ለማገዝም በትምህርት ተቋማት በህብረተሰብ፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በግል ባለሀብቶች እና በተቋማት የውስጥ ገቢ የተሰበሰበ ሀብት በስራ ላይ ውሏል። የዘመኑ የትምህርት ተቋማት የበጀት አቅርቦትን የሚመለከተው መረጃ በክፍል አንድ የተገለጸ ሲሆን የመንግስት እና ሌሎች አጋር አካላት በጀት አፈጻጸም ደግሞ በክፍል ሶስት በዝርዝር የሚቀርብ ይሆናል።

### 2.2.7. የትምህርት ጥራት የማረጋገጥ ሥርዓት

የትምህርት ሥርዓቱ በመልካም ሥነምግባር የታነፁና ለሥራ ዝግጁ የሆኑ ተማሪዎችን ማፍራቱን ለማረጋገጥ የተዘረጉ ስርዓቶች የትምህርት ጥራት እንስፔክሽን ማካሄድ፣ የመምህራንና ትምህርት አመራር ሙያ ፍቃድ አሰጣጥና እድሳት መስጠትና በየሣይክሉ ማጠናቀቂያ ላይ የብቃት ፈተና ማካሄድ በእቅድ የተያዙ ስራዎች ሲሆኑ በአመቱ የተሰሩ ስራዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

#### 2.2.7.1. የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን አፈጻጸም

በ 2013 አዲስ የሚከፈቱ ትምህርት ቤቶች እና ደረጃቸውን የሚያሳድጉ ትምህርት ቤቶች ከስታንዳርድ አኳያ ስራቸውን በወቅቱ እንዲጀምሩ ከማድረግ አንጻር አዲስ የይከፈትልንና ደረጃ ይደግልን ጥያቄ እንደቀረበ ወዲያውኑ ወደ ትምህርት ቤቶች በመሄድ ያሉበትን ደረጃ በማዬት ወዲያውኑ አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት ወደ ተግባር እንዲገቡ ተደርጓል በዚህም መሰረት በስታንዳርዱ መሰረት አሟልተው የተገኙትን 25 (ሀያ አምስት) 2 ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአዲስ እንዲከፈቱ ፈቃድ እንዲኖራቸው ተደርጓል።

በትምህርት ዘመኑ ኢንስፔክት ለማደረግ ከታቀዱ ተቋማት ውስጥ በቅድመ አንደኛ ደረጃ በድጋሜ ኢንስፔክሽን ለ 178 አፀደህፃናት አገልግሎቱን ለመስጠት ታቅዶ ለ 135 (76%) ትምህርት ቤቶች አገልግሎቱን መስጠት ተችሏል። በዚሁ ፕሮግራም በኦ ክፍል በ GEQIP-E Supported Phase 1 Schools ለ 416 ትምህርት ቤቶች አገልግሎቱን ለመስጠት ታቅዶ ለ 391 (94%) ተሰርቷል። በ GEQIP-E Supported Phase 2 Schools ደግሞ ለ 518 ትምህርት ቤቶች አገልግሎቱን ለመስጠት ታቅዶ ለ 375 (72%) ትምህርት ቤቶች ተሰርቷል።

በአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የኢንስፔክሽን አገልግሎት ደግሞ 1896 አዳዲስና ነባር (ድጋሚ) የታቀደ ሲሆን 1684 (89%) ተከናውኗል። በሁለተኛ ደረጃ ለ 149 ትምህርት ቤቶች አገልግሎቱን ለመስጠት የታቀደ ሲሆን በ 135 (91%) ትምህርት ቤቶች ኢንስፔክሽን ተሰርቶ ደረጃ ተሰጥቷል።

#### 2.2.7.2. የመምህራንና ትምህርት አመራር ሙያ ፍቃድ አሰጣጥና እድሳት

በዘመኑ በየደረጃው ለሚገኙ መምህራን፣ ርዕሳነመምህራን እና ሱፐርቫይዘሮች የሙያ ፈቃድ ምዘና በማካሄድ ፍቃድ ለመስጠት እና ለማደስ ከተያዘው እቅድ ውስጥ በመምህራን ትምህርት ኮሌጅ የ 2012 ዓ.ም እጩ ተመራቂዎች ምዘና ተካሂዷል። በዚህም መሰረት እጩ መምህራኑ በሰለጠኑበት ቋንቋ እና የትምህርት አይነት በእንግሊዝኛ፣ በአማርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በአዊኛ እና በህምጣና ቋንቋዎች ከተምህርት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ የመጣውን የምዘና መሣሪያ በመተርጎም 12758 (ወንድ 7394 ሴት 5364) ተመዛኞች ተመዝነዋል። ይህም

መመዘን ከሚገባው አንጻር ሲታይ የዕቅዱን 99.4% ነው። በተጨማሪም የተመዛኞች መልስ ታርሞ መልሳቸው ወደ ዳታቤዝ የገባና የውጤት ትንተና ሥራውም የተጠናቀቀ ነው።

## 2.3. የማጠቃለያ ምእራፍ አፈፃፀም፣

በማጠቃለያ ምዕራፍ ዋነኛው የርብርብ ማዕከል የማጠቃለያ ፈተና መስጠትና አርሞ ውጤቱን ለተማሪዎች ማሳወቅ እንዲሁም የተማሪ ውጤት መተንተንና ለውይይት ዝግጁ ማድረግ ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪ የግለሰብ፣ የቡድንና የተቋም ግምገማ በማድረግ ጠንካራና በቀጣይ መስተካከል ያለባቸውን በመለየት በመልካም አፈፃፀሞች ላይ ተሞክሮ የሚቀመር ይሆናል።

## 2.4. ማጠቃለያ

በ 2013 በጀት ዓመት በዝግጅት ምዕራፍ ወቅት ጥራት ያለው ዕቅድ በማዘጋጀት፣ ኮቪዲ-19 በመከላከል የመማር ማስተማር ተግባር ለመፈፀም አስፈላጊ ኦሪንቴሽን መስጠትና ግብአት ማሟላት የተከናወኑ ሥራዎች፣ ፕሮግራሙ በጠንካራ ድጋፍና ክትትል በመምራት፣ የትምህርት ቤቶችን መሰረተ ልማትና ግብአት በማሟላት ረገድ የተሻለ አፈፃፀም የታየባቸው ተግባራት በመሆናቸው የዝግጅት ምዕራፍ ተግባራት ከሞላ ጎደል በተሻለ ሁኔታ ለመፈጸም ጥረት ተደርጓል። በመድረኮች ውይይት ወቅትም ዋናው ትኩረት የተማሪዎች ምዝገባ፣ የቀውስ ወቅት ትምህርት አመራርን እና ቀጣይ ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዩችን የሚመለከት ነው። ይህም በሁሉም መድረኮች ላይ ከፈጻሚ አካላት ጋር በተደረገው ወይይት በመሰረታዊ ጉዳዮች ዙሪያ የጋር መግባባት ላይ ተደርሷል።

የትምህርት ዘመኑን በተሳካ ሁኔታ ለማስኬድ የሚያስችል በርካታ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች የተከናወኑ ቢሆንም በታቀደው ልክ ያልተሳኩ ተግባራት መኖራቸው ሊሰመርበት ይገባል። ያልተሳኩ ተግባሮቻችን መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሰው የተማሪ ምዝገባ እቅዳችን ነው። በ 2013 የትምህርት ዘመን የተማሪዎች ምዝገባ ዕቅድ አፈፃፀም የቅድመ መደበኛ 671,183 (80.05%)፣ የመጀመሪያ ደረጃ 3,824,010 (88.94%) እና የሁለተኛ ደረጃ 859,724 (86.92%) ላይ ነው። በሁሉም የትምህርት ዕርከኖች የተማሪዎች ምዝገባ ግብ ሙሉ በሙሉ የተሳካ ባይሆንም በተለይ 7 ዓመት የሞላቸው ህፃናትን ሙሉ በሙሉ ወደ ትምህርት ገበታ እንዲመጡ የተቀመጠው ግብ አፈፃፀም 68.92% ላይ የሚገኝ በመሆኑ አሳሳቢ ችግር ነው። ከግብዓት አቅርቦት አንፃር በአንዳንድ ወረዳዎች በበጀት እጥረት የተነሣ ተጨማሪ መምህራን መቅጠር አለመቻል፣ የመፅሃፍት ስርጭት በሚፈለገው ፍጥነት አለመጠናቀቁና የፕላዝማ ትምህርት መቆራረጥ ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊፈቱ የሚገባቸው ችግሮች እንደሆኑ ተገምግሟል።

በተግባር ምእራፍ ወቅትም በቅድመ ዝግጅት ወቅት በአግባቡ ያልተከናወኑትን በማሣካት የምእራፉን ተግባራት በውጤታማነት ለመፈጸም ጥረት ተደርጓል። የተማሪዎችን ውጤት የማሻሻል እና በዓመቱ መጀመሪያ ላይ የተመዘገቡ ተማሪዎች ሳያቋርጡ ትምህርታቸውን እንዲያጠናቅቁ ማድረግ ዋናው የርብርባችን ማዕከል ነበር። የእነዚህ ተግባራት አፈጻጸም እድገትና መሻሻል የታየበት ቢሆንም ከተማሪዎች ውጤት መሻሻልም ሆነ የተማሪዎችን ማቋረጥ መቀነስ አንፃር አፈጻጸሙ አሁንም ቢሆን ትኩረት የሚሻ ነው።

የተማሪዎች አዘውትረው በትምህርት ገበታ ላይ አለመገኘትና ማቋረጥ አንዱ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው። በተለይ በገጠር ትምህርት ቤቶች ችግሩ ሰፊ ነው። ይህን ችግር ለመቅረፍ የት/ቤት ወላጅ ግንኙነትን በማጠናከር ወላጆች ልጆቻቸውን በሁሉም የትምህርት ቀናት ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኳቸው መጠነ ሰፊ ርብርብ ተደርጓል።

ሁሉም ተማሪዎች ቢያንስ የማለፊያ ነጥብ እንዲያስመዘግቡ ለማድረግ የመማር ማስተማር ተግባሩን ውጤታማ በማድረግ ረገድ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት  መጠነ ሰፊ ርብርብ ተደርጓል። በዚህ መሠረት በት/ቤት ደረጃ ወርክሽት አዘጋጅቶ ተማሪዎችን ጥያቄዎችን እንዲለማመዱ ማድረግ፣ ያለፉት ትምህርቶችን በትርፍ ጊዜያቸው የመከለስ፣ የማጠናከሪያ ትምህርት የመስጠት፣ የመማር ማስተማር ሂደቱ አሳታፊና ተማሪ ተኮር ማድረግ፣ ተከታታይ የምዘና ስርዓት በሁሉም መምህራን ዘንድ ወጥ በሆነ አሰራር ተግባራዊ ማድረግ፣ የውስጥ ሱፐርቪዥን በተሟላ ሁኔታ በማካሄድ መምህራን እንዲደጋገፉ ማድረግ፣ ስርዓተ ትምህርቱ በተቀመጠለት የጊዜ ሠሌዳ/ዕቅድ እንዲሸፈን ጥረት እና ክትትል ማድረግ፣ የሳይንስ ትምህርቶች በስታንደርዱ መሠረት በቤተሙከራ ተደግፎ እንዲሰጡ ማድረግ፣ የተሟላ የቤተ መፅሀፍት አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ፣ የመማር ማስተማር ሂደቱን በጥናትና ምርምር እንዲደገፉና መምህራን ብቃታቸውን እንዲያሳድጉ የተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራምን ተግባራዊ የማድረግ አሠራሮች ተከናውነዋል።

የት/ቤቶችን ገጽታ በማስተካከል ረገድም በክልላችን በ 2013 በጀት ዓመት መሠረተ ልማት ያልተሟላላቸውና ምቹ ያልሆኑ በርካታ ት/ቤቶችን ደረጃ ለማስተካከል በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል። በተለይም በዘመኑ በክልላችን በአልማ አስተባባሪነት በሁሉም አካባቢዎች ችግሩን ከምንጩ ለማድረቅ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር መግባባትን በመፍጠር መጠነ ሰፊ ንቅናቄ በመደረግ ላይ ይገኛል።

ሌላው ትኩረት ተሰጥቶት የተከናወነው ተግባር ደግሞ በክልላችን ለሚገኙት --- መደበኛ ት/ቤቶች የተማሪዎች ኮምባይንድ ዴስክ እና ለቅድመ መደበኛ ተቋማት የመቀመጫ ወንበርና ጠረጴዛ ለት/ቤቶች እንዲደርስ በማድረግ አበረታች ውጤቶች ማስመዝገብ ተችሏል።

በሁሉም የትምህርት ተቋማት ሠላማዊ መማር ማስተማር የሰፈነባቸው እንዲሆኑ ማድረግ አንዱ የርብርብ ማዕከል ነው። ከዚህ አንፃር ትምህርት ተቋማት ከፀረ-ሠላም ሀይሎች የብጥብጥና የሁከት ድርጊት የፀዱ እንዲሆኑ ፣ የትምህርት ሴኩላሪዝም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ከማንኛውም የሀይማኖትና የፖለቲካ ቅስቀሳና ተግባር ነፃ እንዲሆኑ ትኩረት ተሰጥቶት ተከናውኗል። ዴሞክራሲያዊነት እንዲስፋፋ የትምህርት ተቋማት በምክንያት ላይ የተመሠረተ ነፃ የሀሳብ ክርክር የሚካሄድባቸው፣ ችግሮች ሲፈጠሩ በሰለጠነ አግባብ በውይይት የሚፈቱባቸው ልዩነትን በማቻቻል ጠንካራ አንድነት የሚፈጠርባቸው የፆታ እኩልነት የሰፈነባቸው እንዲሆኑ ሰፊ ርብርብ ተደርጓል።  በመሆኑም በዘመኑ በሁሉም ት/ቤቶች ፍጽም የሆነ ሠላማዊ የመማር ማስተማር የሰፈነበት ነው።

ከላይ የተጠቀሱ ዋና ዋና ተግባራትን በማከናወን የክልላችን ህዝብ ተጠቃሚነቱን ለማረጋገጥ መምህራን የማይተካ ሚና አላቸው። በመሆኑም ለመምህራን የተመቸ የስራ ሁኔታ እንዲኖራቸው የማድረግ ጉዳይም ትኩረት ተሰጥቶት የተከናወነ ተግባር ነው። በመሆኑም የመምህርነት ሙያ በህብረተሰቡ ዘንድ ተገቢው ክብር እንዲሰጠው ለማድረግ በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል። በዚህ መሠረት የመምህራን ቀን በድምቀት በማክበር በሙያቸው አንጋፋ የሆኑና የላቀ ውጤት ያስመዘገቡት ተገቢው የማበረታቻ ሽልማት እንዲያገኙ የማድረግ ተግባር በሁሉም ደረጃ እየተዘወረ ተከብሯል። በቅጥር፣ በዝውውር፣ በደረጃ ዕድገት እና በልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች ዙሪያ ያሉ ችግሮችን በመቅረፍ በትምህርት ዘርፍ መልካም አስተዳደርን የማስፈን ስራ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ተከናውኗል።

ይህ በእንዲህ እያለ በስራ ዘመኑ እነዚህ የተገለጹትና ሌሎች ያልተዘረዘሩ መልካም አፈጻጸሞች ያሉትን ያህል በየደረጃው የአመራሩንና ፈጻሚውን ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ታይተዋል። ለአብነትም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተማሪ ወደ ትምህርት ገበታ አለመምጣት፣ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ከመጡም በኋላ አለማቆየትና በየደረጃው ከፍተኛ ሊባል የሚችል መጠነ ማቋረጥ መኖር፣ የተማሪዎች የመማር ውጤት ዝቅተኛ መሆን ከትምህርት ውስጣዊ ብቃትና ጥራት አኳያ የታዩ አሳሳቢ ችግሮች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም በሁሉም አካባቢዎችና

የክፍል ደረጃዎች ምቹ የመማር ማስተማር አካባቢ አለመፍጠርና አሁንም ቢሆን ምቹ ባልሆኑ ክፍሎች ተማሪዎች መኖር አንዱ ችግር ሆኖ ይታያል፡፡

በየደረጃው የሚገኘው የትምህርት አመራር የወሰደው ተልእኮ ከሌላ ስራ ጋር በተደራቢነት የሚሰራ ሳይሆን ለሀገሪቱ ህልውና ወሳኝ የሆነ የህዝብና መንግስት አልፋና ኦሜጋ የሆነ የሰውን ልጅ የማፍራት ታላቅ ተልእኮ መሆኑን አውቆና ባወቀው ልክ ከመተግበር አኳያ ውስንነት ያለበት ነው፡፡ በተለይም ከፍተኛ አመራሩ ሀገሪቱ በምንም ደረጃ ላይ ብትገኝ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ለውጦ የነገን ብሩህ ተስፋ መገንቢያ መንገዱ በእሱና እሱ በሚመራው ሴክተር ውስጥ መሆኑን አውቆ አመራር እንዲሰጥ ይጠበቅበታል፡፡ ይሁን እንጂ አሁንም በደራሽ ስራዎች መጠመድና በየደረጃው የሚፈለገውን ስትራቴጂያዊ አመራር ያለመስጠት፣ ተግባሩ ላይ ተተክሎ ያለመፈጸምና ተከታታይነት ያለው አመራር ያለመስጠት፣ አቅጣጫዎችን ለቅሞ አለማውረድና ቋሚ የሆነ የክትትልና ድጋፍ ስልት ዘርግቶ አለመተግበር፣ እየተገበርን ያለውን ያልተማከለ የትምህርት ስርአት ተከትሎ የመካከለኛ አመራር ቾል በመፍጠር አቅሙን ገንብቶ፣ የመወሰን ስልጣን ሰጥቶና ጠንካራ የቁጥጥር ስርአት ዘርግቶ ከማብቃት ይልቅ ስራዎችን አማክሎ የመያዝ በዚህም መነሻ ተተኪ አመራር ያለማፍራትና ለሚፈጠሩ ክፍት ቦታዎች ምደባ የተዘጋጀ አመራር እስከማጣት የደረሱ ችግሮች ይታዩበታል፡፡ ይህ አመራር በሴክተሩ እየደረሱ ያሉ የውስጣዊ ብቃትና የተማሪ የመማር ውጤት መውደቅ የእኔ ችግር ነው ብሎ ከልብ ከመነጨ ስሜት አለመውሰድና በዚህም መነሻ ችግሮቹ ከትምህርት ዘመን ትምህርት ዘመን ከመሻሻል ይልቅ እየተወሳሰቡ መሄዳቸውን እንደ ዋና ችግሩ ወስዶ በትኩረት ሊሰራባቸው ይገባል፤፡

በየደረጃው የሚገኘው መካከለኛ አመራር ለፈጻሚ ሀይል በቅርብ ርቀት የሚገኝ ብቻ ሳይሆን በቁልፍ ጉዳዮች በከፍተኛ አመራሩና ፈጻሚው መካከል ወሳኝ ሚናውን በመጫወት ትግበራው እንዲፋጠን ማድረግ የሚጠበቅበት ሀይል ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የስራ ክፍላቸውን ብሎም ተቋማቸውን ለመለወጥ ሰርተው ለውጥ ያመጡ አመራሮች ቢኖሩም ቁጥራቸው እዚህ ግባ ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ እነዚህ አካላት ሌት ተቀን በስራቸው ላይ ከመጠመድ አልፈው ያላቸውን የግል ጊዜ ጭምር ለእቅዳቸው መሳካት የሚያውሉና ተከታይ እያፈሩ የሚሄዱ ናቸው፡፡ በአንጻሩ ግን ለፈጻሚው ድጋፍ የማይሰጡ፣ ዋና ተልእኮአቸውን ሳይወጡ በሌሎች ስራዎች የሚሸሸጉ፣ ስልጠና በዋለበት በሙሉ የማይጠፉና በሰለጠኑትም ቢሆን እርባና የለው ተግባር ሲፈጽሙ የማይታዩ፣ እቅዳቸውን እየገመገሙ የማይመሩና ራሳቸውን ከፈጻሚው በሚለዩአቸው ጉዳዮች ላይ ግልጽ ያልሆኑ፣ ሆነው ከሆነ በዚህ ልክ የማይንቀሳቀሱ አመራሮች አሉ፡፡ በመሆኑም በየደረጃው ለዚህ አመራር ከተሰጠው ተልእኮ አኳያ ተግባሩን ገምግሞ በማረም ማሰማራት ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ ተግባር ነው፡፡

የትምህርት ቤት ደረጃ አመራሩ የእለት ተእለት የመማር ማስተማር ስራውን በቅርበት የሚመራ አመራር ነው፡፡ ይህ አመራር የተሰማራበት ስራ በቀጥታ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው ትግበራ የሚከናወንበት መስክ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ በርካታ ተልእኮአቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁ፣ የትምህርት ቤትና አካባቢውን ማህበረሰብ ያሳተፈ እቅድ አዘጋጅተው ትግበራውን በባለቤትነት በመምራት የተማሪን ውጤት የሚያሻሽሉ አመራሮች አሉ፡፡ ቀላል የማይባሉ የትምህርት ቤት ደረጃ አመራሮች ያለውን ውስን ሀብት በአግባቡ መርተው፣ አስቸጋሪ ከሆኑ ሁኔታዎች ጋር ተጋፍጠው ሰላማዊ የመማር ማስተማር ከባቢን በመፍጠር የሚያደርጉት ጥረት በአግባቡ ተፈትሾ ተገቢውን እውቅና ሊያገኝ የሚገባው ነው፡፡ ይሁን እንጂ ግልጽነት በጎደለው መንገድ ወደ አመራርነት የመጡ፣ ስትራቴጂክም ሆነ አመታዊ እቅድ ስርአቱን ጠብቆ እንዲታቀድ የማያደርጉ፣ የትምህርት ቤት ማህበረሰቡን የማያሳትፉ፣ ተግባርን በእውቀትና በባለቤትነት የማይመሩ፣ ለውስጣዊ ብቃት ችግርና ለመማር ውጤት መውደቅ የማይደነግጡ፣ የትምህርት ቤት ሀብትን በአግባቡ የማይጠብቁና ስራ ላይ የማያውሉ፣ የመማር ማስተማር ስራውን የማይደግፉ፣ ከተልእኮአቸው ውጪ በሆኑ ስራዎች የሚደበቁ፣ ችግር ፈቺ ከመሆን ይልቅ ራሳቸው የችግር አካል የሚሆኑ የትምህርት ቤት ደረጃ አመራሮች መኖራቸው በተለያየ መልኩ ይገለጻል፡፡ ስለሆነም ለሀገሪቱ የትምህርት ስርአት ትግበራ ወሳኝ በሆነው በዚህ

የአመራር እርከን ላይ ከሌሎች መስፈርቶች በጸዳ አግባብ አመራር ማሰማራት አካባቢውን ብሎም ሀገሪቱን ማዳን መሆኑን አውቆ የማያዳግም የእርምት እርምጃ መውሰድ ይጠበቃል።

መምህራን የመማር ማስተማር ስራውን ተግብረው ሀገሪቱ የምትፈልገውን የበቃ የሰው ሃይል የማራፍት ታላቅ አደራን የወሰዱ አካላት ናቸው። ይህንን ሀላፊነታቸውን እጅግ ባልተመቻቹ ሁኔታዎች ውስጥ ሆነው፣ ያሉባቸውን ውስጣዊና ውጪዊ ችግሮች ተቋቁመው ለመወጣት የሚተጉ፣ የግል የሚባል ጊዜ የሌላቸው ያላቸውን ሁሉ ለተማሪዎቻቸው የሰጡ፣ በተጨባጭ የተማሪዎቻቸውን ውጤትና ስነምግባር የቀየሩ አንቱ የተባሉ መምህራን በየደረጃውና በየአካባቢው አሉን። አመራሩ እነዚህ መምህራን ያከናወኑትን ተግባር ገምግሞና አውቆ ተገቢውን እውቅና መስጠት ይጠበቅበታል። በሌላ በኩል የማስተማርን ታላቅ ሙያና ሀገራዊን ተልእኮ ተገቢ ባልሆነ መልኩና ቦታ ለድርድር የሚያቀርቡ፣ በሚናፈሱ ወሬዎች ሳያገናዝቡ የሚደናገሩ፣ የእለት ተግባርና ሀላፊነታቸውን የማይወጡ፣ ራሳቸውንና ሙያቸውን በአግባቡ አክብረው የማይቀሳቀሱ ጥቂት መምህራን በአንዳንድ አካባቢዎች ይታያሉ። ይህንን ሁኔታ ለማጥራት ከእቅድ አኳያ የግለሰብን አፈጻጸም እየገመገሙ እነዚህ አካላት በታታሪ መምህራን ተነሳሽነት ላይ አሉታዊ ጫና እንዳይፈጥሩ መስራት ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ የ 2013 የትምህርት ዘመን ትልልቅ ውጤቶች የተመዘገቡበት እና በተለይም ለቀጣዩቹ ዓመታት ሥራዎች ብዙ ልምዶች የተገኙት ዓመት በመሆኑ ለ 2014 ሥራችን መስፈንጠሪያ ቦርድ ሆኖ ያገለግለናል። በሌላ በኩል አሁን ካስመዘገብነው በላይ ውጤት ማስመዝገብ እንዳንችልን ላደረጉን ማቆዎች በዝርዝር በመለየት በ 2014 እቅዳችን መልሰናቸው ከገባን በእርግጥም 2014 የትምህርት ዘመን የለውጥ ንቅናቄ ወደ ማይቀለበስበት ደረጃ ልናደርስ የምንችልበት ዓመት ይሆናል።

## 2.5. ቀጣይ እቅዳችን መነሻ የሚሆኑ ስኬታማ አፈጻጸሞችና ወሳኝ ጉዳዮች (Success and Critical Issues)

### 2.5.1. ስኬታማ አፈፃፀሞች

#### 2.5.1.1. ተቋማዊ የመፈፀም አቅም

- በ 2013 የትምህርት ዘመን ለአመራሩ በርካታ ሥልጠናዎች በመሰጠታቸው በማቀድ፣ በመከታተል፣ በአደረጃጀትና በአሰራር ላይ ክህሎታቸውን በማሣደግ ረገድ የተሻለ ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል። በየደረጃው የሚገኙ አመራሮች የባለቤትነት ስሜት (sense of ownership) በመፍጠር ሥራዎችን በውጤታማነት ለመፈጸም የሚያደርጉት ጥረት ጥሩ ነው ማለት ይቻላል። የአካባቢንና የበላይ አካልን ዕቅድ መሠረት በማድረግ ተቋሙን መለወጥ የሚችል ተጨባጭ ዕቅድ የማዘጋጀት አቅሙ መሻሻሉንና በተዘጋጀው ዕቅድ ላይ ተመስርቶ ፈፃሚዎችና ባለድርሻ አካላትን የማዘጋጀት ክህሎቱ ተሻሽሏል። በተግባር አፈፃፀም ሂደት አመራሩና ባሙያው የትምህርት ተቋማትን ተከፋፍሎ ተጨባጭ ዕቅድ በመስጠትና አፈፃፀሙን በመከታተል ውጤታማ የሆኑ ተቋማትን ተሞክሮ ለማስፋት የማደረገው ጥረት በትምህርት አመራሮች መካከል ትልቅ ፉክክር መፍጠር ችሏል።
- የሪፓርትም ሆነ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓታችን የጥራት፣ የወቅታዊነትና የታዓማኒነት ሁኔታ በእጅጉ መሻሻል የታየበት ነው።

#### 2.5.1.2. የትምህርት ተሳትፎና ተደራሽነት

- የቅድመ መደበኛ ትምህርት በሁሉም የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች በመክፈት ዕድሜያቸው ከ 4-6 ዓመት የሆናቸውን ህፃናት ለማስተማር በተደረገው ጥረትና በተፈጠረው ንቅናቄ በርካታ ህፃናት ወደ ት/ቤት መግባት እንዲችሉና በትምህርት አቀባበላቸውም ላይ መሠረታዊ ለውጥ እንዲያመጡ አስችሏል።
- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነትን ለማስፋፋት በተደረጉ ርብርቦች በሁሉም ቀበሌዎች ቢያንስ አንድ ሙሉ ሳይክል ት/ቤት እንዲኖራቸው በመደረጉ ህፃናት 4 ኛ ክፍል ካጠናቀቁ በኋላ በት/ቤት ርቀት ምክንያት ትምህርት እንዳያቋርጡ ማድረግ ተችሏል።
- እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናትንና ነባር ተማሪዎች ትምህርት ከመጀመሩ በፊት መረጃን በጥራት የመለየት፣ የመመዝገብና ወደ ት/ቤት እንዲመጡ የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር የተማሪዎችን ምዝገባ በአጭር ቀናት የማጠናቀቅ አቅም መፍጠር ተችሏል። ይህ በመሆኑም የአዲስ ገቢ ተማሪዎች እና የመጀመሪያ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል /1ኛ-4ኛ/ በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ሽፋን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ ተችሏል።
- የአርሶ አደሩና የሴቶች አደረጃጀቶች ከት/ቤቶች ጋር ጠንካራ ትስስር በመፈጠራቸውና ወላጆችም በአደረጃጀቶቻቸው አማካይነት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ በመደረጉ በትምህርት ሥርዓት ውስጥ ትልቅ ማነቆ የነበሩት የተማሪዎች የማቋረጥና አዘውትሮ በትምህርት ገበታ ላይ ያለመገኘት ችግሮች በወሳኝ መጠን መቀነስ ተችሏል።
- የትምህርት ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በተደረገው ጥረት በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለው ምጥጥን በእጅጉ ማቀራረብ ከመቻሉም በላይ በ 2 ኛ ደረጃ ትምህርት (9-10 ኛ ክፍል) የሴቶች ድርሻ በልጦ ታይቷል። በገጠርና በከተማ መካከል ያለው ክፍተት አሁንም ትኩረት የሚሻ ቢሆንም አፈጻጸሙ በከፍተኛ ደረጃ መሻሻል አሳይቷል። በክልሉ የሚገኙ ብሔረሰቦች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት እንዲያገኙና በዚህ ረገድ የነበሩ የግብዓት ችግሮች ባለፉት ዓመታት የክልሉ መንግስት ሰፊ ትኩረት ሰጥቶ በመሥራቱ በሶስቱም ብሔረሰብ አስተዳደሮች እና በአርጎባ ልዩ ወረዳ የተሻለ ትምህርት ለመስጠት የሚያስችል አቅም መፍጠር ተችሏል።

### 2.5.1.3. የትምህርት ውስጣዊ ብቃትና ጥራት ማረጋገጥ ተግባራት

- በዘመኑ ለመምህራን፣ ር/መምህራንና ለሱፐርቫይዘሮች በርካታ ሥልጠናዎች በመሰጠታቸው መምህራንና የት/ቤት አመራሮች የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ተግባር በባለቤትነት ስሜት (sense of ownership) በውጤታማነት ለመፈጸም የሚያደርጉት ጥረት ጥሩ ነው ማለት ይቻላል።
- በየደረጃው የሚገኙ አመራሮች የአካባቢንና የበላይ አካልን ዕቅድ መሠረት በማድረግ ተቋሙን መለወጥ የሚችል ተጨባጭ ዕቅድ የማዘጋጀት አቅሙ መሻሻሉንና በተዘጋጀው ዕቅድ ላይ ተመስርቶ ፈፃሚዎችና ባለድርሻ አካላትን የማዘጋጀት ክህሎቱ ተሻሽሏል።
- ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት በተለይም ከህብረተሰቡ ጋር በተካሄደው የጋራ ጥረት በ 2013 በጀት ዓመት ብቻ የት/ቤቶችን ችግር ለመቅረፍ ከ 975 ሚሊዩን ብር በላይ የሚገመት በጉልበት፣በቁሣቁስና በገንዘብ አስተዋጽኦ በማድረግ የት/ቤቶችን ገፅታ ለመለወጥ ትልቅ ጥረት አድርጓል። የተማሪ ወላጅ ማህበርም የተማሪዎችን ተሳትፎ በማሳደግና አቋራጭን ከመከከል አኳያ ሰፊ ድርሻ ነበራቸው። መምህራን ማህበር አመራሩን እንደገና በማጠናከር በሴክተሩ በተለይም በመምህራንና በትምህርት አመራሮች የሚነሱትን የመልካም አስተዳደር ችግሮችን እየለዩ ከመንግስት ጋር በመሆን ለመፍታት የተደረገው ጥረት እንዲሁም የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥና በትምህርት ተቋማት ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሁኔታ እንዲሰፍን ተደርጓል።

- አዲስ ገቢ የአንደኛ ክፍል ተማሪዎችን ከ 3 ወር ባነሰ ጊዜ ማንበብ፣ መጻፍና ማስላት የማስቻል ሥራ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ በመሰራቱ አዲስ ገቢ ተማሪዎችን በየዓመቱ እስከ ታህሳስ 30 ድረስ ሦስቱንም ክህሎቶች ዙሪያ ተጨባጭ ለውጥ መኖሩ በገለልተኛ ተቋማት በተደረገው ጥናት ማረጋገጥ ተችሏል።
- በየዓመቱ ሁሉም ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች 50% እና በላይ ማምጣት አለባቸው ተብሎ ከመምህራን፣ ከትምህርት ባለሙያዎች፣ ከተማሪዎች፣ ከወላጆችና ከአመራሮች ጋር መግባባት ተፈጥሮ በተከታታይነት በተደረገው ርብርብ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ለፈተና ከተቀመጡት መካከል 50% እና በላይ ያስመዘገቡት 77.92% ከመሆኑ ጎን ለጎን የመሰናዶ ትምህርት አጠናቀው ወደ ዩኒቨርስቲ የገቡ ተማሪዎች ቁጥር በብዛት እንዲጨምር አስችሏል።
- በሀገር አቀፍ ደረጃ በተቀመጠው ስታንደርድ መሠረት መምህራንን ለየደረጃው ብቁ እንዲሆኑ ለማድረግ በቅድመ ሥራና በሥራ ላይ ሥልጠና በስፋት እንዲሰጥ በመደረጉ በ 2013 በጀት ዓመት በቅድመ መደበኛ 35.30%፣ ከ 1-8 ኛ ክፍል የሚያስተምሩ 7.10% መምህራን፣ በልዩ ፍላጎት 9.90% እና ከ 9 ኛ-12 ኛ ክፍል የሚያስተምሩ 11.20% ለደረጃው የተቀመጡውን ፕሮፋይል እንዲያሟሉ ተደርጓል።
- የክልላችን መንግስት ከ 96 ሚሊዩን ብር ያላነሰ በጀት በመመደብ መፃህፍትን በስፋት ማሳተም በመቻሉ የመፃህፍት አቅርቦት ከሞላ ጐደል 1 ለ 1 ማድረስ መቻሉ ሌላው ትልቅ ስኬት ተደርጐ ይወሰዳል።

#### 2.5.1.4. ሠላማዊ የመማር ማስተማር

- በትምህርት ተቋማት የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በቋሚነት በየዓመቱ እየተጠኑ መፍታት መቻሉና በ 2013 በጀት ዓመትም በክልል ደረጃ ከተለዩት 140 የመልካም አስተዳደር ችግሮች መካከል 104 ወይም 74.29% መፈታር መቻላቸው፣
- ተማሪዎች በክፍልና ከክፍል ውጪ በአደረጃጀቶቻቸው ንቁ ተሳተፎ በማድረግ በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ የሚታዩትን ችግሮች በባለቤትነት መፍታት መቻላቸው፣
- ት/ቤቶች ከወላጆችና ከልዩ ልዩ አደረጃጀቶች ጋር ጠንካራ ትስስር በመፍጠራቸው በበጀት ዓመቱ ከነበሩ መጠነኛ ችግሮች በቀሪው የበጀት ዓመት ሠላማዊ የመማር ማስተማር ሥራ ማከናወን ችለዋል።

### 2.5.2. ዋና ዋና ፈተናዎች (ማነቆዎች)

#### 2.5.2.1. ፍትሃዊ የትምህርት ተደራሽነትና ተሳትፎ

- የቅድመ መደበኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆኑ፣
- የ 2 ኛ ደረጃ ትምህርት ሽፋን/ተደራሽነት ከመካከለኛ ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ መሆኑ፣
- የተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ተሳትፎ ከቁጥር በዘለለ በተጨባጭ መሬት ላይ ወረዶ እንቅስቃሴውን ማግኘት አለመቻል፣
- በቅድመ መደበኛ፣ በመጀመሪያና 2 ኛ ደረጃ ትምህርት በገጠርና በከተማ የፍትህዊነት ክፍተት መኖሩ፣
- የልዩ ፍላጎት ትምህርት በሚፈለገው ደረጃ እየተስፋፋ አለመሆኑ፣

#### 2.5.2.2. የትምህርት ውስጣዊ ብቃትና ጥራት

- የተማሪዎች አዘውትሮ በትምህርት ገበታ ላይ አለመገኘት፣
- ትምህርት ማቋረጥና ክፍል መድገም /የትምህርት ብክነት/ ያልተሻገርነው ችግር መሆኑ፣
- በየደረጃው ያለው አመራር የሚያደርገው ክትትልና ድጋፍ መሬት የነካና ችግር የሚፈታ በመሆን በኩል ውስንነቶች መኖራቸውና ከአጠቃላይ ንግግር ተላቆ ሥራዎችን በዝርዝር እያወቁ በመምራትና በሂደትም አወንታዊ ተፅዕኖ እየፈጠሩ በመሄድ ረገድ ክፍተቶች መኖራቸው፣
- ምርጥ ተሞክሮዎችን የማስፋት ችግርና ተቋማትን ወደ ተቀራራቢ ደረጃ አለማድረስ፣
- አንዳንድ መምህራን በመማር ማስተማር ሂደትም መሠረታዊ የክህሎት ክፍተት ያለባቸው መሆኑ፣
- በወላጆች በኩል ልጆቹን ማስተማርና መከታተል የት/ቤቶችና የመምህራን ኃላፊነት ብቻ አድርጎ በመውሰድ የራስን ሚና አሳንሶ ማየት፣
- አንዳንድ ተማሪዎች ጊዜያቸውን በትምህርትና በጥናት ከማሳለፍ ይልቅ በአልባሌ ቦታ ማሳለፋቸውና የሥነምግባር ችግርም ያለባቸው መሆኑ፣
- አንዳንድ ር/መምህራንና የሱፐርቫይዘሮች በሥራ ገበታቸው ላይ ተረጋግቶ አለመስራት፣
- በት/ቤት አመራርነት የሴት ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆን፣
- በትምህርት ተቋማት የልዩ ልዩ ግብዓቶች አለመሟላት፣
- በሀገር አቀፍ ደረጃ ለት/ቤቶች የተቀመጠውን ስታንዳርድ ያሟሉ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ቁጥር አነስተኛ መሆኑ፣
- ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ዝግጅት ያላቸው መምህራን ቁጥር አነስተኛ መሆን፣
- በበርካታ 2 ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሴክሽን ተማሪ ጥምርታ ከስታንዳርዱ በላይ መሆኑ፣
- በሁሉም የትምህርት ደረጃ ተማሪዎች ለደረጃው የሚመጥን አጥጋቢ የመማር ብቃት ማምጣት አለመቻላቸው (በተለይም በሳይንስ፣ ሂሳብና እንግሊዝኛ ትምህርቶች) ፣
- የሥርዓተ ትምህርት ማቴሪያሎች ለማበልፀግ ጥናትና ምርምር በማካሄድና የሥርዓተ ትምህርት ማቴሪያሎችን በመገምገም በየደረጃው ያሉ መምህራን ተሳትፎ አናሳ መሆኑ፣
- የኮምፒዩተርና የኢንተርኔት አገልግሎትና ተደራሽነት የተሟላ ባለመሆኑ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ትምህርት አሳጣጥ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆኑ፣

## 2.5.3. ለቀጣይ እቅዳችን መነሻ የሚሆኑ ወሳኝ ጉዳዮች፣

በ 2013 የትምህርት ዘመን አመራሩ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ በየደረጃው የሚገኙ ፈጻሚ አካላትን አቅም ለመገንባት ባደረገው ርብርብ በትምህርት ጥራትና አግባብነት ላይ መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት የተቻለ ቢሆንም በዘመኑ ጥራት ያለው ትምህርት በፍትሃዊነት በማዛደረግ ረገድ በቀላሉ የማይታዩ እጥረቶች ተከስተዋል። በዚህም መሠረት በቀጣዩ የትምህርት ዘመን መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት ርብርብ የምናደርግባቸው ወሳኝ ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው።

### 2.5.3.1. ተቋማዊ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ማሣደግ፣

የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ በየደረጃው ያለውን አመራር፣ ባለሙያና መምህራንን አቅም አገልብቶ ማንቀሳቀስ በትምህርት ስራችን ወሳኝና ቁልፍ ጉዳይ ተደርጎ ተወስዷል። ከዚህ በተጨማሪ ትኩረት የተደረገባቸው ጉዳዮች የመረጃ ስርዓትና ፍሰት፣ ህጎችና የሥራ መመሪያዎች እና ለሥራ የሚያገለግሉ መሣሪያዎችና ፋሲሊቲዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸው አቅም በፈቀደ መጠን ማሟላት ይሆናል።

## 2.5.3.2. የትምህርት ጥራትና ተገቢነት ማረጋገጥ፣

የትምህርት ስርዓታችን አንዱ ችግር በየደረጃው የሚሰጠው ትምህርት ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን አለመቻል በመሆኑ የተማሪዎችን ውጤትና ስነምግባር በማሻሻል በትምህርት ጥራት ላይ መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት ወሳኝ ጉዳይ ነው። የትምህርት ጥራት የማረጋገጥ ጉዳይ ብቁ ዜጋ የመፍጠር ጉዳይ ስለሆነ በትምህርት ስራችን ውስጥ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በልዩ ትኩረት መፈጸም ያለበት ስለሆነ በቀጣይ 2014 የትምህርት ዘመን የትምህርት ጥራትን ማሻሻል ወሳኝ የትኩረት መስክ ሆኖ ይተገበራል።

## 2.5.3.3. የትምህርትን ተሳትፎና ተደራሽነት ማስፋት፣

ምንም እንኳን የትምህርት ተደራሽነትን ለማስፋት ሰፊ ስራ የተሰራ ቢሆንም የትምህርት ሽፋናችን የሚፈለገው ደረጃ ላይ ያልደረሰ በመሆኑ የዘላቂ የልማት ግቦችን ሆነ ትምህርት ለሁሉም ግብ መምታታችንን አጠራጣሪ አድርጎታል። በተለይም ከቅድመ መደበኛ ትምህርት፣የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛው ሳይክል፣ ከሁለተኛ ደረጃ እና ከተግባር ተኮር መሠረታዊ ትምህርት አቅርቦትና ተደራሽነት አንፃር ሰፊ ስራ መስራት ያስፈልጋል። ስለሆነም መላ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍና በማንቃንቅ በየደረጃው ያለውን የትምህርት ተደራሽነት ችግር መፍታት አንድ ወሳኝ ጉዳይ ነው።

## 2.5.3.4. መልካም አስተዳደርና ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሁኔታ በትምህርት ተቋማት ማረጋገጥ፣

የትምህርት መዋቅሩ ኪራይ ሰብሳቢነትን ለማዳከምና ልማታዊነትን ለማጠናከር የምንሰራውን ሥራ ለሀገራችንን የፖለቲካ ኢኮኖሚ ትግል ትልቅ አስተዋጽኦ ስለአለው በትምህርት ተቋማት እንዲሁም በትምህርት ማህበረሰቡ ዙሪያ መልካም አስተዳደርን በማስፈንና ኪራይሰብሳቢነትን የመታገል እንዲሁም ማነቆዎችን የመፍታት ሥራ አንዱ ወሳኝ ጉዳይ ሆኖ የሚፈፀም ይሆናል።ከዚህ አኳያ በየደረጃው ያለው ባለሙያና በተለይም መምህራን፣ ር/መምህራንና ሱፐርቪዘሮች የሚያነሷቸውን የመልካም አስተዳደር ችግሮች በጥናት እየለዩ ዘላቂ የመፍትሄ ርምጃ በመውሰድ ሁሉም አካል ለትምህርት ስራው ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራ ምቹ ሁኔታ መፍጠር እንደ አንድ ወሳኝ ተግባር ተወስዶ ሊተገበር ይገባል።

## 2.5.3.5. የትምህርት ግብአቶችን በስታንደርዱ መሠረት ማሟላት፣

የትምህርት ጥራትና አግባብነት ማረጋገጥ የሚቻለው በስታንዳርዱ መሠረት ግብአት ማሟላት ስንችል ነው። በዚህ መሠረት በደረጃም ሆነ በተግባር ብቁ የሆኑ መምህራን፣ ት/ቤቶችና ሌሎች ፓኬጆችንና ስትራቴጂዎችን ፕሮግራሞችን ለመፈፀም የሚያስችሉ ወሣኝ ግብአቶችን ማሟላት ይገባል።

# 3. የእቅዱ ዓላማ፣ ግቦችና ዒላማዎች፣

## 3.1. ዓላማ፣

- በሁሉም ተቋማት የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር ብቃትና ጥራቱ የተረጋገጠ ትምህርት በፍትሃዊነት ለዜጎች ማድረስ፡፡

## 3.2. ግቦች፣

### 3.2.1. ተቋማዊ የመፈፀም አቅም በማጎልበት በዘመኑ የታቀዱ ተግባራት በብቃትና በውጤታማነት መፈፀማቸውን ማረጋገጥ፡፡

ዒላማና መለኪያዎች፣

- ከክልል እስከ ትምህርት ተቋማት በሁሉም ደረጃ የየተቋሙን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ የ 2014 ዓ.ም. የንቅናቄ ዕቅድ በጥራት አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ፡፡

- በ 2014 ዓ.ም. የንቅናቄ ዕቅዳችን ላይ ግልጽነትና የተሟላ መግባባት ለመፍጠር በክልል እስከ በወረዳ ያሉ ፈጻሚዎችና አመራሮች በትምህርት ቤት ደረጃ ሁሉም መምህራን፣ከ 5 ኛ ክፍል በላይ ያሉ ተማሪዎች፣ ወላጆችና ነዋሪዎችን በማሳተፍ በአጠቃላይ በ 2014 ዓ.ም የትምህርት ዕቅድ ላይ ኦሬንቴሽን መስጠት።
- የትምህርት አመራሩንና ባለሙያውን የመፈፀም አቅም የሚያጎለብቱ አጫጭር ስልጠና ለሁሉም ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች፣ለወረዳና ለዞን አመራሮች መስጠት።
- ልዩ ልዩ ስትራቴጂዎች፣ መመሪዎች፣ ማኑዋሎች ማዘጋጀትና ማሻሻል።
- መረጃን መሠረት ያደረገ እቅድ አዘገጃጀትና ውሣኔ አሰጣጥ አፈፃፀም በሁሉም ት/ቤቶች ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፣
- በየደረጃው በሚገኙ የትምህርት ተቋማት (ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ) ያሉ ሠራተኞች የሚታይባቸውን የክህሎት ክፍተት ሊሞላ የሚችል ግለ ሙያዊ ማሻሻያ ዕቅድ (self professional development plan) አዘጋጅተው እንዲተገብሩ ማድረግ፣
- በየደረጃው የተደራጀና ውጤታማ የሆኑ የተማሪ ወላጆች ማህበር 100% ማድረስ፣
- ለ 2014 የትምህርት ዘመን አገልግሎት የሚሰጡ የትምህርት ግብዓቶችን በሁሉም አካላት ርብርብ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ትምህርት ቤት እንዲደርሱ ማድረግ።
- ለ 2014 ዓ.ም. የሚያስፈልጉ ለየደረጃው የሰለጠኑ መምህራንን ቀጥሮ በሁሉም ትምህርት ቤቶች 100% የተሟላ መምህር እንዲኖር ማድረግ።
- ለ 2014 ዓ.ም. የትምህርት ቤቶች የነፍስ ወከፍ በጀት 100% በማስመደብ ስራ ላይ እንዲውል ማድረግ።
- የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ መልካም ተሞክሮዎችን በኤሌክትሮኒክስና ህትመት ሚዲያዎች አማካኝነት ማስፋት፣

### 3.2.2. በአደጋ ጊዜ ትምህርትን ማስቀጠል አሰራርና አደረጃጀት ስርዓት የበለጠ ማጠናከር፣

ዒላማና መለኪያዎች

- ሁሉም ት/ቤቶች በኮቪድ-19 ለመከላከል ሊደረጉ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች የወጡትን መመሪያዎችና ፕሮቶኮሎች 100% ተግባራዊ ማድረግ፣
- በግጭት እና ወሪራ ምክንያት ሙሉ በሙሉ እና በከፊል የወደሙ የትምህርት ተቋማት መልሶ በማስተካከል መማር ማስተማር የጀመሩ ት/ቤቶች 100% ማድረስ፣

### 3.2.3. የአጠቃላይ ትምህርት ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ዒላማና መለኪያዎች

- በመልካም እሴቶች የታነፁ፤ በሁለንተናዊ ስብእና የተገነቡ ዜጎችን በማፍራት ረገድ፣
  - በመምህራንና በተማሪዎች ስነ ምግባር የረኩ የህብረተሰብ ክፍሎች 100% መሆኑን ማረጋገጥ፣
  - የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጡ መምህራንና ተማሪዎች ከ 0.07% ወደ 30% ማድረስ፣
  - የት/ቤት ህገ ደንብ የሚተገብሩ መምህራንና ተማሪዎች ብዛት 100% ማድረስ፣
  - ሁሉም ተማሪዎች በልዩ ልዩ ተጓዳኝ ክበባት መሣተፋቸውን ማረጋገጥ፣
- በክፍል ፈተናዎችና ተከታታይ ምዘናዎች ሁሉም ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች 50% እና በላይ፣ 35% የሚሆኑ ተማሪዎች ከ 75% በላይ እና 15% የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ ከ 85% እንዲያመጡ ማድረግ፤

- ❖ በክልላዊ የትምህርት ቅበላ ምዘና በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች 50% እና በላይ የሚያስመዘግቡ ተማሪዎች ብዛት 90% እንዲሁም 75% እና በላይ የሚያመጡ ደግሞ 50% ማድረስ፣
- ❖ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ክልላዊ ፈተና (8ኛ ክፍል) የተማሪዎችን ውጤት በማሻሻል 50% እና በላይ የሚያመጡ ተማሪዎች በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 71.92 በመቶ በ2014 ዓ.ም 84.05% በመቶ እንዲደርሱ ማድረግ፣
- ❖ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 12ኛ ክፍል አጠናቀው የዩንቨርስቲ መግቢያ ፈተና ከሚወስዱት ውስጥ ወደ ዩኒቨርስቲ የሚገቡ በ2012 ትምህርት ዘመን ከነበረው 66.6% ወደ 67% ማሳደግ፣
- ❖ አዲስ የገቡ የአንደኛ ክፍል ሁሉም ተማሪዎች ታህሳስ 30 ማንበብ መጻፍና ማስላት እንዲችሉ ማድረግ፣
- ❖ ሁሉም የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋን በብቃት መናገር፣ ማንበብና መፃፍ ብቃት እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- ❖ ለ1ኛ፣4ኛ፣6ኛ ፣8ኛ 12ኛ ክፍሎች ልዩ ትኩረት በመሥጠት ተማሪዎችን ማብቃት።
- ❖ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በተለይም ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት፣ ከ5ኛ ክፍል ጀምሮ እስከ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ድረስ ባሉት የክፍል ደረጃዎች ደግሞ ለእንግሊዝኛ ቋንቋ፣ ለሳይንስ እና ሂሳብ ትምህርቶች ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ተማሪዎችን ማብቃት።
- ❖ በሁሉም የትምህርት ደረጃ የመድገም ምጣኔን ወደ 2% ዝቅ ማድረግ፣
- ❖ ለየደረጃው የሚመጥኑና የተሟላ ስልጠና የወሰዱ ብቁ የት/ቤት አመራሮች በመመደብ የትምህርቱን ጥራት ማሻሻል
  - በመጀመሪያ ደረጃ ር/መምህር በመጀመሪያ ዲግሪ ከ63.3% ወደ 79.61% ማድረስ፣
  - በሁለተኛ ደረጃ ር/መምህር በሁለተኛ ዲግሪ ከ53.1% ወደ 72.12% ማድረስ፣
  - በመጀመሪያ ደረጃ ጉድኝት ሱፐርቫይዘር በመጀመሪያ ዲግሪ ከ94.5% ወደ 95.68% ማድረስ፣
  - በሁለተኛ ደረጃ ጉድኝት ሱፐርሀበይዘር በማስተርስ ዲግሪ ከ86.7% ወደ 90.18% ማድረስ፣
- ❖ ለየደረጃው የሚመጥኑና የተሟላ ስልጠና የወሰዱ ብቁ መምህራንን በመመደብ የትምህርቱን ጥራት ማሻሻል
  - የቅድመ መደበኛ በዲፕሎማ ብዛት ከ35.30% ወደ 49.73% ማድረስ፣
  - ከ1-8 ክፍሎች በመጀመሪያ ዲግሪ ብዛት ከ7.10% ወደ 26.76% ማድረስ፣
  - በልዩ ፍላጎት በመጀመሪያ ዲግሪ ብዛት ከ9.90% ወደ 25.95% ማድረስ፣
  - ከ9-12 ክፍሎች በሁለተኛ ዲግሪ ከ11.20% ወደ 27.68 በመቶ ማድረስ፣
- ❖ የተማሪ ክፍል ጥምርታን በስታንዳርዱ መሰረት ማስተካከል
  - ➢ አንደኛ ደረጃ ከ1-8ኛ ክፍል- 50 ተማሪ በአንድ ክፍል ማስተማር
  - ➢ ሁለተኛ ደረጃ 40 ተማሪ በአንድ ክፍል ማስተማር
- ❖ በክልላችን ከሚገኙት ት/ቤቶች መካከል 40 በመቶ ቅደመ መደበኛ፣ 20 በመቶ የመጀመሪያ ደረጃና 20 በመቶ ሁለተኛ ደረጃ የውጭ ጥራት ኦዲት ማድረግ፣
- ❖ 30 በመቶ የሚሆኑ በመለስተኛና በመምህር ደረጃ ለሚገኙ መምህራን የጹሁፍ ምዘና መስጠት፣በ2014 ዓ.ም ለሚመረቁ 5500 የዲፕሎማ መምህራን የብቃት ምዘና መመዘን፣
- ❖ በፈጠራ ስራ እውቅና የተሰጣቸው መምህራንና ተማሪዎች እንደቅደምተከተላቸው 5 በመቶና 15 በመቶ ማድረስ።
- ❖ በዲጂታል ቴክኖሎጂ ተደገፈው የተካሄዱ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች በተመለከተ

- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ምዘና ስርዓቶችና ሀገር አቀፍ ፈተናዎች በመቶኛ 100% ማድረስ፣
- የአቅም ግንባታ ስልጠና ተጠቃሚ የሆኑ መምህራኖች ድርሻ በመቶኛ በ 2014 በጀት ዓመት 50% ማድረስ፣
- የትምህርት ታብሌት ተጠቃሚ የሆኑ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ብዛት 100% ማድረስ፣
- በጥራትና በወቅቱ የተሰበበሰበ፣ የተተነተነና ጥቅም ላይ የዋለ የትምህርት አስተዳደር መረጃ ስርዓት 100% ማድረስ፣
- የልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን ዲጂታል ቴክኖሎጂን በመጠቀም መድረስ የቻሉ በየደረጃው ያሉ ተቋማት (9-12 ክፍል) 100% ማድረስ፡

❖ የተማሪ መማሪያ መጽሃፍ በሁሉም ደረጃና በሁሉም የትምህርት ዓይነት 1፡1 ማድረስ፣

### 3.2.4. የትምህርት ተደራሽነትና ፍትሃዊነትን ማረጋገጥ፣

ዒላማዎችና መለኪያዎች፣

- ቅድመ መደበኛ ትምህርትን በሁሉም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲሰጥ በማድረግ ሽፋኑን አሁን ካለበት 35.24% በ 2014 የትምህርት ዘመን 49.77% ማድረስ፣
- በ 2014 ዕድሜያቸው 7 ዓመት የሞላቸው 691,059 ህፃናትን ሙሉ በሙሉ 1 ኛ ክፍል እንዲገቡ በማድረግ የአንደኛ ክፍል አዲስ ገቢ ንጥር ቅበላ ምጣኔውን 100% ማድረስ።
- በ 2014 አዲስ የአንደኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት 760,165 ህፃናትን ትምህርታቸውን እንዲማሩ በማድረግ ጥቅል የአንደኛ ደረጃ አዲስ ገቢ ተማሪዎች ቅበላ ምጣኔ 110% ማድረስ።
- በ 2014 ዕድሜያቸው 7 ዓመት የሞላቸው 691,059 ህፃናትን፣ 86,058 በተለያዩ ምክንያቶች አቋርጠው የቆዩ፣ በ 2013 ከ 1-7 ኛ የተማሩ ነባር 3,194,789 ተማሪዎችን በድምሩ 3,971,906 ተማሪዎችን በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች መዝግቦ በማስተማር በ 2013 የትምህርት ዘመን ----% የነበረውን ንጥር የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎው ወደ 77.26%፣ እንዲሁም በ 2013 ዓ/ም 75.36% የነበረውን ጥቅል የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎውን 87.06% ማድረስ፣
- ከ 8 ኛ ክፍል ወደ 9 ኛ ክፍል የተዛወሩትን በሙሉ እንዲሁም ነባር ተማሪዎችንና በተለያዩ ምክንያቶች አቋርጠው የቆዩትን ሙሉ በሙሉ በማስገባት በ 2 ኛ ደረጃ ት/ቤቶች (ከ 9-12 ኛ ክፍል) በድምሩ 1,106,678 ተማሪዎችን በማስተማር በ 2013 የትምህርት ዘመን 38.40% የነበረውን ጥቅል የትምህርት ተሳትፎውን በ 2014 ዓ/ም 43.04% ማድረስ፣
- የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርትን በሁሉም ቀበሌዎች በማስፋፋት እድሚያቸው ከ 15-64 ዓመት ከሆናቸው መካከል 7,017,213 ጎልማሶች ከማይምንት ነፃ እንዲወጡ በማድረግ በ 2009 ዓ/ም 47.39% (5,187,484) የነበረውን የክልሉን ማንበብና መፃፍ ምጣኔ /litracy Rate/ በ 2014 መጨረሻ ወደ 7,017,213 (54.72 በመቶ) ማሳደግ።
- በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች የሚታየውን የጾታ ተሳትፎ ክፍተት በማጥበብ በሁሉም ደረጃ የፆታ ክፍተትን ወደ 1.00 ማድረስ።

- የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሽፋንን በማሳደግ በ 2013 የትምህርት ዘመን በጥቅል የትምህርት ተሣትፎ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም 1.91% የነበረውን ወደ 3.66%፣ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ከ 0.33 በመቶ ወደ 0.55 በመቶ ማድረስ፣
- በሁሉም ደረጃዎች የተማሪ ማቋረጥ ምጣኔን ወደ 2% ዝቅ ማድረግ፣

### 3.2.5. የትምህርት ቤቶችን መሰረተ ልማትና ግብዓት ችግሮችን በመፍታት ቢያንስ 75% የሚሆኑትን ትምህርት ቤቶች የተቀመጠውን ትምህርት ቤቶች ደረጃ ስታንዳርድ እንዲያሟሉ ማድረግ።

ዒላማዎችና መለኪያዎች፣

- የትምህርት ቤቶችን መሰረተ ልማትና ግብዓት ችግሮችን በመፍታት ቢያንስ 75% የሚሆኑትን ትምህርት ቤቶች የተቀመጠውን ትምህርት ቤቶች ደረጃ ስታንዳርድ እንዲያሟሉ ማድረግ።
- ግንባታቸው የተጀመሩ -- የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን በትምህርት ዘመኑ ማጠናቀቅ፣
- በሁሉም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በእያንዳንዱ 25 ኮምፒውተር ያለው ወርክሾፕ ማደራጀት፣/ በመንግስትን በህብረተሰቡ ትብብር/፣
- የተማሪ መቀመጫን በተመለከተ ሁሉም ተማሪ መቀመጫ ወንበር እንዲኖረው በማድረግ በአንድ አግዳሚ ሁለት ተማሪ እንዲቀመጥ ማድረግ፣
- በሁሉም የትምህርት ተቋማት የወንድና የሴት መጸዳጃ ቤት በማዘጋጀት አገልግሎቱን አሁን ካለበት 87.57 በመቶ (1ኛ ደረጃ 86.91%፣ 2ኛ ደረጃ 97.40%) ወደ 86.37% (1ኛ ደረጃ 85.58%፣ 2ኛ ደረጃ 98.11%) ማሳደግ፣
- የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦቱን በማሻሻል አሁን ካለበት 47.69% (1ኛ ደረጃ 45.62%፣ 2ኛ ደረጃ 77.56%) ወደ 56.90% (1ኛ ደረጃ 55.40%፣ 2ኛ ደረጃ 79.09%) በማሳደግ ትምህርት ቤቶች የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- በክልላችን ካሉ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች መካከል ከኢንስፔክሽን ስታንዳርድ አኳያ 31.24% (29.36% ደረጃ 3 እና 1.88% ደረጃ አራት) ማድረስ፣ እንዲሁም በ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች 33.65% (29.89% ደረጃ 3 እና 3.76% ደረጃ አራት) ማድረስ።

### 3.2.6. በትምህርት መዋቅሩ መልካም አስተዳደርን በማስፈን ልማታዊ አስተሣሠብን ማስረጽ፣ ሰላማዊ የመማር ሁኔታን ማረጋገጥ፣

ዒላማዎችና መለኪያዎች፣

- በየደረጃው የሚታዩ የመልካም አስተደደር ችግሮችንና ምንጮቻቸውን በጥናት መለየትና የመፍትሔ አቅጣጫ አስቀምጦ መተግበር።
- የግልጽነት፣ የተጠያቂነትና አሣታፊነትን የሚያሰፍን አሠራር ተግባራዊ ማድረግ፣1
- በአፈጻጸም ግልጽ ያልሆነ የአሠራር መመሪያና ማንዋሎችን ከልሶ በጥራት ማዘጋጀት።
- በየደረጃው ባለው ተቋም ያሉ ሁሉም ፈፃሚዎች ከዕቅድ አወጣጥ እስከ ግምገማ ባለው ሂደት የተሟላ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ።

- ሙስናን፣ አድልኦና ብልሹ አሠራርን መከላከልና በጥብቅ መታገል፡፡
- የአገልግሎት አሠጣጥ ሥርዓቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ፡፡-
  - በዞን፣ በወረዳና በትምህርት ተቋማት የዜጐች ቻርተር አዘጋጅቶ ባለድርሻ አካላት እንዲያውቁት ማድረግ፡፡
  - በተቀመጠው የአገልግሎት አሠጣጥ ስታንዳርድ መሠረት ለዜጐች አገልግሎት መስጠት፡፡
  - በሁሉም ደረጃ የሥራ ውጤታማነትን በማምጣት የዜጐችን አመኔታና እርካታ ማሳደግ፡፡
  - በየትምህርት ተቋማት ሠላማዊ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲፈጠር ማድረግ፡፡
- የትምህርት ሃብትን በውጤታማነት መጠቀም
  - የፕሮግራም በጀትን በውጤታማነት መጠቀም
  - የካይዘን አሰራርን ተግባራዊ ማድረግ

# 4. የዕቅድ ዓላማና ግቦቹን ለማሣካት የሚከናወኑ ተግባራት፣

ዓላማና ግቦቹን ለማሣካት የሚከናወኑ ተግባራት (ሀ) የትምህርት ጥራትን ማሻሻል፣ (ለ) የትምህርት ተሣትፎና ፍትሃዊነትን ማሣደግ፣ (ሐ) የትምህርት ቤቶችን መሰረተ ልማትና ግብዓት ችግሮችን በመፍታት ትምህርት ቤቶችን ለመማር ማስተማር ስራ ምቹ እንዲሆኑ ማድረግ/የትምህርት ፋሲሊቲዎችን ማሟላት/፣ እና (መ) በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ መልካም አስተዳደር ማስፈን ናቸው፡፡ እነዚህ ተግባራት በሦስት ምዕራፎች ተከፋፍለው የሚፈፀሙ ሆነው ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 4.1. የዝግጅት ምዕራፍ ተግባራት አፈፃፀም

ከትምህርት ሥራ ባህሪ አኳያ የዝግጅት ምዕራፍ ብለን የምንጠራው ከሃምሌ 1/2013 ጀምሮ እስከ መስከረም 30/2014 ዓ.ም. ድረስ ያለውን ወቅት ነው፡፡ የዝግጅት ምዕራፍ በዋናነት አምስት መሠረታዊ ተግባራትን በብቃት መፈፀምን ይጠይቃል፡፡ እነዚህም ጥራት ያለው የተሟላ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ በዕቅዱ ላይ ፈጻሚዎችን ዝግጁ ማድረግ፣ የማደራጀት ስራ መስራት፣ ግብአቶችን ማቅረብ እና የተማሪዎችን ምዝገባ ማጠናቀቅ ናቸው፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ከትምህርት ዘርፍ ልዩ ባህሪ አኳያ ቀዳሚው ስራ የእቅድ አፈፃፀምን በመገምገም ለአዲሱ አመት ዕቅድ ዝግጅት በትምህርትነት የሚወሠዱ ጉዳዮችን ለይቶ ጥቅም ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ የ 2013 ዓ.ም. በየደረጃው የተካሄዱ የማጠቃለያ መድረኮች እዛው ሣሉ የ 2014 ዓ.ም. የቅድመ ዝግጅት ሥራ አካል ተደርገው ተወስደዋል፡፡ ከዚህ ሁኔታ በመነሳት በዕቅድ አፈፃፀም ዘመኑ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን ለይቶ መቀመርና በቀጣይ ለትግበራ ዝግጁ ማድረግ የቅድመ ዝግጅት ሥራውን የተሣካ ለማድረግ አይነተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ በዚህ መሠረት በቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ የሚከተሉት ዝርዝር ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

### 4.1.1. ተግባር አንድ:- የ 2013 እቅድ አፈፃፀምን በየደረጃው በመገምገም ለ 2014 ዓ.ም. ዕቅድ በትምህርትነት የሚወሠዱ ጉዳዮችን መለየትና ጥቅም ላይ ማዋል፣

ይህ ተግባር ለ 2013 የማጠቃለያ ምዕራፍ የግምገማ መድረኮች አፈጻጸም የተቀመጡ ስልቶችና አቅጣጫዎች መሰረት የሚፈጸም ይሆናል።

### 4.1.2. ተግባር ሁለት :- ጥራት ያለው የተሟላ ዕቅድ ማዘጋጀት

በየደረጃው ካለው አመራር ከሚጠበቁ ተግባራት አንዱ ጥራት ያለው የተሟላ ዕቅድ ማዘጋጀት ነው። ዕቅዱ ጥራት ያለውና የተሟላ ነው ሲባል በአንድ በኩል ዕቅዱ መነሻ የሚያደርጋቸውን ሁኔታዎች ጥልቀት ባለው ግምገማና በበቂ ትንተና ላይ ተመስርቶ ችግሮችን መለየት ሲሆን በሌላ በኩል ችግሮችን መፍታት የሚያስችሉ ቁልፍና አበይት ተግባራትን ለይቶ ማቀድ ነው። ከዚህ አኳያ ትምህርት ቢሮ የ 2014 ዓ.ም. ዕቅድ አምስት መሠረታዊ ሁኔታዎችን በመነሻነት ወስዷል። የመጀመሪያው የትምህርት ስልጠና ረቂቅ ህግ፣ ፖሊሲ እና ስትራቴጂዎች ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የ 2013 ዓ.ም የዕቅድ አፈፃፀም ነው። ሦስተኛው መነሻ በትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ የሕዝብ አስተያየቶች ሲሆኑ አራተኛው ደግሞ በክልልና በፌደራል ደረጃ የተዘጋጀው የአስር ዓመት ዕቅድ ነው። በመጨረሻም የድህረ 2015 ዘላቂ የልማት ግቦች እንደ ስድስተኛ መነሻ ሆኖ ተወስዷል።

በዚህም መሠረት በክልል ደረጃ የተዘጋጀውን ዕቅድ መነሻ በማድረግ በዞን፣ በወረዳና በትምህርት ተቋማት ደረጃ ከራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም፣ የሚያሰራና የተለጠጠ ግቦች ያሉት ዕቅድ ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል።

### 4.1.3. ተግባር ሶስት:- ፈጻሚንና ባለድርሻ አካላትን የማዘጋጀት ሥራ በብቃት መፈፀም፣

ፈጻሚንና ባለድርሻ አካላትን በብቃት የማዘጋጀት ተግባር በዋናነት በሁለት አጀንዳዎች ላይ ተመስርቶ ይከሄዳል። አንደኛው አጀንዳ የ 2014 ዓ.ም. የክልሉ የትምህርት የንቅናቄ ዕቅድ ሲሆን ሁለተኛው አጀንዳ በ 2014 ዓ.ም. በተለየ ሁኔታ ልንፈጽመው የሚገባን የተማሪዎች ምዝገባ አፈጻጸምን በተመለከተ በተዘጋጀው የግምገማ ሰነድ ነው። ከእነዚህ በተጨማሪ ባለፉት ዓመታት እንደተደረገው የትምህርት ቤቶችን ሰላማዊ የመማር ማስተማር ከማስከበር አኳያና ሌሎች ጠቃሚ አጀንዳዎችን በማዘጋጀት ከክልል እስከ ትምህርት ተቋማት ያለው ፈጻሚ፣ አመራሩና ባለድርሻ አካላት የጋራ መግባባት በመፍጠር ለዕቅዱ መፈጸም ክልላዊ ንቅናቄ የመፍጠር ጉዳይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ሊተገበር ይገባል። በዚህም መሰረት ከዚህ በታች የቀረቡት ዝርዝር ተግባራትን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ነው።

- የ 2014 ዓ.ም ዕቅድ ላይ በመጀመሪያ በትምህርት መዋቅሩ ያለው አመራር መድረክ በየደረጃው በመፍጠር በዕቅዱ ላይ ግልጽነትና መግባባት መፍጠር፣ዕቅዱንም ማዳበር፣
- ከአመራሩ መድረክ ቀጥሎ በየደረጃው ያለው ባለሙያ በተሟላ ሁኔታ የሚሳተፍበት መድረክ በማዘጋጀት በዕቅዱ ላይ የተሟላ ግልጽነት በመፍጠር በየዳይሬክቶሬቱ፣ ቡድንና በባለሙያ ደረጃ ከተግባርና ሃላፊነቱ አኳያ ድርሻውን እንዲወስድና እስከ ግለሰብ አውርዶ ማቀድ ይገባል።

- በእቅዱ ላይ የባለድርሻ አካላት በቂ ግንዛቤ ጨብጦ በትግበራ ሂደት የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርግ የሚያስችለው የውይይት መድረክ መፍጠር፣ በተለይም በትምህርት ቤት ደረጃ ወላጆችና መላው ህብረተሰብ በ 2014 የትምህርት ቤቱ ዕቅድ ላይ በዝርዝር ተወያይቶ መግባባት መፍጠር አለበት። ተግባሩም ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት በብቃት መፈጸም ይኖርበታል።

- ከላይ በዝርዝር የቀረቡት ባለድርሻ አካላት ከላይ በተቀመጠው መሰረት ከተልዕኮአቸው አኳያ በተፈጠሩላቸው መድረኮች ከተፈጸሙ በኋላ ሁሉንም ሠራተኛ ያሳተፈ የንቅናቄ መድረክ ከክልል እስከ ትምህርት ቤት ድረስ መፈጠር አለበት። የንቅናቄ መድረኩ እንደየደረጃውና አካባቢው የተለያየ ገጽታ ሊኖረው እንደሚችል ታሳቢ ቢደረግም በክልል ደረጃ ክልላዊ የትምህርት ጉባኤ በሚል የህዝብ ክንፉንና አመራሩን በሰፋት የሚያሳትፍ ክልላዊ መድረክ እንዲሆን ይደረጋል። በዚህ መድረክ የሚሳተፉ አካላትና የጉባዔው አጀንዳዎች በራሱ የተለየ ዕቅድ የሚመለስ ይሆናል።

- በየደረጃው የሚደረጉ መድረኮች በዋናነት የበላይ አካሉ የበታች አካላትን ለመደገፍና በዕቅዶች ዙሪያ የጋራ መግባባት መፍጠር በሚያስችሉ አግባቦች መፈጸም ይኖርበታል። በዚህም መሰረት ክልሉ ትምህርት ቢሮ የዞንና የወረዳ አመራሩ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮችን በሚያሳትፍ አግባብ መድረኩ እንዲመቻች መደረግ አለበት። በዞንም በተመሳሳይ ሁኔታ የሚፈጸም ሲሆን በወረዳ ደረጃ የወረዳ ፈጻሚውንና የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሚያሳትፍ መሆን ይኖርበታል። በትምህርት ተቋማት ደረጃ ሁሉንም መምህራን፣ ተማሪዎችና የአካባቢውን ህብረተሰብ በተሟላ ሁኔታ የሚያሳትፉ የንቅናቄ መድረኮች ሊሆኑ ይገባል።

### 4.1.4. ተግባር አራት፡- አደረጃጀቶችን መፍጠርና ማጠናከር፣

በቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ ወቅት ከሚከናወኑ ወሣኝ ተግባራት አንዱ ዕቅዱን በንቅናቄ ለማስፈፀም የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠርና ከተልዕኮአቸው አኳያ የአሠራር ግልጽነት መፍጠር ነው። በዚህም መሠረት ከቢሮ እስከ ትምህርት ተቋማት ያለው ሀይል በሚከተለው ሁኔታ ተደራጅቶ ወደ ተግባር እንዲገባ ይደረጋል።

#### 4.1.4.1. የድርጅት ዘርፍ አደረጃጀቱን ማጠናከር፣

የድርጅት ዘርፍ አደረጃጀት የሚያካትታቸው አካላት ከክልል እስከ ወረዳ ባለው መዋቅር በየደረጃው ያለው አመራር፣ በቡድን መሪና በባለሙያ ደረጃ ያሉ የድርጅት አባላት ሲሆኑ በትምህርት ቤት ደረጃ የድርጅት ክንፍ ውስጥ በአደረጃጀት የሚታቀፉ አካላት ርዕሰ መምህራንና ም/ር/መምህራን፣ ሱፐርቫይዘሮች፣ አባል መምህራንና አባል ተማሪዎች ናቸው። እነዚህ አካላት ተንቀሳቅሰው የትምህርት ስርዓቱን የመምራት ሃላፊነት ያለባቸው ስለሆነ በህዋስና በመሰረታዊ ድርጅት ማደራጀት ያስፈልጋል። አደረጃጀታቸው ካላቸው ተልዕኮ አኳያ በመለየት መምህራንና ተማሪዎችን በየራሳቸው አደረጃጀት ማደራጀት ተገቢ ነው።

#### 4.1.4.2. መንግስታዊ አደረጃጀቶችን ማጠናከር፣

መንግስታዊ አደረጃጀት ተብለው የተለዩ አካላት በክልል ደረጃ ዳይሬክተሮች እና በዞንና በወረዳ ደረጃ ደግሞ የቡድን መሪዎች እንዲሁም በየደረጃው የሚገኙ ባለሙያዎች ናቸው። በትምህርት ቤት ደረጃ ከእነዚህ አደረጃጀቶች በተጨማሪ መምህራንና አመቻቾችን አካቶ መደራጀት ይኖርበታል። እነዚህን ሃይሎች በትምህርት ስራ ውስጥ ካላቸው ተልዕኮ አኳያ በተለያየ አግባብ ሊደራጁ ይገባል። ዝርዝሩ ትምህርት ቢሮው የተላከው አደረጃጀት መመሪያ ማየት ተገቢ ነው።

#### 4.1.4.3. የባለድርሻ አካላት አደረጃጀት

በክልል ደረጃ ባለድርሻ አካላት የሚባሉት የወጣቶች ማህበር፣ የሴቶች ማህበር፣መምህራን ማህበር፣ በትምህርት ዘርፍ ላይ የሚሰሩ መያዶችና ባለሃብቶች፣ የግል ት/ቤት ማህበር፣ አልማን የሚያጠቃልል ነው፡፡

በክልል ያለው አደረጃጀት በዞንና በወረዳ ደረጃ ከነባራዊ ሁኔታው ጋር በሚመጥን መንገድ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡ በትምህርት ተቋማት ደረጃ የባለድርሻ አካላት አደረጃጀቶች ክልሉ ላይ የተለዩት የወጣቶች፣ የሴቶችና የመምህራን ማህበራት እንዲሁም የአርሶ አደሩ አደረጃጀቶች ይሆናሉ፡፡ በተጨማሪም በትምህርት ቤት ደረጃ ዋናው የባለድርሻ አካል ተደርጎ የሚወሰደው የተማሪዎች ልዩ ልዩ አደረጃጀቶችና የወተመህ አደረጃጀቶች ናቸው፡፡ እነዚህን አደረጃጀቶች ከየባህሪያቸው አኳያ ተልዕኮ ሰጥቶ ለማስማራት እንዲቻል በራሳቸው አደረጃጀት ያላቸው የአደረጃጀታቸው ነጻነት ተጠብቆ የሚሳተፉበት ሁኔታ መፍጠር የሚገባ ሲሆን ያልተደራጁት በተለይም የተማሪዎችና የወተመህ አደረጃጀቶችን ካለፈው ዓመት እንቅስቃሴያቸው አኳያ ገምግሞ የሚጠናከሩበትን ወይም በአዲስ የሚቋቋሙበትን ሁኔታ መፍጠር የዚህ የዝግጅት ምዕራፍ ዋና ተግባር ተደርጎ በተሟላ ሁኔታ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

በሌላ በኩል የግል ዘርፉ ለአጠቃላይ ትምህርት መስፋፋት የሚጠበቅበትን ሚና እንዲጫወት በትምህርት ስራ ላይ የተሰማሩ የግል ትምህርት ቤቶች ባለሃብቶች የራሳቸው አደረጃጀት እንዲኖራቸው አስፈላጊውን ድጋፍና አመራር መስጠት ያስፈልጋል፡፡

### 4.1.5. ተግባር አምስት:- የአሠራር ግልጽነትን መፍጠር፣

የአሠራር ግልጽነትን ለማስፈን በዋናነት ማተኮር ያለብን ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች የሚሠሩባቸው መመሪያዎች፣ ማንዋሎችና የአሠራር ስልቶች በየደረጃው ባለው በሁሉም ተቋማት መኖራቸውን ማረጋገጥና የአሰራር ማንዋሎችን ማሻሻልና አዳዲስ ማንዋልና መመሪያዎችን ማዘጋጀት ላይ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ጉዳዩ ተገቢ ትኩረት ተሰጥቶት ሊተገበር ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከአሠራር አኳያ፡

- የውጤት ተኮር የአሠራር ሥርዓት በሁሉም ደረጃ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡
- የዜጎች ቻርተር ተከልሶ የተቋማት ደንበኞች እንዲያውቋቸው ይደረጋል፡፡
- አስፈላጊ በሆኑባቸው የስራ ክፍሎችና ተቋማት (በክዘና ማእከላት፣ በቤተ መጽሀፍት፣ በንብረት ክፍሎች፣ በቤተ ሙከራዎች) የካይዘን አሰራር ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

### 4.1.6. ተግባር ስድስት:- ግብአትን በወቅቱ ማቅረብ፣

ግብዓትን ከማቅረብ አኳያ የሚኖሩትን ተግባራት በአራት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ እነዚህም የሰው ሃይል ግብዓት፣ የትምህርት መሣሪያዎች፣ የበጀት ግብአትና የመሠረተ ልማት ማሟላት ናቸው፡፡ ይህ ተግባር በቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ ብቻ ተከናውኖ የሚጠናቀቅ ሳይሆን በተግባር ምዕራፍም ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡

#### 4.1.6.1. የሰው ሃይል አቅርቦት፣

ከሰው ሀይል አቅርቦት አኳያ በዋናነት ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ የመምህራን፣ የት/ቤት አመራርና እንዲሁም በወረዳና በትምህርት ቤት ደረጃ ቁልፍ ድርሻ ያላቸውን ባለሙያዎች የቅጥርና ምደባ ጉዳዩ ነው፡ በዚህም መሠረት፡-

- የት/ቤት ር/መምህራንና የጉድኝት ሱፐርቫይዘር የሌላቸውን ት/ቤት ከመከፈቱ በፊት ማሟላት፣ የሚሸጋሸጉ /ከኃላፊነት የሚነሱም ካሉ በትካቸው ምደባ ማካሄድ፣
- የመምህር ቅጥርና ምደባን በተመለከተ በየአመቱ በፊፀምንበት አግባብ በተሟላ ሁኔታ መምህራንን በመቅጠር በየት/ቤቱ አስቀድሞ መመደብ ይገባል፡፡ በበጀት እጥረትና በመሣሠሉ ሠበቦች ያለመምህር ክፍል ታሽጐ የሚቀመጥ ተማሪ እንዳይኖር ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡
- የክልል ትምህርት ቢሮ፣ የዞን ትምህርት መምሪያና የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች ባለሙያ ተመድቦላቸው ሁሉም ተግባርና ሃላፊነቱን እንዲወጣ መደረግ ይገባል፡፡
- የት/ቤት የአስተዳደር ሠራተኞች ማለትም የቤተ መጽሀፍት አስነባቢ፣ ንብረት ክፍል፣ ወዘተ ተሟልተው ስራ የሚጀምሩበት ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል፡፡

### 4.1.6.2. ለ.የትምህርት መሣሪያዎችና ሌሎች ቁሣቁሶች አቅርቦት

#### ሀ) የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ አቅርቦት፡-

የተማሪ መማሪያ መጽሐፍት በ 2014 ዓ/ም በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት ለተዘጋጁት የትምህርት አይነቶች ውጭ ነባሩ መጽሀፍ የማይታተም ሲሆን በየደረጃው ያለው አካል ነባሩን የመማሪያና ማስተማሪያ መጽሀፍት ከት/ቤት ት/ቤት፣ ከወረዳ ወረዳ፣ ከዞን ዞን በማሸጋሸግ በስራ ላይ እንዲውል ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ በመሆኑም በ 2014 ዓ.ም. በናሙና ት/ቤቶች የሚሞከሩት መጽሀፍት አቅርቦት በተቻለ መጠን በሚከተለው አኳኋን መፈፀም አለባቸው፡፡

- በክልል ደረጃ የታተመ መጽሐፍትን እስከ ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ድረስ የማሠራጨት፣
- ወረዳዎችና ት/ቤቶች በመተጋገዝ መጽሐፍቱን ወደ ት/ቤት በማጓጓዝ መጽሃፍቱ ወረዳ በደረሠ በአምስት ቀን ውስጥ አሠራጭቶ ማጠናቀቅ ይገባቸዋል፡፡
- ት/ቤቶች የወሠዱትን መጽሐፍት ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ለሁሉም ተማሪዎች መጽሐፍ መስጠት አለባቸው፡፡

ከዚህ ባሻገር ት/ቤቶች በውስጥ ገቢያቸው አማካኝነት ለቤተ መጽሀፍት አገልግሎት የሚውሉ የንባብና የማጣቀሻ መጽሀፍት እንዲያሟሉ በትኩረት መፈፀም ይገባል፡፡

#### ለ) የትምህርት መሣሪያዎችን ማሟላትን በተመለከተ

ት/ቤቶች የደረጃ ምደባ ሲሠጣቸው የጐደላቸው ነገር ምን እንደሆነ የሚታወቅ በመሆኑ በተለይ በክረምቱ ወራት የትምህርት መሣሪያዎችንና ግብአት በማሟላት ረገድ ሠፊ ሥራ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ አኳያም የሚከተሉት ጉዳዩች በትኩረት መፈፀም አለባቸው፡፡

- የትምህርት ቴክኖሎጂ መሣሪያዎች የሆኑትን ሬዲዮ፣ ኮምፒዩተር አስቀድሞ ማሟላትና በአገልግሎት የተበላሸትን የተሟላ ጥገና አድርጐ ዝግጁ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የክልሉ ትም/ቢሮ የትምህርት ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ

ዳይሬክቶሬት ከዞንና ወረዳ መዋቅሩ ጋርና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት በሁሉም የመጀመሪያ ደረጃና 2 ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ፍተሻና ጥገና ማድረግ አለበት።

- በየደረጃው ለሳይንስ ቴክኖሎጅ ኢንጅነሪንግ ስነ- ጥበብና ሂሳብ (STEAM) ፕሮግራምን ለማጠናከር ሁሉም የሳይንስ ቤተ ሙከራ እንዲኖራቸው ከማድረግ ጎን ለጎን በቤተ ሙከራ የሚገኙ ኬምካሎችና አፓራተስ በአይነታቸው በመለየት ለአገልግሎት ዝግጁ ማድረግ ይገባል።
- የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች የድጋፍ መስጫ ማዕከላትን በማደራጀትና በማጠናከር አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት ማጠናከር፣

### ሐ) ፈርኒቸር ማሟላትን በተመለከተ

በየትምህርት ተቋማት ያሉ የግብዓት ችግሮችን ማለትም የተማሪዎች መቀመጫ ወንበር፣ ጥቁር ሠሌዳ፣ ሸልፎች ወዘተ ለመፍታት ሰፊ የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር ከፍተኛ ጥረት መደረግ ይኖርበታል። ከዚህ በተጨማሪ አገልግሎት የማይሰጡና የተሰባበሩት ፈርኒቸር ጥገና በማስደረግ ለአገልግሎት ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ ይገባል።

### 4.1.6.3. የበጀት ግብአት መሟላቱን ማረጋገጥ፣

የትምህርት ተቋማት አራት ዋና ዋና የበጀት ምንጭ አላቸው። እነርሱም ከመንግሥት ግ/ቤት የሚመደብ በጀት፣ ከውጭ ብድርና እርዳታ የሚገኝ ሐብት፣ ከውስጥ ገቢ የሚሰበሰብ ሐብት እና ከህብረተሰብ ተሣትፎ የሚገኝ ሐብት ናቸው። ከዚህ አኳያም የሚከተሉት ጉዳዩች በትኩረት መፈፀም አለባቸው።

- ከወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት የተማሪዎችን ቁጥር ታሣቢ ባደረገ መልኩ የተማሪዎች የነፍስ ወከፍ በጀት መመደቡን ማረጋገጥ፣
- በ 2013 ዓ/ም ከፌዴራል ትምህርት ሚኒስቴር የተማሪዎችን ቁጥር መሠረት አድርጎ የተመደበው የድጎማ በጀት በስራ ላይ ውሎ የሂሣብ ሠነዱ ወረዳ ፋይናንስ ጽ/ቤት መድረሱን ማረጋገጥና የ 2014 ደግሞ መመደቡን ክትትል ማድረግ፣
- የት/ቤቶች የውስጥ ገቢ እና የህብረተሰብ ተሣትፎ በት/ቤቶች ግለ ግምገማ የተቀመጡ ጉዳዩችን ታሣቢ በማድረግ መታቀዱን ማረጋገጥ፣

### 4.1.6.4. የት/ቤቶችን መሠረተ ልማት ማሟላትን በተመለከተ

- ትምህርት ከመጀመሩ በፊት የት/ቤቶች ግቢ ጸድተው፣ ቀለም ተቀብተውና አምረው ዝግጁ መሆን አለባቸው። በተጨማሪም የተሠባበሩ በሮች፣ መስኮቶች እንዲሁም የፈራረሱ አጥር መጠገንና ለተሟላ አገልግሎት ዝግጁ መሆን አለባቸው።
- በ 2014 የትምህርት ዘመን በት/ቤቶች የሚገኘውን የተማሪዎች ብዛት መሠረት ያደረገ የትምህርት ተቋማት ግንባታ፣ ደረጃ ማሣደግና ማስፋፋት ስራዎችን ከወዲሁ ማከናወን ይገባል።
- በረጅም ዘመን አገልግሎትና በእርጅና የተነሣ የተጎሣቀሉ የህንፃ ግንባታዎችን የማደስና ለመማር ማስተማር ተግባር ማራኪ ማድረግ በንቅናቄ አግባብ መከናወን አለበት።
- የአስተዳደርና የድጋፍ ሰጭ ክፍሎች የሆኑት ህንፃዎች (ቅርንጫፍ ማዕከል፣ ቤተ መጽሀፍት፣ ቤተ ሙከራ፣ የአስተዳዳር ህንፃ፣ ዕቅ ግ/ቤት ወዘተ) በአግባቡ እንዲሟሉ መደረግ አለበት።

**4.1.7.** ተግባር ሰባት**:-** በቀውስ ወቅት ትምህርትን ለማስቀጠል የሚያስችሉ አሰራርና አደረጃጀት ስርዓት በማጠናከር በድንገተኛ አደጋ በሚጠቁ አካባቢዎች የሚገኙ የት/ቤት አመራሮችና መምህራን በአደጋ ጊዜ ውጤታማ ምላሽ እንዲሰጡ ማድረግ፣

- በኮቪድ-19 ለመከላከል ሊደረጉ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች የወጡትን መመሪያዎችና ፕሮቶኮሎች መሠረት በማድረግ ተግባራት ሣይንጠባጠቡ መፈፀም፣
- የተለያዩ ሚዲያዎችን ማለትም የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎችን፣ የህትመት ሚዲያዎችን፣ ማህበራዊ ሚዲያዎችና የተቋሙን ድረ-ገጽ በመጠቀም የኮቪድ 19 መከላከያ መንገዶች ግንዛቤ በመፍጠር ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ እና ተማሪዎችም ያለስጋት ከትምህርት ገበታቸው ላይ እንዲገኙ ማድረግ፣
- በግጭት እና ወረራ ምክንያት ሙሉ በሙሉ እና በከፊል የወደሙ የትምህርት ተቋማት መልሶ የማደራጀት ሥራ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን መልሶ ማስተካከልና የመደበኛ መማር ማስተማር እንዲጀመር ማድረግ፣
- በጉዳቱ ሠለባ የሆኑ መምህራን፣ ተማሪዎችና የትምህርት ባለሙያዎች የማህበራዊ ስነ ልቦና ስልጠና አዘጋጅቶ መስጠት፣
- በቀውስ ውስጥ በገቡ አካባቢዎች ለሚኖረው የትምህርት ማህበረሰብ የተጨማሪ ሐብት ማሰባሰብ ሥራዎችን ማከናወን፣

***4.1.8.*** ተግባር ስምንት**:-** በ ***2014 ዓ.ም.*** ትምህርት ቤት መግባት ያሉባቸው ተማሪዎች በሙሉ ምዝገባ ማጠናቀቅና ወደ ትምህርት ቤት ገብተው የዘመኑን ትምህርት እንዲጀምሩ ማድረግ፣

- የዘላቂ የትምህርት የልማት ግብና የትምህርት ለሁሉም ግቦችን ከማሳካት አኳያ እንደ ክልል፣ዞን፣ ወረዳና ትምህርት ቤት የምንገኝበትን ደረጃ በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሰረተ ግምገማ በየደረጃው ማድረግና የግምገማ ሰነድ ማዘጋጀት፣
- ግምገማውን መነሻ ያደረገ የዘላቂ ልማት ግብና የትምህርት ለሁሉም ልዩ እቅድ እንደ ክልል፣ ዞን፣ ወረዳና ትምህርት ተቋም አዘጋጅቶ በየደረጃው ባለው አመራር የጋራ በማድረግ ማጸበርና ማጸደቅ፣
- የምዝገባና ተማሪን የማምጣት ስራው የሚመራበትን የማስፈጸሚያ እቅድ በማዘጋጀት ማስፈጸም። በእቅዱ 7 አመት የሞላቸው፣ እድሜያቸው የደረሰ ሆኖ ወደ ትምህርት ቤት ያልመጡ፣ በተለያዩ ምክንያቶች ያቋረጡ፣ በ 2013 በየክፍል ደረጃው በመማር ላይ የነበሩ ተማሪዎች በሙሉ እንዲመዘገቡ የማድረግ ስራ በግልጽ ተካትቶ እንዲተገበር ማድረግ፣
- እቅዱ በተለየ ትኩረትና በሁሉም አካላት ባለቤትነት መፈጸም የሚችልበትን አቅጣጫ በማስቀመጥ በተለየ ቅንጅትና ንቅናቄ እንዲተገበር ማድረግ፣
- አሁን ባለንበት ደረጃ ይህንን ተግባር መፈጸም ማለት የምእተ አመቱን የልማት ግቦች ለማሳካት የሞት ሽረት ጉዳይ መሆኑን አምኖ በየደረጃው የሚገኘው አመራር ወደ ተግባር እንዲገባ ማድረግ፣
- እድሜያቸው ለየክፍል ደረጃው የደረሱ ሕጻናትን በመንደርና ቤት ለቤት በስም መለየት፣ በተለይ የተረሱ ችግር ያለባቸው ሕጻናት ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግ መሥራት፣ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ቅበላውን መሸከም የሚችል ዝግጅት ማድረጉን ማረጋገጥ፣

***4.1.9.*** ተግባር ዘጠኝ**:-**የዘመኑን ትምህርት ሁሉን ባለድርሻ አካላት ባሳተፈ መልኩ በሕዝብ ንቅናቄ መጀመር፤ ይኸውም ሥራ አመቱን ሙሉ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ስልት ቀይሶ መተግበር፣

አዲሱ የትምህርት ዓመት የሚጀመረው የትምህርት ሣምንት በዓል ከመስከረም 3-16/2014 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ በማክበር በየደረጃው ከፍተኛ ንቅናቄ በመፍጠር መሆን አለበት። የትምህርት ሣምንት በዓል አከባበር በራሱ ዕቅድ የሚመለስ ቢሆንም በሣምንቱ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-

- መስከረም 24 ቀን በሁሉም የትምህርት መዋቅራችን የትምህርት ሣምንት፤ የንቅናቄ መጀመሪያ በአሉን በደመቀ ሁኔታ ማክበር፣ክልላዊ በዓሉ በተመረጠ አንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ይከበራል። በተመሣሣይ ሁኔታም ሁሉም ዞንና ወረዳዎች አንድ የትምህርት ተቋም መርጠው መስከረም 24/2014 ዓ.ም ማክበር አለባቸው።
- መስከረም 25 ቀን በክልሉ ትም/ቢሮ አመራሮች በኘላዝማና በሬዲዮ የሚያቀርቡትን መግለጫዎች ሁሉም መምህራን እንዲከታተሉትና በየተቋሙም እንዲወያዩበት ማድረግ፣
- ከመስከረም 25 እስከ 30 ድረስ በሚወጣው ኘሮግራም መሠረት ሁሉም መምህራን፣ ተማሪዎችና ህብረተሰቡ በሚከተሉት ርዕሶች ላይ ስልጠና ይወስዳሉ፤
    - o የአገር አቀፍ የክልል አቀፍና እና የት/ቤት የተማሪዎች የተጠቃለለ ውጤት ትንተና፣
    - o የ 2014 ዓ.ም የተቋሙ የትምህርት ዕቅዶች ላይ
- ተንጠባጥበው የቀሩ /ያልተመዘገቡ/ ነባርና አዲስ ተማሪዎች ከሉ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት የማጥራት ሥራ መስራት
- ሁሉም ተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፍት ያገኙ መሆናቸውን ማረጋገጥ
- የት/ቤቶችን ምድረ ግቢ በማጽዳት ዝግጁ ማድረግ
- Day One Class One በትምህርት ካሌንደሩ መሠረት በተሟላ ሁኔታ መጀመር

## 4.2. የተግባር ምዕራፍ ተግባራት አፈፃፀም

የተግባር ምዕራፍ የዝግጅት ምዕራፍ በበቂ ሁኔታ ከተከናወነ በኋላ የሚቀጥለውና ዋናው የሥራ ርብርብ የሚካሄድበት ምዕራፍ ነው። በዚህ ምዕራፍ አስፈፃሚውና ባለድርሻ አካላት በእቅዱ የተቀመጡትን ግቦች ለማሣካት በተደራጀ አኳኋን ሰፊ የህዝብ ንቅናቄ የምንፈጥርበት ምዕራፍ ነው። በመሆኑም በዚህ ምዕራፍ ሁሉም አደረጃጀቶች ተልእኮአቸውን በተሟላ መንገድ ጨብጠው ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በማስገባት የተጣሉ ግቦችን እንዲተገበሩ ማስቻል ነው። ይህንን በተሟላ መልኩ ለመፈፀም ደግሞ ጠንካራና የማያቋርጥ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በዓመቱ የታቀዱ ተግባራት ለመፈፀም ንቅናቄ መፍጠርና ወደ ተግባር ማስገባት ይገባል።

### 4.2.1. ተግባር አንድ:- ጠንካራና የማያቋርጥ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የአመቱን ዕቅድ የሚፈጽምበት ንቅናቄ መፍጠርና ወደ ተግባር ማስገባት፣

- ወጥ የሆነ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት በየደረጃው መዘርጋት
- የመደበኛ ሱፐርቪዥንና የኢንስፔክሽን ስራዎችን በመርሀ ግብሩ መሰረት ተግባራዊ ማድረግና በክትትሉ የተለዩ ጉዳዮችን በየወሩ ከስራ ክፍሎችና በየሩብ አመቱ ከዞኖችና ወረዳዎች ጋር በሚኖር መድረክ ተወያይቶ የመፍትሄ አቅጣጫ ማስቀመጥ፣
- በተግባር ሂደት የሚታዩ ምርጥ አፈፃፀሞችን እየለዩ በሁሉም ተቋማት በማስፋት የፈጻሚ አካላት የመፈፀም ብቃትና ክህሎት ተቀራራቢ ማድረግ
- በተግባር ሂደት የሚታዩ የክህሎት ክፍተቶች እየለዩ መሙላት
- በየአደረጃጀቱ አኳያ የግምገማና የሂስ ግለሂስ መድረኮችን እያዘጋጁ ቀጣይነት ያለው የአቅም ግንባታ ተግባር ማከናወን፣
- የልምድ ልውውጥ ኘሮግራሞች እያዘጋጁ በተግባር ላይ የተመሠረተ ልምድ የማለዋወጥ ተግባር መፈፀም

- በተግባር ሂደት በአፈፃፀማቸው ግንባር ቀደም የሆኑ አደረጃጀቶችን፣ ግለሰቦችን እየለዩ ማበረታታት

**4.2.2.** ተግባርሁለት:- የንቅናቄውን ቀጣይነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የህዝብ ግንኙነት ስራዎች/ የንቅናቄ መድረኮችን በየደረጃው በመፍጠ በውጤታማነት መፈፀም።

- የትምህርት ባለድርሻ አካላት ምክር ቤት/ ጉባዔ ማዘጋጀት
- የወላጆች ኮንፍረንስ በየትምህርት ተቋሙ ማካሄድ
- የጐልማሶች ትምህርት ጉባኤ ከባለድርሻ አካላት ጋር በክልል፣ በወረዳና በዞን ደረጃ ማድረግ
- መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ፎረም/አትክልት ፎረም በክልል ደረጃ ማካሄድ
- የመምህራን ቀን በዓል በደመቀ ሁኔታ በትምህርት ቤቶች እንዲከበር ማድረግ፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ የመምህራን በዓልን በፓናል ውይይቶች በማክበር በህብረተሰቡ ውስጥ የስርጸት ስራ መስራት።
- የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሣይንስ፣ የሂሳብና የእንግሊዝኛ መምህራን፣ ርዕሰ መምህራን የሚሳተፉበት የልምድ ልውውጥ መድረክ በየደረጃው ማዘጋጀት፣እንደ ክልል በተመረጡ ትምህርት ቤቶች ልምድ ልውውጥ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይሆናል።
- የ 1 ኛ ክፍል መምህራን ፎረም መድረኮች በትምህርት ቤቶች በየሳምንቱ፣ በወረዳ ደረጃ በየወሩ በማካሄድ የአንደኛ ክፍል ተማሪዎችን በመርሃግብሩ መሰረት እንዲበቁ ማድረግ፣
- የሴቶች ትምህርት ፎረም በክልል ደረጃ ማካሄድ
- የመምህራን ኮሌጆች የለውጥ ፎረም በክልል ደረጃ መመስረትና ወደ ስራ ማስገባት፣
- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የለውጥ ፎረም በዞን ደረጃ መመስረትና ወደ ስራ ማስገባት፣

**4.2.3.** ተግባር ሦስት :- በተግባር ሂደት የሚከሰቱ የኪራይ ሰብሳቢነት ተግባርና ዝንባሌዎችን በመለየት፣ በማጋለጥና በመታገል ልማታዊ ዲሞክራሲያዊ አስተሣሠብ እንዲስፋፋ የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ተግባራትን በውጤታማነት መፈፀም

- የትምህርት ሥራው በውጤታማነት እንዳይፈፀም የሚያሰናክሉ በየደረጃው የሚታዩ የተበላሹ ልምዶችና አሠራሮችን ታግሎ ማስተካከል።
- የትምህርት ሥራውን የሚያደናቅፉ አመለካከቶችን በመለየት ለማስተካከል የሚያስችል የግምገማና ሂስ ግለሂስ መድረኮችን እያዘጋጁ በውጤታማነት መፈፀም
- ልማታዊና ዲሞክራሲያዊ አስተሣሠብን ሊያዳብሩ የሚችሉ ርዕሰ ጉዳዮችን እየለዩ በሠራዊቱ ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች አማካይነት ቀጣይነት ያለው የግንባታ ሥራ ማካሄድ።

**4.2.4.** ተግባር አራት:- በየደረጃው የሚሰጠው የአጠቃላይ ትምህርት ጥራትን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ፣

- በየደረጃው በመምህራንና ተማሪዎች የተጀመረውን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የበለጠ ማጠናከር፣ መምህራንና ተማሪዎች የት/ቤት ህገ ደንብ መተግበራቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም ሁሉም ተማሪዎች በልዩ ልዩ ተጓዳኝ ክበባት መሣተፋቸውን ማረጋገጥ፣
- አዲሱን ስርዓተ ትምህርት በተሟላ ሁኔታ ለመተግበር ናሙና በወረዳ ደረጃ ከክልል በሚላከው መስፈርት መሠረት በመምረጥ አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅት ማጠናቀቅና ፕሮግራመን በተሣካ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ፣

- የ 11 ኛ ክፍል ተግባራዊ የሚደረግባቸውን ት/ቤቶች ከክልል በሚላከው መስፈርት መሠረት መምረጥና አስፈላ ቅድመ ዝግጅቶችን ማጠናቀቅ፣
- በየደረጃው የትምህርት ተቋማትን ሥራ በባለቤትነት የሚመራ አካል ለማሟላት የተጀመረውን ጥረት አጠናክሮ ማስቀጠል፣
- የመማር ማስተማር ተግባራ በውጤታማነት ለመፈፀም እንዲረዱ የተፈጠሩ አደረጃጀቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ማስቻል፣
- ለሁሉም ት/ቤቶች ለትምህርቱ ሥራ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት ምቹ የትምህርት አከባቢ መፈጠሩን ማረጋገጥ፣
- የሁሉንም ትምህርት ቤቶችን ውስጣዊ ብቃት በማሻሻል የትምህርት ብክነትን መቀነስ፣
- ህብረተሰቡ ትምህርት ቤቶችን በሙሉ ባለቤትነት መምራት የሚችልበት ደረጃ ላይ ማድረስ፣
- በ 2014 የምንቀበላቸው የ 1 ኛ ክፍል ተማሪዎች በሙሉ እስከ ታህሳስ 30 ማንበብ፣ መጻፍና ማስላት ማስቻል።
- ሁሉም ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት አይነት 50% እና በላይ እንዲያመጡ፣ 35% የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ ከ 75% በላይ እንዲሁም 15% ተማሪዎች 85% እንዲያመጡ ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራትን በመፈፀም የተማሪዎችን ውጤት ማሻሻል፣
- በአመት ሁለት ጊዜ በተመረጡ የክፍል ደረጃዎች ክልላዊ የብቃት ማረጋገጫ ፈተና በመስጠት የተማሪዎችን ውጤት መተንተን፣ በየደረጃው እስከ ትምህርት ቤት ድረስ ግብረ መልስ መስጠት፣
- የሁለቱም ወሠነ ትምህርቶች ማጠቃለያ ፈተና ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች /9 ኛና 11 ኛ ክፍል/ በክልል ትምህርት ቢሮው፣ ከ 5-7 ኛ ክፍል በዞን ትምህርት መምሪያዎች፣ የ 4 ኛ ክፍል በወረዳ ደረጃና ከ 1-3 ኛ ክፍል በጉድኝት ደረጃ ፈተናዎች ተዘጋጅተው እንዲሠጡ ማድረግ፣
- የሁለቱም ወሠነ ትምህርት ማጠቃለያ ፈተና በሁሉም ክፍሎች ውጤት ትንተና ከትምህርት ቤት ጀምሮ እስከ ክልል ማካሄድ፣ ግብረ መልሱም በየደረጃውና ለተማሪዎችና ለህብረተሰቡ እንዲደርስ ማድረግ፣
- የመምህራን ልማት ኘሮግራም (CPD) እና ሌሎች ልዩ ልዩ ስልጠናዎች በማዘጋጀት የመምህራንን ብቃት የማሻሻል ሥራ መሥራት፣
- የኮምፒዩተርና የሬዲዮ ኘሮግራም ትምህርቶች ሣይቆራረጡ በአግባቡ የሚሠጡበትን ተመራጭ ዘዴ ፈልጐ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የመምህራንና የትምህርት ቤት አመራር የሙያ ፈቃድና እድሳት አሠጣጥ ሥርዓትን ተግባራዊ በማድረግ ብቃት ያላቸው መምህራንና አመራሮች በትምህርት ሥርዓቱ እንዲቀጥሉና እንዲበረታቱ የሚያስችል ሥራ መስራት፣
- በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች የትምህርት ጥራቱን በጥናትና ምርምር እያረጋገጡ መሄድ፣
- በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት በክልላችን ካሉ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች መካከል ከእንስፔክሽን ስታንዳርድ አኳያ 31.24% (29.36% ደረጃ 3 እና 1.88% ደረጃ አራት) ማድረስ፣ እንዲሁም በ 2 ኛ ደረጃ ት/ቤቶች 33.65% (29.89% ደረጃ 3 እና 3.76% ደረጃ አራት) እንዲደርሱ ማድረግ፣

### 4.2.5. ተግባር አምስት:- የትምህርት ተደራሽነትን፣ ተሣትፎንና ፍትሐዊነትን ማረጋገጥ።

- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተሣትፎን ለማሣደግ በሁሉም የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች “0” /ዜሮ/ ክፍል በመክፈትና የተከፈቱትን በማጠናከር እና ከመደበኛ ት/ቤት ራቅ ብለው በሚገኙ መንደሮች የቅድመ መደበኛ ት/ቤት በመገንባት ህፃናቱን በማስተማር ሽፋኑን ለማሣደግ ባለፈው ዓመት የተጀመሩ ጥረቶች አጠናክሮ ማስቀጠል፣

- የልዩ ፍላጎት ትምህርት ግብን ለማሳካት በሁሉም ወረዳዎች ቢያንስ አንድ ትምህርት ቤትና በተመረጡ ጉድኝቶች ውስጥ የልዩ ፍላጐት ትምህርት ዩኒት መክፈት፣
- የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶችን ተደራሽነት ለማስፋት በ 2014 ዓ.ም. ፡-
    - 310 አዲስ የተገነቡ ት/ቤቶች የተሟላ አገልግሎት ይሠጣሉ።
    - 345 የመጀመሪያ ደረጃ የመጀመሪያ ሣይክል ት/ቤቶች ወደሙሉ ሣይክል ደረጃ እንዲያድጉ ይደረጋል።
    - በ 2013 ዓ.ም. 5 ኛ ክፍል ትምህርት መስጠት የጀመሩ ትምህርት ቤቶች በ 2014 ዓ.ም. 6 ኛ ክፍል ይከፍታሉ።
    - በ 3 ኪ.ሜ ራዲየስ ትምህርት የማያገኙ አካባቢዎች ካሉ አጥንቶ የማስተካከያ ርምጃ መውሠድ።
- የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ተደራሽነት ለማስፋት በ 2014 ዓ.ም.
    - 36 አዲስ ሁለተኛ ደረጃ ትም/ቤቶችን የተሟላ የትምህርት አገልግሎት ይሠጣሉ።
    - 27 የከፍተኛ 2 ኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሣይክል ት/ቤቶች ወደ መሠናዶ በማሳደግ ከ 9 ኛ-12 ኛ ክፍል ትምህርት የሚሠጡ የተሟሉ ተቋማት ይሆናሉ።
    - አዳዲስ ት/ቤቶችን በመገንባት ለ 2015 ዓ.ም. ዝግጁ ማድረግ።
- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የማጠናቀቅ ምጣኔን (Completion Rate) ለማሣደግ የትምህርት ብክነትን /መድገምና ማቋረጥን/ መከላከል።
- ተግባር ተኮር የጐልማሶች ትምህርትን አጠናክሮ ማስቀጠል።
- በብሔረሰብ ዞኖች የሚሰጠውን ትምህርት ማጠናከር።

### 4.2.6. ተግባር ስድስት:- የትምህርት ፋሲሊቲዎችን /መሠረተ ልማትና ግብአት/ማሟላት፣

- የት/ቤቶችን የውሃ ሽፋን ለመሳደግ የሚያስችል ሰፊ የህዝብ ንቅናቄ መፍጠር፣
- የመፀዳጃ ቤት አገልግሎት 100% የተሟላ ማድረግ የሚያስችል ስራ መስራት።
- በክልሉ መቀመጫ ወንበርና ደስክ የሌለው አንድም ተማሪ እንዳይኖር አልሞ መስራት።

### 4.2.7. ተግባር ሰባት:- በየደረጃው ባለ የትምህርት መዋቅር መልካም አስተዳደርን በማስፈን ልማታዊ አስተሣሠብን ማስረጽ

- በየደረጃው የሚታዩ የመልካም አስተደደር ችግሮችንና ምንጮቻቸውን በጥናት መለየትና የመፍትሔ አቅጣጫ አስቀምጦ መተግበር።
- የግልጽነት፣ የተጠያቂነትና አሣታፊነትን የሚያሰፍን አሠራር ተግባራዊ ማድረግ።
- በአፈጻጸም ግልጽ ያልሆነ የአሠራር መመሪያና ማንዋሎችን ከልሶ በጥራት ማዘጋጀት።
- በየደረጃው ባለው ተቋም ያሉ ሁሉም ፈፃሚዎች ከዕቅድ አወጣጥ እስከ ግምገማ ባለው ሂደት የተሟላ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ።
- ሙስናን፣ አድልኦና ብልሹ አሠራርን መከላከልና በጥብቅ መታገል።
- የአገልግሎት አሠጣጥ ሥርዓቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ።-

- o በዞን፣ በወረዳና በትምህርት ተቋማት የዜጐች ቻርተር አዘጋጅቶ ባለድርሻ አካላት እንዲያውቁት ማድረግ።
- o የተሸሻለውን የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ክለሣ ጥናት ተግባራዊ ማድረግ፣
- o በተቀመጠው የአገልግሎት አሠጣጥ ስታንዳርድ መሠረት ለዜጐች አገልግሎት መስጠት።
- o በሁሉም ደረጃ የሥራ ውጤታማነትን በማምጣት የዜጐችን አመኔታና እርካታ ማሳደግ።
- o በየትምህርት ተቋማት ሠላማዊ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲፈጠር ማድረግ።

- የትምህርት ሃብትን በውጤታማነት መጠቀም
  - o የፐሮግራም በጀትን በውጤታማነት መጠቀም
  - o የካይዘን አሰራርን ተግባራዊ ማድረግ

## 4.3. የማጠቃለያ ምዕራፍ ተግባራት አፈፃፀም

የማጠቃለያ ምዕራፉ በ 2014 ዓ.ም የዕቅድ አፈጻጸምን በመገምገም ለቀጣይ ስራችን ልምድ በምንወስድበት፣ በትምህርት ዘመኑ ግባቸውን ያሳኩና ውጤታማ የሆኑ ተቋማት፣ የትምህርት አመራሩ፣ መምህራን፣ ተማሪዎችና ባለድርሻ አካላት በሚበረታቱበት አግባብ ይፈጸማል። በዚህም መሰረት የሚከተሉት ተግባራት ይከናወናሉ።

### 4.3.1. ተግባር አንድ:- የዘመኑን እቅድ አፈጻጸም ተቋማዊ በሆነ መንገድ መገምገምና ለአደረጃጀቶችና ፈጻሚዎች ግምገማውን መነሻ ያደረገ ደረጃ መስጠት፣

- የማጠቃለያ ግምገማ ማስፈጸሚያ እቅድ በየደረጃው ተዘጋጅቶ በሁሉም ተቋማት ተግባራዊ ይደረጋል፣
- በግምገማው በቅድሚያ እያንዳንዱ የሥራ ክፍል የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርታቸውን እንዲያዘጋጁ በማድረግ በአደረጃጀት ደረጃ የአካል ግምገማ ከተካሄደ በኋላ እያንዳንዱ ባለሙያ ሂስ ግለሂስ እንዲያደርግ ይደረጋል፣
- ትምህርት ቤቶች የዘመኑን የተማሪ ውጤት በክፍል ደረጃና በትምህርት አይነት ተንትነው ከተጣለው ግብ አኳያ በማሳየት ለመድረኮቹ በግብአትነት ይጠቀሙበታል፣
- በትምህርት ቤት ደረጃ ለአደረጃጀቶች ግምገማውን መነሻ ያደረገ ደረጃ ይሰጣል፣ በፈጻሚዎች መድረክም በተመሳሳይ ለተማሪዎችና ለመምህራን ደረጃ ይሰጣል፣
- ትምህርት ቤቶች በተዘጋጀው ስታንዳርድ መሰረት የውስጥ ግምገማቸውን ከጨረሱ በኋላ በወረዳ ደረጃ በተደራጀ ገምጋሚ ቡድን ተገምግመው ደረጃ ይወጣላቸዋል፣ በተዋረድ ለወረዳዎችና ለዞኖች አፈጻጸማቸውን መነሻ ያደረገ ደረጃ ይወጣላቸዋል፣
- ርእሳነ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ተቆጥሮ ከተሰጣቸው ተግባር አፈጻጸም አኳያ በወረዳ ደረጃ የማጠቃለያ ግምገማ አካሂደው ሂስ ግለሂስ ያደርጋሉ፣ ደረጃም ይወጣላቸዋል፣ በተግባር አፈጻጸማቸው ተቋማቱን ለመምራት ችግር የታየባቸው አመራሮች በግንባር ቀደሞች እንዲተኩ ይደረጋል፣

### 4.3.2. ተግባር ሁለት:- የዘመኑን የተግባር አፈጸጸም በህዝባዊ ኮንፈረንስና ጉባኤ ማጠቃለል፤

- በየደረጃው የትምህርት ጉባኤ በማካሄድ በትምህርት ዘመኑ ግባቸውን ያሳኩና ውጤታማ የሆኑ ተቋማት፣ የትምህርት አመራሩ፣ መምህራን፣ ተማሪዎችና ባለድርሻ አካላት እንዲበረታቱ ይደረጋል።

- በትምህርት ቁልፍ አጀንዳዎች ላይ ከመንግስት ከፍተኛ አመራሮች፣ከትምህርት ባለድርሻ አካላትና ከህዝቡ ጋር የምንመክርበትና ከእነዚሁ አካላት ጋር መግባባትና ስትራቴጂያዊ አጋርነትን በምናጠናክርበ አግባብ ተግባራዊ ይደረጋል።
- ፊስቲቫሉ መላውን ባለድርሻ አካላትና ህብረተሰቡን በሰፊው ማሳተፍ እንዲቻል ከትምህርት ተቋማት ጀምሮ በየደረጃው እንዲካሄድ ይደረጋል። በዚህም መሰረት
  - በትምህርት ቤት ደረጃ ሁሉንም ባለ ድርሻ አካላት ያሳተፈ የትምህርት ጉባኤ/ኮንፈረንስ ማካሄድ፣
  - በመድረኮቹ የዘመኑን የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት አቅርቦ በማዳበር ማጸደቅ እና ጥሩ አፈጻጸም ያላቸው አካላት እውቅና እንዲያገኙ ማድረግ፣
  - በዝግጅት ምእራፍ ሊከናወኑ የሚገባቸውን ተግባራት በመድረኩ በማቅረብ የየድርሻቸውን ለይተው ለተግባር ተነሳሽነትን መፍጠር፣

#### 4.3.3. ተግባር ሶስት:- በዘመኑ የታዩ ምርጥ አፈጻጸሞችን መቀመርና ለ 2015 ዕቅድ ዝግጅት ማድረግ፣

- በዕቅድ አፈጻጸም የታዩ ምርጥ ተሞክሮዎችን ከምርጥ ተቋማት በመቀመር ለስልጠና ዝግጁ ማድረግ
- በግምገማ ሂደት የተገኙ ግብዓቶችን በመጠቀም ለ 2015 ዕቅድ ዝግጅት ማድረግ፣

#### 4.3.4. ተግባር አራት:- የተማሪዎች ውጤት በማጠናከርና በመተንተን ለቀጣይ ለ 2015 ዕቅድ ዝግጁ ማድረግ፣

- የማጠቃለያ ፈተና መስጠትና አርሞ ውጤቱን ለተማሪዎች ማሳወቅ፣
- የተማሪ ውጤት መተንተንና ለውይይት ዝግጁ ማድረግ።

# 5. የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት፣

## 5.1. በክልል ደረጃ፣

- የቢሮ ከፍተኛ አመራር በቀጣና ተከፋፍሎ እንዲደራጅ ከተደረገ በኋላ የታቀዱ ሥራዎችን ይከታተላል፣ በሥሩ የቴክኒክ ቡድን ይደራጃል፣
- ሁሉም ዳይሬክቶሬቶች በየወሩ የታቀዱ ሥራቸውን ይገመግማሉ፣
- አጠቃላይ የቢሮው ሠራተኛ በየስድስት ወር የሥራ ግምገማ ያካሂዳል፣
- የቢሮው ሥራ አመራር ኮሚቴ በየ 15 ቀኑ ሥራውን ይገመግማል
- በየወሩ ከዞን ትም/መምሪያዎች ጋር በአካል ወይም በኘላዝማ አጫጭር ግምገማዎች ያካሄዳሉ፣
- በየ 3 ወሩ የዞን አመራር ጋር ዝርዝር ግምገማ ይካሄዳል እንደ አስፈላጊነቱ የወረዳ አመራር የሚጨመርበት ሁኔታ ይመቻቻል፣
- የቢሮው ሱፐርቪዥን ቡድን 4 ጊዜ ወረዳና ዞንን ወርዶ ይደግፋል / መስከረም ፣ታህሣሥ ፣ የካቲትና ሰኔ/
- የመስክ ምልከታ፣ የፅሑፍ ሪፖርቶችና ግብረ መልሶች በየሳምንቱ እና በየሩብ አመቱ መጨረሻ ይካሄዳሉ።

## 5.2. በዞን ደረጃና በወረዳ ደረጃ፣

- ✓ የትምህርት ተቋሙን መዋቅር ተከትሎ ከላይ በተቀመጠው መሰረት የክልሉን አካሄድ መነሻ ያደረገ በየደረጃው የድጋፍና ክትትል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት።
- ✓ ወደ ታችኛው መዋቅር ወርዶ በመደገፍ በተቻለ መጠን ሁሉንም ወረዳዎችና የትምህርት ተቋማት ለማገዝ እንዲቻል ዞን ክልሉ ባልሸፈናቸው እንዲሁም ወረዳ ክልሉና ወረዳው ባልሸፈናቸው ተቋማት በመደገፍ የክትትልና የድጋፍ አድማሱን ማስፋት ይገባል።

# 6. የአፈጻጸም አቅጣጫዎችና ስልቶች፣

## 6.1. አጠቃላይ አቅጣጫዎች፣

- ትኩረታችን የተቀመጡ ዕቅዶችን በዘመቻ ማሳካት ሳይሆን ውጤታማ የአሰራር፣ የክትትልና የድጋፍ ስርዓት /System/ ፈጥረን በተፈጠረው ስርዓት ውስጥ ወደ ተግባር በማስገባት ዕቅዶችን ማሳካት ይሆናል።
- እያንዳንዱ ተግባር በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት መፈጸሙን እያረጋገጡ መሄድ፣
- በየጊዜው ምርጥ ተሞክሮዎችን እየቀመሩ በማስፋት ሁሉም ዞኖች፣ ወረዳዎችና ትምህርት ቤቶች ተቀራራቢ የአፈጻጸም ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ፣

- የንቅናቄ ስራው በልዩ ልዩ የሚዲያና የህዝብ ግንኙነት ሥራዎች ታጅቦ እንዲፈጸም ማድረግ፣
- ስራዎችን በጥብቅ ዲሲፕሊን መፈጸም፣የማበረታቻና የተጠያቂነት አሰራርን ተግባራዊ ማድረግ፣
- በየደረጃው ያለ አስተባባሪ ኮሚቴ በየጊዜው ሪፖርት እየቀረበለት ሥራውን እየገመገመ እንዲመራው የማድረግ አቅጣጫን መከተል

## 6.2. ዝርዝር የማስፈጸሚያ አቅጣጫዎችና ስልቶች፣

### 6.2.1. የቅድመ መደበኛ ትምህርትን ለማስፋፋት የምንከተላቸው የአፈፃፀም አቅጣጫና ስልቶች፣

- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ላይ የህብረተሰብ በተለይም የወላጆችን ግንዛቤ በማሳደግና ከእቅድ አወጣጥ ጀምሮ ማሳተፍ፣
- የሴቶችን አደረጃጀት ተጠቅሞ ቤት ለቤት የህፃናት ልየታ ስራ በመስራት ሁሉም ህፃን /ከ 4-6 ዓመት/ ወደ ቅድመ መደበኛ እንዲመጣ ማድረግ
- በመደበኛ ት/ቤቶች የኦ-ክፍል በመክፈት፣ የሣተላይት መማሪያ ጣቢያዎችን፣ የተፋጠነ የትምህርት ዝግጁነት በመጠቀም መርሃ ግብሩን ማስፋፋት፣
- የቅድመ መደበኛ ትምህርት የሚመራ አደረጃጀት ከክልል ት/ቤት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ፣ በክልል የቅድመ መደበኛ ካውንስል፣ በዞንና በወረዳ ቴክኒካል ኮሚቴ አቋቁሞ ለተግባሩ ባለቤት መስጠት፣
- መንግስትና ልዩ ልዩ አካላት ተግባሩን አካተው/mainstreaming አድርገው/ በእቅዳቸው ይዘው እንዲተገብሩት ማድረግ

- ከቤተሰብ፣ ከህብረተሰብና ከመያድ ጋር ጥብቅ ትስስር መፍጠር

### 6.2.2. የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን ለማስፋፋት የምንከተላቸው የአፈጻጸም አቅጣጫዎችና ስልቶች፣

- በት/ቤቶችና በተማሪዎች መኖሪያ አካባቢ ያለውን ርቀት መቀነስ። ለዚህም እንዲረዳ በሁሉም ቀበሌዎች በ 2.5 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ት/ቤቶች እንዲኖሩ ማድረግ
- የመሬቱ አቀማመጥ ገደላማና ተራራ በሆነባቸው ቀበሌዎች በጥናት ላይ ተመርኩዞ ሣተላይት መማሪያ ክፍሎችን መክፈት፣
- በሁሉም የገጠር ቀበሌዎች ሙሉ ሳይክል ት/ቤት እንዲከፈት ለማድረግ ከ 1-6 ያሉ ት/ቤቶችን ወደ መካከለኛ ደረጃ በማሳደግ እንዲፈፀም ማድረግ
- የመማሪያ ክፍሎች እጥረት ካጋጠመ multi grade system መፍጠር
- ለመማር ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች የአካባቢውን ህብረተሰብ ልዩ ልዩ አደረጃጀቶችን በመጠቀም የት/ቤት ምገባ ስርዓት መዘርጋት፣

### 6.2.3. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ሽፋንን ለማሳደግ የምንከተላቸው የአፈጻጸም አቅጣጫዎችና ስልቶች፣

- የ 2 ኛ ደረጃ ት/ቤት አቅርቦትን በተመለከተ የመጀመሪያው አማራጭ የመጀመሪያው የአፈፃፀም ስልት በመንግስትና በህብረተሰብ ትብብር ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን በአዲስ መገንባት፣ በነባሮች ላይ ተጨማሪ ክፍሎችን በመገንባት አቅርቦቱን ማስፋት
- ሁለተኛው የአፈፃፀም ስልት የግል ባለሃብቱ 2 ኛ ደረጃ ት/ቤት ገንብቶ ለአገልግሎት እንዲያቀርብ ማድረግ።

- የ 11 ኛና የ 12 ኛ ክፍል ትምህርት የሚሰጥባቸውን ለማደራጀት ቢያንስ በወረዳ ደረጃ አንድ ት/ቤት መምረጥና ከወዲሁ ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት ማጠናቀቅ፣ በተቻለ መጠን አንድ መሰናዶ ት/ቤት ለ 3 2 ኛ ደረጃ ት/ቤት በአማካይ ቦታ ላይ እንዲኖር በማድረግ ነው፡፡
- በቤተሰብ፣ በኢኮኖሚና በመሳሰሉ ችግሮች ትምህርታቸውን መማር ለማይችሉ ተማሪዎች በተመረጠ ሁኔታ የትምህርት ወጭያቸውን ለመሸፈን የሚያስችል ድጋፍ ከህብረተሰቡ፣ ከአድሮችና ከበጐ አድራጐት ድርጅቶች እንዲያገኙ ማድረግ፡፡

## 6.2.4. የተቀናጀ የተግባር ተኮር የጐልማሶች ትምህርትን በሁሉም የገጠርና ከተማ ቀበሌዎች እንዲሰጥ ለማድረግ የምንከተላቸው የአፈጻጸም አቅጣጫዎችና ስልቶች፣

- አመቻቾችን በሁሉም ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች ለመመደብ ትምህርቱን በብቃት ለመስጠት በ 2014 ዓ.ም በቂ ቁጥር ያላቸው አመቻቾች እንዲቀጠሩና ሰልጥነው እንዲሰማሩ ማድረግ፣
- ኘሮግራሙን በባለቤትነት የሚመራው ቦርድ በየደረጃው ማቋቋምና በተቋቋመባቸው ደግሞ ማጠናከር፣
- ኘሮግራሙን በውጤታማነት ለመፈፀም ከመንግስት የተለያዩ አካላትና የልማት ድርጅቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በቅርበት መስራትና በላቀ ደረጃ የሚሳተፉበትን አሰራርና አደረጃጀት መዘርጋት የስምምነት ቻርተር መፈራረም፤
- በትምህርት መዋቅሩ ውስጥ የተግባር ተኮር ትምህርት አደረጃጀት በተሟላ ሁኔታ መፈጠርና መጠናከር የሰው ሃይሉን በተለይ በወረዳ ደረጃ መሟላት አለበት፡፡
- ራሱን የቻለ የህዝብ ንቅናቄ ዕቅድ አዘጋጅቶ ስራ ላይ ማዋል፣
- በየአካባቢው ያሉ የትምህርት ተቋማትን ለማስተማሪያነት መጠቀም፣
- ከአርሶ አደሩ ስራና አኗኗር ጋር የሚስማማ ኘሮግራም አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የተግባር ተኮር የጐልማሶች ትምህርትን አጠናክሮ ማስቀጠል የትምህርት ለሁሉም ግብን ለማሳካት ትልቅ ሚና ያለው ከመሆኑም በላይ መንግስት ሀገራችንን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ እንድትሰለፍ ለማድረግ የያዘው ራዕይ ሊሳካ የሚችለው እያደገ የመጣው የሀገራቱ ኢኮኖሚ የሚጠይቀውን የተማረ ህብረተሰብ ማፍራት ሲችል ብቻ መሆኑ ግንዛቤ ተይዞ ኘሮግራሙን ለማስፈፀም ከማንኛውም አካል በላይ የመንግስት ሚና /Commitment / ከሁሉም የላቀ መሆን ይገባዋል፡፡ በመሆኑም የተግባር ተኮር የጐልማሶች ትምህርትን ለማስፋፋት የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት ከሚያስፈልገው አጠቃላይ ወጪ አብዛኛውን መንግስት እንዲሸፍን ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ሊተገበር ይገባል፡፡

## 6.2.5. የት/ቤቶችን መሰረተ ልማት በስታንዳርዱ መሰረት ለማሟላት የአፈጻጸም አቅጣጫዎችና ስልቶች

- የት/ቤቶችን የመጠጥ ውሃና መፀዳጃ ቤቶች በማዘጋጀት ትም/ቢሮ፣ ጤና ቢሮና ውሃ ቢሮዎች በጋራ የሚሰሩ ሲሆን የጋራ የስምምነት ቻርተር አዘጋጅተው ተግባራዊ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ይህንን አሰራር ተከትሎ አደረጃጀቱን በዞንና በወረዳም በማስፋት ለተግባሩ ባለቤት መስጠትና ለ WASH ኘሮግራም ተፈፃሚነት ጠንክሮ መስራት፣
- የአካባቢውን ህብረተሰብና መያዶችን በማስተባበር በተለይ ሴቶች መፀዳጃ ቤት እንዲኖረው ማድረግ ላይ ርብርብ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
- በንፁህ መጠጥ ውሃና የመፀዳጃ አገልግሎት አስፈላጊነት ላይ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግና በንቃት እንዲሳተፉ ማድረግ

### 6.2.6. በትምህርት ስራ ውስጥ የህብረተሰብ ተሳትፎ ማሳደግ የምንከተለው የአፈጻጸም ስልትና አቅጣጫዎች፣

- ወላጆችና መላው ህብረተሰብ በትምህርት ስራ ላይ በተለይም በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች የሚኖረውን ተሳትፎ በላቀ ደረጃ ለማሳደግ በስምምነትና በፍላጎት ተግባብቶ እንዲፈፀሙ ማድረግ፣
- የወላጆች ጉባዔና ኮንፈረንሶች በት/ቤት ደረጃ ማዘጋጀት
- ወላጆችንና መላውን ህብረተሰብ በት/ቤቱ ዕቅድ ዝግጅት፣ ትግበራና ግምገማ ሂደቶች ላይ በንቃት እንዲሳተፍ ማድረግ
- የወተመህ አደረጃጀትን ማጠናከር
- በተማሪዎች ምዝገባና በትምህርት ወቅት ተማሪዎችን በማስመዝገብና አሳላሽ ተማሪ እንዳይኖር በሚደረገው ጥረት ወላጆች ባለቤት ሆነው እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ።

### 6.2.7. የትምህርት ጥራትና ብቃትን ለማሻሻል የምንከተላቸው አቅጣጫዎችና ስልቶች፣

- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ፖሊሲ፣ ስትራቴጅና የአፈፃፀም መርሆዎች ላይ የተጠናከረ የግንዛቤ ማዳበሪያ ስራዎችን በህዝቡ ውስጥ በስፋት መስራት
- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ኘሮግራም (ECCE) በሁሉም ሴክተሮችና በአጠቃላይ የልማት ዕቅዶች ውስጥ ተካተው እንዲታቀዱና እንዲፈፀሙ ማድረግ
- ኘሮግራሙ በደንብ ተጠንቶ በተዘጋጀ ስርዓተ ትምህርት እንዲፈፀም ማድረግና ት/ቤቶች እንዲጠቀሙበት ማድረግ፣
- ቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ሳይከታተሉ በቀጥታ 1ኛ ክፍል ለሚገቡ ተማሪዎች የመስተካከያ ፕሮግራም /Adjustement Progeram/ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ፣
- በትምህርታቸው ወደ ኋላ የሚቀሩ/ Low achievers/ ተማሪዎች በተለየ ሁኔታ የሚደገፉበትን አሰራር ማመቻቸት፣
- በሙከራ ደረጃ በተመረጡ ት/ቤቶች በስራ ላይ የሚውለውን ስርዓተ ትምህርት በውጤታማነት መተግበር፣ ለዚህም ተከታታይነት ያለው ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
- ለአዲሱ ስርዓተ ትምህርት የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ደረጃ በደረጃ ማሟላት፣

# 7. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና መፍትሄዎች፣

## 7.1. ችግሮች

- የተማሪ ምዝገባን አሟልቶ በየሰፈሩ አለመፈፀም፣

- በጊዜ የለኝም መንፈስ አለመንቀሳቀስ፣
- ችግሮችን ወደ ራስ አስጠግቶ ከማየት ይልቅ ውጫዊ የማድረግ፣
- አንዳንድ ግቦች ሊደረስባቸው የማይችሉ አድርጎ አክብዶ የማየት፣
- የክትትልና ድጋፍ ስራው ሞቅ ቀዝቀዝ የማለት ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላል፣
- የተማሪ ማቋረጥ ችግር ትርጉም ባለው ሁኔታ ሊገታ አለመቻሉ፣
- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አቅርቦት ዕድገት አዝጋሚ መሆኑ፣
- የትምህርት ቤቶች ፋሲሊቲ የተሟላ አለመሆን በትምህርት ጥራት ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ መኖሩ፣
- የመምህራን ብቃትና ተነሣሽነት (Motivation) የሚጠበቀውን ያህል አለመሆን
- በዞኖች፣ በወረዳዎችና በትምህርት ቤቶች መካከል ተቀራራቢ የአፈጻጸም ደረጃ አለመኖር።

## 7.2. መፍትሔ፣

- በትምህርት አመራሩ የስልጠና መድረኮችና በአመቱ መጀመሪያ በሚካሄዱ መድረኮች በትምህርት ሥርዓት ውስጥ ባሉ ችግሮችና ችግሮቹ ካልተፈቱ ሊያስከትሉ በሚችሉት አደጋ ላይ የጋራ መግባባት መፍጠር፣ በተግባር አፈፃፀም ሂደት እያንዳንዱ ተግባር በተቀመጠለት ጊዜ ሰሌዳ መሠረት መፈፀሙን እያረጋገጡ መሄድ፣
- በዕቅዱ ውስጥም ሆነ ፈፃሚን በማዘጋጀቱ ወቅት የእያንዳንዱን አካል ችግሮች ቆጥሮ በማስቀመጥ ውጤት የሚመጣው ሁሉም አካላት ባለቤት ሆነው ችግሮቻቸውን ሲቀርፉ ብቻ እንደሆነ አቋም እንዲያዝበት ማድረግ፣
- ሁሉም ዕቅዶች ሊሳኩ የሚችሉ መሆናቸውን ከ 2013 አፈፃፀማችን የተገኙ ውጤቶችን ማሳየትና በተግባር ምዕራፍ ወቅት የሚገኙ ምርጥ ውጤቶችን እየቀመሩ ወደ ሁሉም አካባቢዎች ማድረስ፤ በሚዲያ አማካኝነት ንቅናቄውን ማጀብ፣
- ክትትልና ድጋፍ በታቀደው መሠረት መፈፀሙን እያረጋገጡ መሄድ። የክትትልና ድጋፍ አግባባችን በየደረጃው ያሉ ችግሮችን በሚፈታና ተደማሪ አቅም ሊሆን በሚያስችል ሁኔታ መፈጸም።
- አካባቢያዊ መፍትሄ የችግሮች ሁሉ የመፍቻ አቅጣጫ አድርጎ በመቀበል መፈፀም፣